ክፍል ሁለት

በንግግር የሚገለጹ ስጦታዎች

ምዕራፍ		ገጽ
5.	በጥበብ የመናገር ስጦታ.....	80
6.	በዕውቀት የመናገር ስጦታ.....	95
7.	በልዩ ዓይነት ልሳን የመናገርና በልሳኖች የተነገረውን የመተርጎም ስጦታ.....	108
8.	ትንቢት የመናገር ስጦታ.....	136
9.	የወንጌል ሰበካ ስጦታ.....	159
10.	የማስተማር ስጦታ.....	170
11.	የመምከር ስጦታ.....	182
12.	የሐዋርያነት ስጦታ.....	197
13.	የእረኛነት ስጦታ.....	207

ምዕራፍ
5

በጥበብ የመናገር ስጦታ

"መንፈስ ቅዱስ ለአንዱ ሰው በጥበብ የመናገር ችሎታን ይሰጠዋል..."
(1ኛ ቆሮ. 12፥8)።

አንዳንድ የሥነ መለኮት ምሁራን ዘጠኙን የጸጋ ስጦታ ዎች በሦስት መደብ ወይንም ክፍል ይከፍሏቸዋል። አንደኛውን ክፍል *"የአዕምሮ ስጦታዎች"* ብለው የመደቧቸው ሲሆን፥ እነርሱም፥-

1ኛ) በጥበብ መናገር
2ኛ) በዕውቀት መናገር
3ኛ) የመንፈስ መለየት ስጦታዎች ናቸው።

በሁለተኛው ክፍል የመደቧቸውን ደግሞ *"ተአምራዊ የሆኑ የኃይል ስጦታዎች"* ሲሏቸው፥ እነርሱም፥-

1) የመፈወስ ስጦታ
2) ተአምር የማድረግ ስጦታ
3) የእምነት ስጦታ ናቸው።

በሦስተኛው ክፍል የመደቧቸውን ደግሞ "የንግግር ስጦታ ዎች" ሲሏቸው፥ እነርሱም፦

1ኛ) በልዩ ልዩ ልሳን መናገር

2ኛ) በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም

3ኛ) የትንቢት ስጦታ የተባሉት ናቸው።

1. "ጥበብ" ከጸጋ ስጦታዎች ሁሉ መጀመሪያ ለምን ተጠቀሰ?

ሐዋርያው ጳውሎስ የመጀመሪያውን የቆሮንቶስን መል ዕክት በተለይ ምዕራፍ 12፥ 13ንና 14ን ዝም ብሎ ወይንም ያለ ምክንያት አልጻፈውም። በወቅቱ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲ ያን ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን በሚመለከት ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ጭቅጭቅ ተፈጥሮ ስለነበር ያንን ለማስተካከል ወይንም ለጥያቄያቸው መልስ እንዲሆን የጻፈላቸው መልዕክት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምዕመናን በጻፈው በመጀመሪ ያው ደብዳቤው ላይ *"የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን"* ሲዘረዝር፥ *"በጥበብ የመናገር"* ስጦታን መጀመሪያ ያደረገበት አጥጋቢ ምክንያት ሳይኖረው እንዲሁ እንዳላደረገው እንገምታለን። በሰው ዘንድ ጎልተው የሚሰሙ፥ ደምቀው የሚታዩ ስጦታዎች፥ ይኸ ውም *በልዩ ልዩ ልሳን መናገር፥ በልሳን የተነገረውን መተር ጎም፥ የመፈወስና ተአምር የማድረግ* የመሳሰሉ ስጦታዎች የነበራቸው አንዳንድ አማኞች፥ እኛ ከሁሉም እንበልጣለን በማ ለት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛ ሁከትና ረብሻ ይፈጥሩ ስለነበረ፥ እንደነዚህ ዓይነቶቹን አማኞች መስመር ለማስያዝ፥ ወይንም ለማረም የጻፈው እንደሆነ የሥነ መለኮት ምሁራን ይናገራሉ። በዝርዝሩ ላይ *የቃንቃ መናገርን ስጦታ* አንደኛ ያላደረገው፥ ስጦታው ከሌሎች ስጦታዎች እኩል ለቤተ ክርስ

የሚበልጥ እንዳልሆነ ለማሳየት ነበር። በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12፥ 13ና 14 ላይ ስለ *መንፈስ ቅዱስ ስጦታና* አጠቃቀም ሰፊ ትምህርት እንደሰጠ እናያለን።

ሐዋርያው ጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ሲዘረ ዝር *"በጥበብ መናገርን"* መጀመሪያ፥ ቋንቋን መጨረሻ ያደረ ገበት ምክንያት የቋንቋ ስጦታ ከሁሉም ስጦታዎች ይበልጣል ብለው ይገምቱ የነበሩት የቆሮንቶስ አማኞች ግምታቸው ልክ እንዳልሆነ ትምህርት ሊሰጣቸው አስቦ ይሆን? በጥበብ የመናገር ስጦታ መጀመሪያ በመሆኑ ከተቀሩት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ዎች ሁሉ ይበልጣል ማለት ይሆን? ጳውሎስ ይህን ያደረገው አንዱን ስጦታ ከሌላው ጋር ለማበላለጥ እንዳልሆነ እርግጠኞች ነን። ስጦታዎች ሁሉ እኩልና እንዲሁም ለቤተ ክርስቲያን ሁሉም የሚያስፈልጉ በመሆናቸው፥ የስጦታዎችን ዝርዝር በቅ ደም ተከተል ማስቀመጥ አንዱ ከሌላው ይበልጣል ማለት እን ዳልሆነ ግልጽ ነው። የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ባለበት አካባቢ ሁሉ ከስጦታዎች ሁሉ ተጋኖ የሚነገረው፥ ምዕመናኑ ሁሉ እንዲኖረው የሚፈልገው ስጦታ ቢኖር *በልሳን መናገር* እንደ ሆነ እናውቃለን። *በልሳን መናገር* አያስፈልግም ማለት ሳይሆን፥ ለቤተ ክርስቲያናችን የሚያስፈልገን ስጦታ በቋንቋ መናገር ብቻ ሳይሆን፥ ከዛያ የሚበልጡ ስጦታዎች ሁሉ ያስፈልጉናል ለማለት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 13፥13 ላይ *"እምነትና ተስፋ ፍቅርና እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ! ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር"* ነው ይላል። አንድ ክርስቲያን ጸሐፊ፥ "ሚዛናችውን የለቀቁ አንዳንድ የዘመኑ ክርስቲያኖች ይህን ጥቅስ የሚያነቡት *እምነትና ተስፋ ፍቅርና እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ! ከእነዚህም የሚበልጠው "በቋንቋ መናገር* ነው ብለው እንደሆነ እገምታለሁ" አለ። ጳውሎስ ለቤተ ክርስ ቲያን ዕድገት የጥበብንም ጠቃሚነት ይግለጽ እንጂ፥ ከሌሎቹ ስጦታዎች ሁሉ ይበልጣል ሲል አንሰማውም።

2. "ጥበብን መናገር" ምን ማለት ነው?

ለመሆኑ *"ጥበብ መናገር"* ማለት ምን ማለት ነው? ይህ ስጦታ ሁለት ቃል እንደያዘ እናያለን። ይኸውም *"ጥበብና"* እንዲሁም *"መናገር"* ናቸው። በግሪክ ቋንቋም *"ሎጎስ ሶፍያ"* ተብለው በሁለት ቃላት ይጠራሉ። *"ሎጎስ"* ማለት *"ቃል"* ወይ ንም *"መልዕክት"* ማለት ነው። ቃሉም ተራ ቃል ሳይሆንና በመንፈስ ቅዱስ የተነገረ መለኮታዊ ቃል ማለት ነው። *"ሶፍያ"* የሚለው ቃል ደግሞ *"ጥበብ"* ማለት ሲሆንና ይሄም የሰው የተፈጥሮ ጥበብን ወይንም ችሎታን የሚገልጽ ሳይሆንና "መለ ኮታዊ" የሆነውን የእግዚአብሔርን ፈቃድና ወይንም የመንፈስ ቅዱስን ሀሳብ ተረድቶ ለሰዎች የመግለጽ ችሎታ ነው። መንፈ ሳዊ መመሪያን ተከትሎ ወቅታዊ የሆነውን የቤተ ክርስቲያንን ችግር የመፍታት ችሎታ ነው። ስለዚህ *"ሎጎስ ሶፍያ"* ማለት *"የጥበብ ቃል"* ማለት ነው። *"ጥበብ የመናገር ስጦታ"* በሁለት ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላል። ይኸውም፥

2.ሀ. የሥነ መለኮት ጥበብ (Theological Wisdom)

የሥነ መለኮት ጥበብ (TheologicalWisdom) ምን ማለት ነው? ጳውሎስ "ጥበብን" ሲገልጽ፥ *"እግዚአብሔር አስቀድሞ ከዘመናት በፊት ለደህንነታችን የወሰነውን ዕቅድ ተሰውሮ የነበ ረውን መግለጥ..."* ይለዋል። ለብዙ ዘመን ተሰውሮ የቆየውና አሁን ግን በክርስቶስ ኢየሱስ እንዴት እንደተገለጸ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 2 ላይ ጠቅሶታል።

ለሰው ልጅ ዘለዓለማዊ ደህንነትን ለመስጠት ኢየሱስ መሞት እንደነበረበት እግዚአብሔር ከመጀመሪያው ጀምሮ ያቀ ደው ዕቅድ ነበረ። ይሁን እንጂ ይሄ ዕቅድ ለብዙ ዘመን ማለትም የተወሰነው ጊዜ እስኪደርስ ድረስ ድብቅ ወይንም

ምስጢር ነበር። እንደ ጳውሎስ አነጋገር የእግዚአብሔር ጥበብ "ድብቅ" ወይንም ሁሉም ሰው የማያውቀው ነው። ዓለም ያደነ ቃቸው ፈላስፋዎች እንኳን ያንን ምስጢር የመረዳት ችሎታ የላቸውም። ምክንያቱም *"መለኮታዊ ጥበብ"* ምስጢራዊው ከሆ ነው ከደህንነት ዕቅድ ጋር የተያያዘ በመሆኑ፥ ለሥጋዊ ሰው ፍጹም ግልጽ አልነበረም። የሰውን የኃጢአት ዋጋ ለመክፈል የክርስቶስ በመስቀል መሞት ታላቁን "የእግዚአብሔርን ጥበብ" ሲገልጽ፥ ለዓለም ግን ይህ ሀሳብ እንደ ሞኝነት ይታያል። ለመ ንፈሳዊ ሰው ግን *"እውነትን መረዳት"* መቻል ነው።

የክርስቶስ መስቀል የሰላም ምንጭ ሲሆንና ለዓለም ሰው የሚታየው ግን ሁከትና ረብሻ እንደሆነ ነው። *የክርስቶስ መስቀል* ለዓለም መከራን የሚያሳይ ቢሆንም፥ የመስቀሉን ምስ ጢር ለተረዱት አማኞች ግን በውስጡ ፈውስን ይዟል። *የክርስ ቶስ መስቀል* ሞት ያለበት ቢሆንም፥ ሕይወት ሰጪ ነው። *የክርስቶስ መስቀል*፥ ደካማነት ቢመስልም፥ ተወዳዳሪ ለሌለው ኃይል ምክንያት ነው። *የክርስቶስ መስቀል*፥ በሞት መቀጣት ቢሆንም፥ በውስጡ ምህረትና ይቅርታም አለበት። *የክርስቶስ መስቀል*፥ ጥላቻን ቢያሳይም፥ ፍቅርም ይታይበታል። እንግዲህ የክርስቶስ መስቀል ከላይ እንደዘረዘርነው፥ የያዘውን ድብቅ ሀሳብ ለመረዳት፥ የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ ያስፈልገናል። ሰው ውስን በሆነው በስጋዊ አዕምሮው ወሰን የሌለውን የእግዚአብ ሔርን ጥበብ መረዳት አይችልም።

2.ለ. ተግባራዊ ጥበብ

ሁለተኛው ጥበብ፥ *"ተግባራዊ ጥበብ"* ነው። ጳውሎስ "ጥበብ መናገር" ሲል *"የሥነ መለኮት ጥበብ"* ይኸውም የእግ ዚአብሔር አጠቃላይ የደህንነትን ታሪክ መረዳት ቢሆንም፥

ከዚህ ሌላ ሀሳብ እንዳለ እናውቃለን። ያም *ተግባራዊ* ጥበብ ነው። እግዚአብሔር ልጆቹ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሲያልፉ፥ ምንማድረግ እንዳለባቸውና ምን ዓይነት መልስ መስጠት እን ዳለባቸው ባለማወቅ ግራ በተጋቡበት ወቅት *መለኮታዊ* ጥበብን ይሰጣቸዋል። ይሄን ዓይነቱን ጥበብ ኢየሱስ በምድር በነበረበት ዘመን ብዙ ጊዜ ሲጠቀምበት አይተናል።

ጻፎችና ፈሪሳውያን ኢየሱስ ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር ሲበላ አይተውት "ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር ይበላልI ይጠጣል" ብለው ሲከሱት የሰጣቸው መልስ *መለኮታዊ* ጥበብ እንዳለበት ግልጽ ነው። *"ሕመምተኞች እንጂ ብርቱዎች ባለ መድኀኒት አያስፈልጋቸውምI ኃጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም"* አላቸው (ማር. 2፥17)። ጥበብ የተሞላበት የኢየሱስ መልስ፥ ሊቃወሙትና ሊተቹት የተነሱትን ጻፎችና ፈሪሳውያንን አፋቸውን እንዳስያዘ እናውቃለን።

የኢየሱስን ኃይል ለማቃለል ከሳሾቹ *"...በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል"* ብለው በተናገሩት ጊዜ ኢየሱስ ከሳሾቹን ጠርቶ በጥበብ የተሞላ ትምህርት እንዲህ ሲል ሰጣቸው። *"..ሰይጣን ሰይጣንን ሊያወጣው እንዴት ይችላል? መንግ ሥትም እርስ በርስዋ ኩተሊያየች ያቺ መንግሥት ልትቆም አትችልምI ቤትም እርስ በርሱ ኩተሊያየ ያ ቤት ሊቆም አይ ችልም። ነገር ግን አስቀድሞ ኃይለኛውን ሳያስር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ ዕቃውን ሊበዘብዝ የሚችል የለምI ከዚ ያም ወዲያ ቤቱን ይበዘብዛል"* አላቸው (ማር. 3፥23-27)። ሰይጣንም ራሱን ተቃውሞ ኩተሊያየ መጨረሻ ይሆንበታል እንጂ ሊቆም አይችልም።

አንዳንድ ከፈሪሳውያንና ከሄሮድስ ጋር የነበሩ ሰዎች ኢየሱስን ከቄሣር ጋር ለማጋጨት አስበው *"...መምህር ሆይ! የሰውን ፊት ሳትመለከት በእውነት የእግዚአብሔርን መንገድ*

ታስተምራለህና እውነተኛ እንደሆንህ ለማንም እንዳታደላ እና ውቃለንI ለቄሳር ግብር መስጠት ተፈቅዶአልን ወይንስ አልተ ፈቀደም? እንስጥ ወይስ አንስጥ? አሉት። እርሱ ግን ግብዝነ ታቸውን አውቆ *"ለምን ትፈትኑኛላችሁ? አየው ዘንድ ዲናር አምጡልኝ አላቸው።* እነርሱም *አመጡለት። ይህቺ* መልክ ጽሕፈቲቱስ የማን ናት? *አላቸውI* እነርሱም *የቄሣር ናት አሉት።* ኢየሱስም መልሶ *የቄሣርን ለቄሣር፥ የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር አሰረክቡ አላቸው"* (የማር. 12፥13-17)። በጥበብ የተሞላ መልስ ስለሰጣቸው በጣም ተደነቁ። የክርስቶስን ጥበብ ደጋግመው የሰሙ አንዳንድ ሰዎች አንድ ጊዜ በመደነቅ *"ይህን ጥበብና ተአምራት ይህ ከወዴት አገኘው?"* ብለው እንደጠየቁት እናስታውሳለን (የማቴ. 13፥54)። በዚህ ዓይነት መልክ ክርስቶስ በሌሎችም ብዙ ሁኔታዎች በጥበብ እንደተናገ ረና መልስ እንደሰጠ ከመጽሐፍ ቅዱስ መጥቀስና ማሳየት እን ችላለን።

ይህን *"በጥበብ መናገር"* በአዲስ ኪዳን ብቻ ሳይሆን በብሉይ ኪዳንም ውስጥ ብዙ የተጠቀሙበት ሰዎች እንደነበሩ እናውቃለን። ከብዙዎቹ መካከል አንደኛው ሰው ዮሴፍ ነው። በአንድ ወቅት የፈርኦንን ህልሙንና የህልሙን ፍቺ የሚናገር አዋቂ በግብጽ ምድር ማንም አልተገኘም ነበር። *"...ወደ ህልም ተርጓሚዎች ሁሉ ወደ ግብፅ ጠቢባንም ሁሉ ልክ ወደ እርሱ ጠራቸውI ፈርኦንም ሕልሙን ነገራቸውI ነገር ግን ከእርሱ ለፈርኦን የሚተረጉም አልተገኘም"* ይላል (ዘፍ. 41፥8)። እግዚአብሔር ለዮሴፍ ምስጢርን የማወቅ፥ ህልምን የመፍታት ጥበብ ሰጥቶት ስለነበረ፥ ዮሴፍ ሕልሙን ለመፍታት አልተቸገ ረም። ችሎታው ከራሱ የመነጨ ሳይሆን ከእግዚአብሔር እንደ ሆነ ፈርኦንም እንኳን ስለተረዳ ዮሴፍን እንዲህ አለው *"...እንደ አንተ ያለ ብልህ አዋቂም ሰው የለምI እግዚአብሔር ይህን*

ሁሉ ገልጠልሃልና። አንተ በቤቴ ላይ ተሾምI ሕዝቤም ሁሉ ሊቃልህ ይታዘዝI እኔ በዙፋኔ ብቻ ከአንተ እበልጣለሁ" አለው (ዘፍጥ. 41፥39-40)።

ሁለተኛው በጥበብ የተሞላ ሰው *ሠለሞን* ነበር። የጥበቡ ምክንያት፥ ሠለሞን ከአምላኩ ጋር የቀረበ ግንኙነት ስለነበረው እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። *"...የዳዊት ልጅ ሠለሞንም በመንግሥቱ በረታI አምላኩም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረ"* ይላል (2 ዜና 1፥1)። ሠለሞን ከእግዚአብሔር ጋር የተቀራረበ ግንኙነት ስለ ነበረው፥ እግዚአብሔር በሌሊት ወደ ሠለሞን ቀርቦ *"...ምን እንድሰጥህ ለምነኝ"* አለው። ለእኔና ለአናንተ ዛሬ ለሠለሞን የቀረበለትን ዓይነት ጥያቄ ቢቀርብልን ምን ዓይነት መልስ እንሰጥ ይሆን? አንዳንዶቻችን "በቋንቋ እንድናገር፥ ሰዎች ሁሉ እንዲያደንቁኝ የመፈወስ ስጦታ፥ ተአምር የማድረግ ስጦታ፥ የመግለጥ ስጦታ ስጠኝ" ብለን እንደምንጠይቅ እርግጠኞች ነን፥ ሠለሞንም ሌላ ነገር መጠየቅ ይችል ነበር። ሠለሞን ግን "ምን እንድሰጥህ ትፈልጋለህ?" ብሎ እግዚአብሔር ለጠየቀው ጥያቄ ሲመልስ፥ *"...በዚህ ሕዝብ ፊት እወጣና እገባ ዘንድ ጥበብንና ዕውቀትን ስጠኝI ይህን በሚያህል በዚህ በታላቅ ሕዝብህ ላይ ይፈርድ ዘንድ የሚችል የለምና"* አለው (2 ዜና 1፥10)።

እግዚአብሔርም የሠለሞንን ጥያቄ አደነቀI ማድነቅ ብቻ ሳይሆን ከጠየቀው በላይ አትረፍርፎ ሰጠው። *"...ይህ በልብህ ነበርናI ባለጠግነትንና ሀብትን፥ ክብርንና የጠላቶችህን ነፍስ፥ ረጅምም ዕድሜን አልለመንህምና፥ ነገር ግን ባነገስሁህ በሕዝቤ ላይ ለመፍረድ ትችል ዘንድ ጥበብንና ዕውቀትን ለራስህ ለምነ ሃልናI ጥበብና ዕውቀትን ሰጥቼሃለሁI ከአንተ በፊትም ከነበሩት፥ ከአንተም በኋላ ከሚነሱት ነገሥታት አንድ ሰንኳ የሚመስልህ እንዳይኖር፥ ባለጠግነትንና ሀብትን፥ ክብርንም እሰጥሃለሁ አለው"* (2 ዜና 1፥11-12)።

ሠለሞን ይህን እግዚአብሔር የሰጠውን ጥበብ ሕዝቡን ሲያስተዳድር እንደተጠቀመበት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታሪኩን እናነባለን። በሁለት ሴቶች (እናቶች) መካከል የተነሳውን ጭቅ ጭቅ ለመፍታት ሠለሞን በምን ዓይነት ጥበብ ፍርድ እንደ ሰጠ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ታሪኩን በዚህ ትምህርት ውስጥ ለማቅረብ ጊዜና ቦታ ስለሚፈጅ፥ መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ምዕራፍ 3 ላይ ስለተገለጸ በግላችሁ እንድታነቡት ለእናንተው እተውላችኋለሁ። ለመጥቀስ የምፈልገው ነገር ቢኖር፥ የእስራኤል ሕዝብ ሠለሞን የሰጠውን ፍርድ በማድነቅ የተናገረውን ነው። *"...ንጉሡም የፈረደውን ፍርድ እስራኤል ሁሉ ሰሙI ፍርድን ለማድረግ የእግዚአብሔር ጥበብ እንደ ነበረበት አይተ ዋልና ንጉሡን ፈሩ"* ይላል (1ኛ ነገሥ. 3፥28)።

የሳባ ንግሥት ስለ ሠለሞን ጥበብ ሰምታ እውነተኛነቱን ለማረጋገጥ "በእንቆቅልሽ ልትፈትነው" እንደሄደች እናውቃለን። የሠለሞንን ጥበብ በራሷ ዓይን አይታ በጆሮዋ ከራሱ ከሠለሞን ሰምታ መጨረሻ ላይ እንዲህ አለች። *"...ስለ ነገርሀና ስለ ጥበብህ በአገሬ ሳለሁ የሰማሁት ዝና እውነት ነው። እኔም መጥቼ በዓይኔ እስካይ ድረስ የነገሩኝን አላመንሁም ነበርI እነሆም እኩሌታውን አልነገሩኝም ነበርI ጥበብሀና ሥራህ ከሰማሁት ዝና ይበልጣል። በፊትህ ሁልጊዜ የሚቆሙ፥ ጥበብህንም የሚሰሙ ሰዎችህና እነዚህ ባሪያዎችህ ምስጉኖች ናቸው"* አለችው (1ኛ ነገሥት 10፥6-8)።

3. ሌሎች ልዩ ልዩ ዓይነት ጥበቦች

3.1. የተፈጥሮ ጥበብ

ሰው በተፈጥሮ ያገኘው *"የማሰብ ችሎታው"*፥ በመኖር ከሚያገኘው ልምምድ ጋር ሲጣመር፥ በኑሮው ላይ የሚያጋጥሙትን ልዩ ልዩ ችግሮችንና እንቅፋቶችን መመርመርና መፍ

ታት ያስችለዋል። ይህን ዓይነቱ "የተፈጥሮ ጥበብ" ይባላል። ይህ ጥበብ እግዚአብሔርን የሚቃወም ጥበብ አይደለም። የአዕምሮ ማመዛዘንና የመመራመር ፍሬ ሲሆን፥ ሰው ለሚያጋጥመው ችግር ጥሩ መልስ የሚሰጥበት ነው። ይሁን እንጂ፥ ይህን ዓይነት የተፈጥሮ ጥበብ ያላቸው አንዳንድ ሰዎች፥ ይህን ጥበብ ከእግዚአብሔር እንደተቀበሉት አያውቁም። የኤፌሶን ሰዎች የጳውሎስን ጓደኞች ጋይዮስንና አርስጥሮኮስን ለማዳን የተጠቀሙበት ጥበብ ይህን ዓይነቱ ጥበብ ነበር (የሐዋ. 19፥ 23-41)።

3.2. የዓለም ጥበብ

ይህን ዓይነቱ ጥበብ ከፉ ስለሆነ እግዚአብሔር ራሱ ይቃ ወመዋል። *"...የጥበበኞችን ጥበብ አጠፋለሁ፤ የአስተዋዮችንም ማስተዋል እጥላለሁ ተብሎ ተጽፏልና"* ይላል (1 ቆር. 1፥19)። እግዚአብሔር ይህን ጥበብ የሚቃወምበት ምክንያት "ዓለምን እግዚአብሔር አልፈጠረም፤ ሰው መዳን የሚችልበት ሌላ መን ገድ አለው፤ ሰው በእግዚአብሔር ብቻ መታመን አያስፈልገ ውም" ስለሚል ነው። ስለዚህ ጥበብ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር እንዲህ ይላል *"...ይህ ጥበብ ከላይ የሚወርድ አይደለም፤ ነገር ግን የምድር ነው፤ የሥጋም ነው፤ የአጋንንትም ነው"* ይላል (ያዕቆብ 3፥15)።

3.3. አጠቃላይ ጥበብ

ሌላው ለሚጠይቅ አማኝ ሁሉ የሚሰጥ "አጠቃላይ ጥበብ" ነው። *"ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፤ ለእርሱም ይሰ ጠዋል"* ይላል (ያዕ. 1፥5)። ይህን ዓይነቱን ጥበብ ያዕቆብ

ሲገልጸው *"ላይኛይቱ ጥበብ ግን በመጀመሪያ ንጽህት ናት፤ በኋላም ታራቂ፥ ገርና እሺ ባይ፥ ምህረትና በጎ ፍሬ የሞላ ባት፥ ጥርጥርና ግብዝነት የሌለባት ናት"* ይላል (ያዕ. 3፥17)።

ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ መልዕክቱ የጠቀ ሰው *"የጥበብ መናገር"* ስጦታ ከላይ ካየናቸው የተለያዩ ጥበቦች ሁሉ የተለየ ነው። ይሄ ጥበብ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚነካ ነው። የጊዜውን ችግር ቃሉን በመጠቀም የሚፈታ ወይንም መልስ የሚሰጥ ነው። ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ማንንም አይመክርም። ይህ ስጦታ ያለው ሰው የብዙዎችን ልብ ወደ እግዚአብሔር እንዲያዘነብል መቀስቀስ ይችላል። ፈርአን የዮሴ ፍን ጥበብ ካየ በኋላ ፊቱን ወደ እግዚአብሔር አቀና። *"...እግ ዚአብሔር ይህን ሁሉ ገልጦልሃል..."* አለው (ዘፍ. 41፥39)። የሳባ ንግሥትም የሰለሞንን ጥበብ አይታ እግዚአብሔርን እንዲህ እያለች አከበረች *"..አንተን የወደደ በእስራኤልም ዙፋን ያስቀመጠህ አምላክህ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን..."* አለች (1ኛ ነገሥት 10፥9)።

"የጥበብ መናገር" ስጦታ ከሌሎች ዓይነት ጥበቦች በምን ይለያል? *"የጥበብ መናገር"* ስጦታ ከሌላው ዓይነት ጥበብ የሚ ለይበት፥ ስጦታው ያለው ሰው የሚጠቀምበት ሁኔታ ወሳኝ ነው። ስጦታው በአማኙ ሕይወት አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በተደጋጋሚ ሲሠራ የታየ እንደሆነ ያ ሰው *"የጥበብ መናገር"* ስጦታ እንዳለው ይታወቃል። ሌላው መለያ፥ የጥበቡ ውጤት ንጹህ፥ በሰላምና በምህረት የተሞላ፥ የዋህ፥ ግብዝነት የሌለበት፥ የማያወላውል፥ እንዲሁም ፍሬያማ የሆነ እንደሆነ ነው። ስጦታው ያለው ሰው የሚሰጠው አስተያየትና ውሳኔ፥ በአካባቢው ባሉት ሰዎች ዘንድ ተቀባይነትን ያገኛል። ብዙዎች ችግር ሲደርስባ ቸው፥ በግላቸው መፍታት የማይችሉት የሕይወት ዕንቆቅልሽ ሲያጋጥማቸው ምክር፥ ሀሳብ ፍለጋ ወደዚህ ሰው ይመጣሉ።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስልጣን ቢኖረውም፥ ባይኖረውም ተደማጭነት ያለው ሰው ይሆናል።

"የጥበብ መናገር" ስጦታ ያለው ሰው፥ በአካባቢው ያሉት ሁሉ፥ ሁልጊዜ በሚወስነው ውሳኔ፥ በሚሰጠው ምክር ይስማማሉ ማለት አይደለም። ባይስማሙም በውስጡ ስላለው ጥበብ እግዚአብሔርን ያከብራሉ። የማይስማሙበት ምክንያት የሚሰጠው ሀሳብና ምክር ጥሩ ባለመሆኑ፥ ወይንም "የእግዚአ ብሔር ፈቃድ የለበትም" ብለው ሳይሆን፥ አንዳንዶቹ ከአሮጌው ተፈጥሮአቸው ያልተላቀቁ በመሆናቸው፥ መንፈሳዊ የሆነውን ነገር መቀበል ስለሚያቅታቸው ነው። *"የጥበብ መናገር"* ስጦታ ያለው ሰው ምልክቱ፥ መንፈስ ቅዱስ የትህትናን መንፈስ ያለ በሰው ነው። ባለው ጥበብ ራሱን ከሌሎች የተሻለ እንደሆነ አድርጎ የሚመለከት፥ ከሆነ፥ ያ ሰው "አለኝ" የሚለው ጥበብ ከመንፈስ ቅዱስ የመጣ መሆኑ ያጠራጥራል። *"የጥበብ መና ገር"* ስጦታ የአማኞችን አንድነት የሚያጠነክር እንጂ እርስ በርሳቸው የሚከፋፍላቸው አይደለም። ከመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ እውነተኛ "ጥበብ" ሕብረቱን ጨለማ ውስጥ የሚከት፥ ግራ የሚያጋባ ሳይሆን፥ ለቤተ ክርስቲያን የእውነትን ጮራ የሚፈነ ጥቅ፥ ትክክለኛ አቅጣጫን የሚያስይዝ መሆን አለበት።

በዘመናችን ይህ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በመካከላችን ሲሠራ የማይታየው ለምን ይሆን? ስጦታው ስለሌለ ነው ወይ ንስ በተግባር ላይ ሲውል ስለማናየው ይሆን? *የጥበብ መናገር* ስጦታ ጎልተው ከሚታዩት ከሌሎች ስጦታዎች የተለየ ነው። ይሄ ስጦታ ባላቸው አማኞች ሕይወት ውስጥ በግልጽ ሲሠራ ለብዙዎች አይታይም ይሆናል። ምናልባትም ለዚህ ይሆናል ብዙዎች ይህንን ስጦታ ለማግኘት የማይመኙት። ይሁን እንጂ፥ ቤተ ክርስቲያን *"በመከፋፈል ፈተና"* በተወጠረችበት በአሁኑ ዘመን፥ *"የጥበብ መናገር"* ስጦታ ያላቸው አማኞች

ያስፈልጓታል። እንዲሁም ውስብስብ ያለ ችግር ያለባቸውን ምዕመናን መምከር የሚችሉ *"የጥበብ መናገር"* ስጦታ ያላቸው አማኞች በዘመናችን ከምንጊዜውም የበለጠ ያስፈልጉናል።

"በጥበብ መናገርና" እንዲሁም *"በእውቀት መናገር"* መካከል ያለውን ልዩነት ለማስረዳት፥ ራልፍ ኔበር የተባሉት የሥነ መለኮት ምሁር፥ በህክምና ዓለም ውስጥ ያለውን አሠራር ጠቅሰው ለማስረዳት ይሞክራሉ። በህክምና ምርምር ውስጥ ያለው ሰው *(Medical Researcher) "በፊዚዮሎጂ፥ በጀኔቲክስና በቫክሲን"* ላይ ጊዜ የፈጀ ጥናትና ምርምር ያደርጋል። ይህን ዓይነቱን ሰው *"የዕውቀት መናገር"* ስጦታ ባለው ሰው ይመስ ሉታል። ይህን ዓይነቱ ሰው በመንፈሳዊ ዓለም ውስጥ፥ ወይንም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፥ ከላይ ያየነው "የህክምና ምርምር" ውስጥ ያለው ሰው የሚሠራውን ዓይነት ሥራ ይሠራል። *ሥራ ውም "እውነትን" መፈለግ ነው። "የጥበብ ስጦታ"* ያለው ሰው ግን፥ የህመምተኛው ችግር፥ ወይንም በሽታ ምን ዓይነት እን ደሆነ ተረድቶ የሚያስፈልገውን ሕክምና እንደሚሰጠው ሀኪም ወይንም ዶክተር ነው። *ሥራውም "እውቀትን" ወይንም "እው ነትን" በሥራ ላይ ማዋል ነው ይላሉ።*

ዶክተር ፒተር ዋግነር "የጥበብ መናገር" ስጦታን ሲገ ልጹ፥ *"የጥበብ መናገር ስጦታ፥ እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲ ያን አካል ለሆኑት አንዳንድ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ያለው ሀሳብና ዓላማ ምን እን ደሆነ የሚያውቁበት፥ እንዲሁም ችግር ሲፈጠር ችግሩን መፍ ታት የሚችሉበትን ልዩ ችሎታ የሚሰጣቸው ስጦታ ነው"* ይላሉ።

"የጥበብ መናገር" ስጦታ ያለው ሰው፥ በቤተ ክርስ ቲያን ውስጥ ችግር ሲፈጠር፥ ችግሩ ምን እንደሆነ፥ ወይንም

የችግሩ ምንጭ የት ላይ እንደሆነ ቶሎ የመረዳት ችሎታ አለው። ችግሩን ማወቅ ብቻ ሳይሆን፥ ችግሩ የሚፈታበትንም ብልሃት ያውቃል። የሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ውጤቱ ምን ዓይነት እንደሆነ በማያጠራጥር ሁኔታ ማወቅ ስለሚችል፥ ይህን ያህል "ውሳኔ ለመወሰን" አያመነታምI ወይንም ውሳኔ ለመስ ጠት ጊዜ አይፈጅም። *"የጥበብ መናገር"* ስጦታ ያለው ሰው ሀሳቡን ሲገልጽና መፍትሄ ይሆናል ብሎ ውሳኔ ሲሰጥ፥ የቤተ ክርስቲያኑ አካል የሆኑት ሁሉ ሀሳቡን መቀበል አያቅታቸውም። *"የጥበብ መናገር"* ስጦታን ለማግኘት ትምህርት ቤት ገብቶ መማርን አይጠይቅም። ይህን ስንል፥ የጌታን ሥራ ለመሥራት "ትምህርት አያስፈልግም" ማለቱ እንዳልሆነ ይታወቅልኝ።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ውሳኔ ለመስጠት ብዙ ውይይ ቶች ይደረጋሉ። አብዛኛዎቹ በሰላምና በእርቅ የሚያልቁ አይ ደሉም። ዋናው ምክንያት የውይይቱ ተካፋዮች፥ ሁሉም የራሳ ቸው ሀሳብ ተቀባይነት እንዲያገኝ አጥብቀው ስለሚታገሉ ነው። በዚህ ምክንያት ብዙ ሁከትና ረብሻ፥ የከፋም እንደሆነ መከፋ ፈልና መለያየት ይፈጠራል። በዚህ ጊዜ ነው *"የጥበብ መናገር"* ስጦታ ያላቸው በመካከላችን ተገኝተው የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ሊያስማሙና አንድ ሊያደርጉ የሚችሉት። *"የጥበብ መናገር"* ስጦታ ያላቸው፥ ከሌላው አማኝ ተለይተው የሚታወቁበት አን ዳንድ ነገር አላቸው።

1) ስሜታቸውንና የግል ፍላጎታቸውን የማያስቀድሙ፥ የእ ግዚአብሔር ሕዝብ አንድ መሆኑን እንጂ ስምና ዝናን የሚፈልጉ አይደሉም።
2) "ፍጹም ሊታረቁ አይችሉም" ተብለው የሚገመቱትን የተ ለያዩ ሀሳቦችን "የማስታረቅ ችሎታ" አላቸው።
3) ለሌሎች ሰዎች ስሜት የማይጨነቁ፥ ለሚያቀርቡት ሀሳብ

ግድ የሌላቸው አይደሉም። በውይይቱ ወቅት እያንዳንዱ የውይይቱ ተሳታፊ የሚፈልገው ነገር ምን እንደሆነ ለይ ተው ያውቃሉ።

4) "የውይይቱ ተካፋዮች ሀሳቤ ተደማጭነት አላገኘም" እን ዳይሉ የማድረግ ችሎታ አላቸው። በዚህ ዓይነት ሁሉም ደስ እንዲለው በማድረግ፥ በሕዝቡ መካከል አንድነትና ስምምነት እንዲፈጠር ያደርጋሉ። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚፈጠሩት ችግሮችና ጭቅጭቆች እየተገኙ፥ ችግሩን የሚፈቱ፥ ሊፈርስ ያለውን አንድነት መልሶ እንዲገነባ የሚያደርጉ፥ የችግራቸው ምክንያት ምን እንደሆነ የመ ረዳት ችሎታ ያላቸው አማኞች፥ *"የጥበብ መናገር"* ስጦታ ያላቸው እንደሆኑ እንረዳለን። ዛሬ በየቦታው ቤተ ክርስቲያን የምትከፋፈለው፥ ይህን ዓይነት ስጦታ ያላቸው አማኞች በመካከላችን ስለማይኖሩ፥ ቢኖሩም ስጦታቸውን እንዲጠቀሙበት ዕድል ስለማንሰጣቸው ነው።

☆ ☆ ☆ ☆



በእውቀት የመናገር ስጦታ

"...ያው መንፈስ በዕውቀት የመናገርን ችሎታ ይሰጠዋል።"
(1ኛ ቆሮ. 12፥8)

1. "እውቀትን መናገር" ትርጉሙ ገብቶን ይሆን?

ከዘጠኙ የጸጋ ስጦታዎች ውስጥ ሁለተኛው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ *"እውቀትን መናገር"* ነው። ጳውሎስ *"በእውቀት የመናገር ስጦታ"* ሲል ምን ማለቱ ነው? በዚህ ስጦታ ላይ ሁለት ፍጹም የተለያየ ሀሳብ ያላቸው ክፍሎች አሉ። የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ተከታዮች (charismatics)"በእውቀት መናገር" ምን እንደሆነ ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ። *"...እውቀት የመናገር ስጦታ ማለት በተፈጥሮ መንገድ ሰው ማወቅ የማይችለውን ነገር መለኮታዊ በሆነ መገለጥ ልዩ የሆነ መረዳትን ወይንም*

እውቀትን ማግኘት ነው" ይላሉ። ይህን ሀሳባቸውን የሚደግፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ምሳሌ ከሚያቀርቡት መረጃ አንደኛው፥ ነብዩ ናታን የዳዊትን ድብቅ ኃጢአት አውቆ *"አንተ ይህን ኃጢአት በስውር ሠርተሃልና እኔ ግን እስራኤል ሁሉ ይመለከቱ ዘንድ ይህን ነገር የቀን ብርሃን ባለበት በግልጥ አደርገዋለሁ"* በማለት ያጋለጠውን ነው (2ኛ ሳሙ. 12፥12)። ሌሎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚጠቅሷቸው ይህንን የመሳሰሉ ብዙ ታሪኮች አሏቸው። ኤልሳዕ የአሽከሩን የግያዝን ውሸት እንዳወቀ (2 ነገ. 5፥20-27)፥ ጴጥሮስ የሀናንያንና የሰጲራን በመንፈስ ቅዱስ ላይ መዋሸታቸውን አውቆ እንዳጋለጣቸው (የሐዋ. 5፥1-11) ከሚጠቅሱአቸው ታሪኮች አንዳንዶቹ ናቸው።

በዘመናችን ስለዚህ ስጦታ በየቦታው የሚጠቀስና የሚነገር ምሳሌ ቢኖር፥ የጆን ዊምበር ታሪክ ነው። *ጆን ዊምበር* የፉለር ቲዮለጂካል ሴሚናር ፕሮፌሰር የነበሩ ሲሆኑ፥ *በፔንቴኮስታል "ቤተ እምነት" (ዲኖሚኔሽን)* አካባቢ የታወቁና ተቀባይነት ያላቸው ሰው ናቸው። *ጆን ዊምበር "የዕውቀት መናገር"* ስጦታቸውን በተግባር ላይ እንዴት እንደተጠቀሙበት ከልምምዳቸው ሲናገሩ እንዲህ አሉ። "አንድ ጊዜ በአይሮፕላን ወደ አንድ ስፍራ ስበር፥ አይሮፕላኑ ውስጥ ድንገት ፊቴን ወደ አንድ አቅጣጫ ዞር ሳደርግ፥ ከፊት ለፊቴ አንድ ሰው አየሁ። እዚያ ሰው ፊት ላይ "ዘማዊ" የሚል ቃል በትልልቅ ፊደላት ተጽፎ በግልጥ ታየኝ። ጽሁፎቹ በእርግጥ በስጋ ዓይን እንደምናያቸው ሳይሆኑ፥ መንፈሳዊ አመለካከትን የሚጠይቁ ናቸው። ያም ሰው ዓይኔን አፍጥጬ ስመለከተው፥ አየኝና "ለምን ታየኛለህ? ምን ትፈልጋለህ?" ብሎ ጠየቀኝ። ይህን ብሎ ሲጠይቀኝ የሴትየዋ ስም ወደ አዕምሮዬ ድንገት ብቅ አለ። ወደ ሰውየው ጠጋ ብዬ የሴትዮዋን ስም ጠራሁና፥ ይሄ ስም ትዝ ይልሃል? ብዬ ጠየቅሁት። ፊቱ በድንጋጤ ጠቆረ፤ እንዳነጋግረ ውም ጠየቀኝ።

"እንጓዝበት የነበረው አይሮፕላን በጣም ትልቅ አይሮፕላን ስለነበረ፥ ሰዎች መጠጥ የሚጠጡበት አንድ የተለየ ክፍል ስለነበረው፥ ለመነጋገር ወደዚያ ተያይዘን ሄድን። ወደዚያ እየሄድን ሳለን፥ "ይህ ሰው ከሌላ ሴት ጋር እያመነዘረ ስለሆነ፥ ከምንዝር ተግባሩ ባይመለስ እንደማጠፋው ንገረው" ብሎ ጌታ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነገረኝ። እኔም ጌታ እንዳዘዘኝ፥ ከዚያች ቀደም ሲል ስሟን ከጠራሁለት ሴት ጋር ዝሙት ማድረጉን ካላቆመና ንስሀ ካልገባ፥ ጌታ የሚያጠፋው እንደሆነ እንድነግረው እንዳዘዘኝ ገለጽኩለት። ይህን ሲሰማ ልቡ በድንጋጤ ፍጹም ቀለጠና "ታዲያ ምን ማድረግ አለብኝ?" ብሎ ጠየቀኝ። እኔም የንስሀ ጸሎት አብሮኝ እንዲጸልይ ጠየቅሁትና ጌታን እንደ ግል መድኀኒቱ አድርጎ ተቀበለ። ይህ ሲሆን ሁለት የአይሮፕላኑ አስተናጋጆች ይሰሙ ስለነበረ፥ እነርሱም በነገሩ መደነቅ ብቻ ሳይሆን ያለቅሱም ነበር። ሚስቱም አይሮፕላኑ ውስጥ አብራው እንዳለች ነገረኝ። እኔም ሄደህ ታሪኩን በሙሉ ንገራት አልኩት። እርሱም ታሪኩን በደንብ ከነገራት በኋላ ወደ ጌታ አመጣት"። ይህን ታሪክ ስንሰማ፥ በአዕምሮአችን ውስጥ ብዙ ጥያቄዎች ስለሚፈጠሩ፥ ብዙዎቻችን ማመንና መቀበል ያቅተናል። ይህም ማለት እግዚአብሔር የተደበቀውን፥ የተሰወረውን የሰዎችን ኃጢአት መግለጥ አይችልም ማለት አይደለም። ችግራችን ያለው "እግዚአብሔር አይሠራም" በሚለው ነጥብ ላይ ሳይሆን፥ የአሠራሩ ሁኔታ ላይ ነው።

2. ስጦታችንን በትክክል ካልተጠቀምንበት፥ በማነጽ ፈንታ እናፈርሳለን

"የዕውቀት መናገርን" ስጦታ ከላይ ባየነው ሁኔታ የሚረዱት አንዳንድ ሰዎች የሚያቀርቡት ብዙ ታሪክ አላቸው። ይህን ዓይነቱ ሁኔታ፥ የማያምኑትን ወደ ጌታ በማቅረብ ፈንታ

የበለጠ እንደሚያሸሽና በክርስትና እምነት ላይ፥ በተለይ በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ላይ ትልቅ ጥያቄ እንዲፈጠርባቸው እንደሚያደርግ እናውቃለን። ጊዜውና ቦታው ቢፈቅድልኝ በሰዎች አዕምሮ ጥያቄ የፈጠሩትን ብዙ ምሳሌዎች ላቀርብላችሁ እችል ነበር። ጊዜ ለመቆጠብ አንዱን ብቻ ከዚህ ቀጥሎ አቀርብላችኋለሁ። ዓላማዬ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በዘመናችን አይሠራም ለማለት ሳይሆን፥ ስጦታው ምን እንደሆነ በትክክል ባለመረዳት ምክንያት የሚደርሰውን ስህተትና ችግር ለማመልከት ብቻ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የማይሠራ ቢሆን ኖሮ፥ ለማይሠራ ነገር የእናንተንና የእኔን ጊዜ አላጠፋም ነበር። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በዘመናችን ይሠራል ብዬ ስላመንኩ ነው አሳሳች የሆነውን ከእውነተኛው ለይታችሁ እንድታውቁ፥ ጊዜ ፈጅቼ፥ ደክሜ ይህን ትምህርት ለማቅረብ የሞከርኩት።

አንድ ጊዜ አንዲት በሕይወቷ በብዙ ትግል ውስጥ ያለፈች ሴት ጌታን ፍለጋ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደች። መዝሙሩንና ስብከቱን ሰምታ ደስ አላት። ከስብከቱ መጨረሻ ላይ፥ የዕለቱ ተናጋሪ፥ "የሲጋራ ሱስ ያለባችሁ፥ ሲጋራ ማጨስን ማቆም እየፈለጋችሁ ያቃታችሁ፥ ወደዚህ ውጡና እጸልይላችኋለሁ" በማለት ለሕዝቡ ጥሪ አደረገ። ይህቺም ሴት ከትግሏ አንደኛው ሲጋራ ማጨስን ማቆም ስለነበረ፥ በራሷ ኃይል ታግላ ማቆም እንደማትችል ስለ ተረዳች፥ ጸሎት ፍለጋ ወደ ፊት ወጥታ ከሌሎች ሰዎች ጋር ተሰለፈች። ተራዋ ሲደርስ ሰባኪው ወደዚህች ሴት ጠጋ ብሎ እጁን ጫነባት። *"የዕውቀት መናገር"* *(Word of Knowledge)* ስጦታ አለኝ የሚል ሰባኪ ስለነበረ፥ ይህቺን ሴት አይቶ ያልጠበቀችውን ዓይነት ንግግር ተናገራት። "ጌታ አንድ ነገር ስለ አንቺ ነግሮኛል፤ ጠንቋይ ቤት፥ ወይንም ከከብ ቆጣሪዎች ዘንድ ትሄጃለሽና፥ መንገድሽ የጥፋት መንገድ ነውና ተመለሺ ይልሻል የሠራዊት ጌታ" አላት።

ይህቺ ሴት ይህን ስትሰማ ደነገጠች፤ አንቀጠቀጣት። ያንቀጠ ቀጣት መልዕክቱ እውነትነት ኖሮት ሳይሆን፥ የሰባኪው ውሸት አበሳጭቷት ነው። "በእርግጥ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ነግሮት ከሆነ፥ እግዚአብሔር ውሸታም ነው፤ ወይንም ምንም አያውቅም ማለት ነው። እግዚአብሔር ካልነገረው ደግሞ ያ ሰባኪ ውሸታም ነው ማለት ነው። በዚህ ዓይነት የእግዚአብሔርን ቃል እናስተምራለን፤ በሽተኞችን እንፈውሳለን የሚሉት ሁሉ ውሸታሞች ናቸው" አለች። ስለ ራሷ ሁኔታ ስትናገር እንዲህ አለች። "በሕይወቴ ያላደረግሁት ኃጢአት የለም፤ ንጹህ ነኝ ብዬ አልቀረብኩም፤ ብዙ ነገር አድርጌአለሁ። ያላደረግሁት ነገር ቢኖር፥ ጠንቋይ ቤት፥ ወይንም ኮከብ ቆጣሪ ቤት መሄድን ብቻ ነው። ያልሄድኩት ኃጢአት ይሆንብኛል ብዬ በመፍራት ሳይሆን፥ ምንም ማድረግ እንደማይችሉ፥ ውሸታሞችና አታላዮች እንደሆኑ ስለማውቅ ብቻ ነው። ታዲያ ይሄ ሰባኪ ሄጄ ሳላውቅ "ጠንቋይ ቤት መሄድሽን አቁሚ" እንዴት ሊለኝ ይችላል? እኒዚህስ ከጠንቋዮች ምን ተሻሉ! ሁለተኛ እንደነዚህ ዓይነት ሰባኪዎች ዘንድ መሄድ አልፈልግም" ብላ ወሰነች። ለመሆኑ ያ ሰባኪ ይህችን ሴት እንዲህ ሊላት የቻለው በምን ምክንያት ይሆን? በእርግጥ ሥውር የሆነው ነገር ለእርሱ ተገልጾለት ይሆን? ሴትየዋ የተማረች ስለሆነች ሳይኮለጂው ሳይገባት አልቀረም። እንደዚያ ያለበትን ምክንያት ስትገልጽ፥ "የዛን ዕለት ኸጉርጉር ቀሚስ ለብሼ ስለነበረ፥ ምክንያቱ ያ ሳይሆን አይቀርም" አለች። እግዚአብሔር ስጦታን የሚሰጠው ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ፥ ከጌታ የሸሹትን ወደ እርሱ ለማቅረብ እንጂ፥ የበለጠ እንዲሸሹ ለማድረግ አይደለም። ከላይ የተመለከትነው ሁኔታ ግን፥ ያቺን ሴት የበለጠ አሸሻት እንጂ አላቀረባትም።

"እግዚአብሔር ምስጢርን አይገልጥም" ማለት አይደለም። ይገልጣል፤ ግን በዚህ ዓይነት መንገድ አይደለም። ይህንን

የመሰሉ ቁጥር ስፍር የሌላቸው በየቤተ ክርስቲያኑ፥ በየጸሎት ቤቱ፥ በየሰዎች ቤት በዘመናችን እየታዩ ናቸው። በጣም የሚያሳዝነው የዘመኑ አማኝ እግዚአብሔር ለእርሱ ያለው ዓላማ ምን እንደሆነ ለማወቅ መጽሐፍ ቅዱስን በመመርመር ፈንታ፥ ስጦታው አላቸው ብሎ የሚያምናቸው አማኞች የሚነግሩትን ለመስማት መናፈቁና መጓጓቱ ነው። በዚህ ምክንያት ወደ ቤታቸው ጋብዘው አብረዋቸው እንዲጸልዩ የሚፈልጓቸው ሰዎች ይህን ዓይነቱ ስጦታ አላቸው ብለው የሚያስቧቸውን ሰዎች ብቻ ነው። ከዚህ ሁሉ የገረመኝና ያሳዘነኝ፥ በየዓመቱ ኮንፍራንስ የሚያዘጋጁ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ክርስቲያኖች፥ በየዓመቱ እየመጡ እንዲያስተምሯቸው ሁለት ሰባኪዎችን ብቻ ለምን እንደሚጋብዙ የሰውትን ምክንያት ስሰማ ነው። ይሄ ሁኔታ ያስደነቃቸው አንዳንድ ክርስቲያኖች፥ "ለምንድነው እነ እከሌ ብቻ እንዲሰብኩ በየዓመቱ የሚጋበዙት? እነ እከሌስ ለምን አይጠሩም?" ብለው ጠየቋቸው። ፕሮግራሙን የሚያቀነባብሩት ወንድሞች ለዚህ የሰጡት መልስ "እኛ የፈውስ ስጦታ፥ የመገለጥ ስጦታ የሌላቸውን ሰባኪዎች መጋበዝ አንፈልግም፤ እነ እከሌ ያላቸኋቸው ጥሩ አስተማሪዎች እንደሆኑ እናውቃለን። ግን ከላይ የጠቀስናቸውን ዓይነት ስጦታ ስለ ሌላቸው እነርሱን መጋበዝ አንፈልግም" የሚል መልስ ሰጧቸው። እነዚህ "መሪ ነን" ብለው ራሳቸውን የሚጠሩ ወንድሞች ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ ያላቸው ዕውቀት ይሄው ብቻ መሆኑ ያሳዝናል። ለቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጉት ከላይ የተጠቀሱት ሁለቱ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ብቻ ቢሆኑ ኖሮ፥ እግዚአብሔር ከሃያ የሚበልጡትን ልዩ ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ለቤተ ክርስቲያን ባልሰጠም ነበር። ሌላው የሚያሳዝነው ነገር፥ እነዚህ ስጦታዎች ያላቸው ሰዎች የሚያገኙትን ክብርና እንዲሁም ከሌላው የበለጠ መፈለግን አንዳንድ ወጣት ሰባኪዎች ያዩና፥ ስጦታው ሳይኖራቸው "የዚህና የዚያ ስጦታ አለኝ" በማለት

በየቦታው ችግርና ሁከት የሚፈጥሩ መሆናቸው ነው።

"እውቀትን የመናገር" ስጦታ በእርግጥ ከላይ ያየነውን ዓይነት ነው ወይ? ከላይ ካየነው የተለየ አመለካከት ያላቸው ክፍሎች አሉ። አሁንም ከፔንቲኮስታል አካባቢ ታዋቂነትን ያተረፉ ፒተር ዋግነር "እውቀት መናገር" ስጦታን ሲገልጹ፥ *"...እግዚአብሔር፥ ቤተ ክርስቲያን የምታድግበትንና የምትታነጽበትን ዕውቀት ለአንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አባላት ይሰጣል። ስጦታው ያለው ሰው ዕውቀትን የመሰብሰብ፥ የማከማቸት፥ የመተንተንና ግልጽ የማድረግ ልዩ ችሎታ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ይሰጠዋል"* ይላሉ።

3. እውቀትን የመናገር ስጦታ ምንድነው?

ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ. 12፥8 ላይ *"እውቀትን የመናገር"* ስጦታ ሲል ምን ማለቱ ነው? ከላይ በምሳሌ ያየናቸውን ዓይነት "መገለጥ" ይሆን? "እውቀትን መናገር" *(Word of Knowledge)* በትምህርት ወይንም በምርምር የሚገኘውን ዓይነት እውቀት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። *"...ያ አንዱ መንፈስ እንደ ሚፈቅድ..."* ሲል፥ ዕውቀቱን የሚገልጠው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ እንረዳለን። ስጦታው መንፈሳዊነት ያለው "ጥልቅ ዕውቀት" ነው። "እውቀት የመናገር" ስጦታ፥ የሰውን ሳይሆን የእግዚአብሔርን ጥልቅ የሆነውን ሀሳብ ማወቅ ነው። በዚህ ስጦታ ላይ ያለው ችግር፥ ወይንም ስህተት፥ በአጠቃቀሙ ላይ ነው። *"እውቀትን መናገር"* የሚለውን ስጦታ አንዳንዶች ለመተርጎም የሚፈልጉት በራሳቸው ልምምድ ላይ ብቻ ተመ ሥርተው እንጂ፥ የእግዚአብሔርን ቃል መሠረት አድርገው አይደለም። ይሄ አቋም ያለው ድካም፥ እኛ ያለንን ዓይነት ልምምድ የሚመስል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳለ እንፈልግና፥ ልምምዳችንን እንዲደግፍልን፥ የማይለውን እንዳለ አድርገን

መውሰድ እንጀምራለን። መሆን ያለበት ግን መጀመሪያ ወደ ቃሉ መሄድና፥ ቃሉ የሚለውን በትክክል በመተርጎም ልምምዳችንን በቃሉ አማካኝነት መመዘን ነው።

ሌላው ትልቁ ስህተታችን ያለው፥ መጽሐፍ ቅዱስን አተረጓጎማችን ላይ ነው። ጳውሎስ ስለ *"እውቀትን መናገር"* የተናገረውን ሀሳብ፥ ፊጽሞ ከማይገናኘው ጥቅስ ወይንም መጽሐፍ ጋር በማያያዝ ለመተርጎም በመሞከራችን እንስታለን። ለምሳሌ ጳውሎስ በ1 ቆሮ. 12፥8 ላይ የጠቀሰውን *"እውቀትን መናገር"* የሚለውን ሀሳብ ከዮሐንስ 4፥4-42 ካለው ጥቅስ ጋር እናያይዘዋለን። እዚህ ላይ ኢየሱስ የሳምራዊቷን ሴት ኃጢአት እንዴት እንዳወቀ ይናገራል። ጳውሎስ *"እውቀትን መናገር"* ያለው እንደዚያ ዓይነቱን ነው ብለው ትርጉም የሚሰጡ አሉ። በ1ኛ ቆሮ. 12፥8 ላይ "እውቀትን መናገር" የሚለው ሀሳብ እንዴት እንደተገለጸ በመጠየቅ ፈንታ፥ ልምምዳችንን የሚደግፍልንን ሀሳብ፥ ወይም ለዚያ ሀሳብ እኛ የሰጠነውን ትርጉም የሚደግፍልንን ቃል ሌላ ሥፍራ ሄደን መፈለግ እንጀምራለን። በዚህ ዓይነት ትክክል ያልሆነ ትርጉም በመስጠት፥ ራሳችንና ሌሎችን እናሳስታለን። ታዲያ ጳውሎስ 1ኛ ቆሮንቶስ ላይ "እውቀትን መናገር" ያለው ምንድነው?

መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች ስለሚገልጠው ዕውቀት በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 2 ላይ እናነባለን። ይሄንን ልዩ እውቀት ለአማኞች ብቻ የሚገልጠው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ጳውሎስ ይጽፋል። *"በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአ ብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያው ቅም። እኛ ግን ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ ሳልተቀበልንም። መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊው ነገር ጋር*

አስተያይተን መንፈስ በሚያስተምረን ቃል ይሆን ደግሞ እንናገ ራለን እንጂ የሰው ጥበብ በሚያስተምረን ቃል አይደለም" (1 ቆሮ. 2፥11-13) ይላል። የዓለም ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ስላል ተቀበሉ ይሄን ዓይነቱ መገለጥ የላቸውም። አማኞች ግን አፅ ምሮአቸው በመንፈስ ቅዱስ የተቀደሰ በመሆኑ፥ መንፈሳዊ የሆ ነውን ነገር የመረዳት ችሎታ አላቸውI መንፈስ ቅዱስ በሚሰ ጣቸው ቃልም ሀሳባቸውን መግለጽ ይችላሉ።

ጳውሎስ *"የእግዚአብሔርን ጥልቅ የሆነውን ሀሳብ እን ድናውቅ መንፈስ ቅዱስ በነጻ ተሰጠን"* ሲል ምን ማለቱ ይሆን? ለዚህ ጥያቄ መልስ ማግኘቱ አስፈላጊ የሚሆንበት ዋናው ምክንያት፥ *"እውቀትን የመናገር"* ስጦታ ትክክለኛ ትርጉሙ ምን እንደሆነ እንድናውቅ ስለሚያስችለን ነው። ጳውሎስ *"በጥበብ መናገር"* ስጦታን ለሁለት እንደከፈለው፥ አሁንም *"ዕውቀት መናገርንም"*፥ የሥነ መለኮት እውቀትና (Theological knowledge) ተግባራዊ ዕውቀት (Practical knowledge) ብሎ በሁለት ይከፍለዋል። ጳውሎስ የእግዚአብ ሔር የሆነውን ነገር እንድናውቅበት በነጻ ተሰጠን ሲል፥ የመን ፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታን ማለቱ ነው። የመጀመሪያውና ትልቁ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ በክርስቶስ በኩል ያገኘነው የዘለዓ ለም ሕይወት ነው። ጳውሎስ "የእውቀት መናገር" ሲል ለዓለም እግዚአብሔር ልጁን እንዲሁ እንደሰጠ መናገር መቻል ነው።

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምዕመናን *"...እምነታችሁም በእግ ዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን..."* ያለው (1 ቆሮ. 2፥4) ይህን ዓይነቱ ዕውቀት ከእግዚአብሔር ብቻ እን ደሚገኝ ሲገልጽ ነው። *"ዕውቀት"* የሚለው ቃል *"ጊኖስኮ"* ከሚ ለው የግሪክ ቃል የመጣ ነው። ቀጥታ ትርጉሙም፥ *"ወደ ማወቅ መድረስ፥ ማስታወስ፥ ወይንም ሙሉ በሙሉ መረዳት"* ማለት ነው። ይሄም መረዳት የሚመጣው "በመመልከትና በልምምድ"

ነው። "እውቀትን መናገር" ስጦታ ያለው ሰው የእግዚአብሔርን ቃል በጥልቀት ለመረዳት፥ ለማወቅ ልዩ ጥማት በውስጡ ይሰ ማዋል። ይህ ስጦታ ያለው ሰው ጥሩ ተማሪ ነው። ለመማር፥ ለመመራመር ጉጉት ያለው፥ መማር የማያስለቸው፥ የተማረውን ዕውቀት በተግባር ማዋል ችሎታ ያለው ነው። "እውቀትን መናገር ስጦታ" ያለው ሰው፥ በሰው ከመከበብ ይልቅ፥ ብቻ ውን ሆኖ ማሰብንና መመራመርን ይመርጣል።

"እውቀትን የመናገር" ስጦታ ያላቸው ሰዎች፥ ብዙ ጊዜ ሀሳቡን ከየት እንዳገኙት መግለጽ አይችሉም። ሀሳብ በሚፈል ጉበት ወቅት "ሀሳቡ" ይመጣላቸዋል። ሀሳቡ በበለጠ በውስጣቸው እንዲዳብር ለብቻቸው ሆነው ማሰብን ይመርጣሉ። የእግዚአብ ሔር ዕውቀትና ጥበብ መታየት የሚችለው፥ ለሕዝቦቹ በሚሰ ጠው የዕውቀትና የጥበብ መናገር ስጦታ ነው። ዕውቀትን የመናገር ስጦታ፥ አማኞች ትክክለኛ ውሳኔ እንዲያደርጉ የሚ ረዳቸው ነው። "ዕውቀት" ስንል ምድራዊውን የሚያስታብየውን ዕውቀት ማለታችን አይደለም። ስለ ዓለም ዕውቀት ጳውሎስ ሲናገር፥ *"እውቀት ያስታብያልI ፍቅር ግን ያንጻል። ማንም አንዳች የሚያውቅ ቢመስለው ሊያውቅ እንደሚገባው ገና አላ ወቀምI ማንም ግን እግዚአብሔርን ቢወድ እርሱ በእርሱ ዘንድ የታወቀ ነው"* ይላል (1 ቆሮ. 8፥2-3)። *"የዕውቀት መናገር"* ስጦታ ያለው እግዚአብሔር በዓለም ላይ ስለሚሠራው ሥራ ግልጥ ያደረገበትን "እውነት" በቂ የሆነ መረዳትን ይሰጠ ዋል። በዚህ ጥልቅ መረዳት፥ የዕውቀት መናገር ስጦታ በግልጽ ሲታይ፥ ስጦታው ያለው አማኝ እንዲታበይ የሚያደርገው ፈተና ሊያጋጥመው ይችላል።

ይህ ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን በጣም አስፈላጊ ነው። አስፈላጊ ውሳኔዎችን ለመውሰድ የሚጠይቀውን ድፍረትና ዲሲፕሊን፥ ምእመናኑን ለማነቃቃት ምን ዓይነት ቃል መጠቀም

እንደሚያስፈልግ ለማወቅ "የዕውቀት መናገር" ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን በጣም አስፈላጊ ነው። ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልዕክት ላይ፥ እግዚአብሔር መጀመሪያ ከእስራኤል፥ ቀጥሎ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለው የተቀራረበ ግንኙነት ምን ዓይነት እንደሆነ ያሳያል። የእግዚአብሔር ዕውቀትና ጥበብ ምን ያህል ጥልቅ እንደሆነ የሚታየው መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች በሚሰጠው "በዕውቀትና በጥበብ ስጦታ" እንደሆነ ይገልጻል። *"የእግዚአብሔር ባለጸግነትና ጥበብ ዕውቀትም እንዴት ጥልቅ ነው! ፍርዱ የማይመረመር፥ መንገዱም የማይታወቅ ነው"* ይላል (ሮሜ 11፥33)። "የዕውቀት መናገር" ስጦታ በተለይ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወይንም ሽማግሌዎች በጣም አስፈላጊ ነው። ይሁን እንጂ፥ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምንም ዓይነት ስልጣን የሌላቸው፥ ነገር ግን በቤተሰብ ውስጥ፥ በቤተ ክርስቲያንና እንዲሁም በሕብረተሰቡ ውስጥ ጌታ በሰፊው የሚጠቀምባቸው፥ የእግዚአብሔር ሰዎች "የዕውቀት መናገር" ስጦታ እንዳላቸው በግልጽ የሚታይበት ጊዜ አለ።

ሐዋርያው ጳውሎስ "የዕውቀት መናገር" ስጦታ ሲል፥ ምን ዓይነት "ዕውቀት" ማለቱ ነው? የሥነ መለኮት አዋቂዎች *"ጠልቆ ማወቅ...፥ ማብራራት መቻል..."* *(insight.; illumination)* እንደሆነ ይናገራሉ። ቤተ ክርስቲያን በዚህ ስጦታ የምት ጠቀመው በምን ዓይነት ሁኔታ ይሆን? ቤተ ክርስቲያን የተለ ያየ ችግርና እንቅፋት ሲያጋጥማት፥ ችግሩ ምን እንደሆነ ለማወቅ፥ ይሄ ስጦታ ያስፈልጋታል። ቤተ ክርስቲያንን በሚ መለከት ጉዳይ ውይይት ለማካሄድ፥ ውሳኔ ለመስጠት፥ የተወ ሰደውን እርምጃ በተግባር ላይ ለማዋል፥ መቀጣት ያለባቸውን ለመቅጣት፥ ምክር ለሚያስፈልጋቸው ምክር ለመስጠት እንዲ ቻል፥ "የእውቀት መናገር" ስጦታ ያላቸው አማኞች መኖር አስፈላጊ ነው። "የዕውቀት መናገር" ስጦታን ለመረዳት መመ ሪያ የሚሆነን 1ኛ ቆሮንቶስ 2፥11-16 ላይ የተጠቀሰው ሀሳብ ነው። በነዚህ ጥቅሶች ውስጥ፥ ሰው መንፈሳዊ ስለሆነው ነገር የሚኖረውን የመረዳት ወይንም የማወቅ ደረጃዎች ይናገራል።

"ስለ ሰው የሆነ እንደሆነ፥ ከገዛ ራሱ መንፈስ በቀር በእርሱ ያለውን አሳብ የሚያውቅ ሌላ ማንም የለምI እንዲሁም ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር የእግዚአብሔርን አሳብ የሚያውቅ ማንም የለም። እኛ የዚህን ዓለም መንፈስ አልተቀበልንምI እኛ የተቀበልነው እግዚአብሔር የሰጠንን ሁሉን ለማወቅ የሚ ያስችለንን የእግዚአብሔርን መንፈስ ነው" (1 ቆሮ. 2፥11-12)።

4. "እውቀትን የመናገር" ስጦታን፥ "ከትንቢት ስጦታ" ጋር እናማታው ይሆን?

"እውቀትን መናገር" በሌላ ሰው ሕይወት ውስጥ ያለ ውን "ድብቅ ነገር" ማወቅና መናገር ነው" ብለን ትርጉም መስ ጠት እንችላለን? "ነው" ካልንስ፥ ይህንን ሀሳብ የሚደግፍ የመ ጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እናገኛለን? የተደበቀውን የሚገልጸው "ትን ቢት የመናገር" ስጦታ እንጂ፥ *"እውቀትን የመናገር"* ስጦታ እንዳልሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል። "ትንቢት" በማ ያምኑት ሰዎች መካከል ሲነገር የሚያመጣውን ውጤት ጳውሎስ ሲገልጽ እንዲህ ይላል። *"ሁሉ ትንቢት ቢናገሩ ግን የማያምን ወይም ያልተማረ ሰው ቢገባ በሁሉ ይወቀሳልI በሁሉም ይመ ረመራልI በልቡም የተሰወረ ይገለጣልI እንዲሁም እግዚአብ ሔር በእውነት በመካከላቸው ነውI ብሎ እየተናገረ በፊቱ ወድቆ ለእግዚአብሔር ይሰግዳል"* (1 ቆሮ. 14፥24-25)። በዚህ ጥቅስ መሠረት "በልብ የተሰወረ ይገለጣል" የሚለው "የትንቢ ትን ስጦታ" ነው እንጂ "እውቀትን የመናገር" ስጦታን አይ ደለም። ኢየሱስ ያቺን ሳምራዊት ሴት ሲያነጋግር፥ *"አምስት ባሎች ነበሩሽና አሁን ከአንቺ ጋር ያለው ባልሽ አይደለም"* (የዮሐ. 4፥18) ብሎ ምስጢሯን ገልጦ ሲናገር በመደነቅ "ጌታ ሆይ! አንተ እውቀትን መናገር" ስጦታ አለህ" አላለችውም። ነገር ግን *"ጌታ ሆይ! አንተ ነቢይ እንደሆንህ አያለሁ"* (የዮሐ.

4፥19) ነው ያለችው። እርግጥ ነው ብዙ ጊዜ አንዱ ስጦታ ከሌላው ስጦታ ጋር እንደሚያያዘው *(overlap)* የትንቢት ስጦታም ከእውቀት መናገር ስጦታ ጋር ሊያያዝ ይችላል።

☆ ☆ ☆ ☆



በልዩ ልዩ ዓይነት ልሳን የመናገርና በልሳኖች የተነገረውን የመተርጎም ስጦታ

"...ለአንዱ በአዲስ ቋንቋዎች የመናገር ችሎታን ይሰጠዋል፤ ለሌላው ደግሞ ባልተለመዱ ቋንቋዎች የተነገረውን የመተርጎም ችሎታን ይሰጠዋል።"
(1ኛ ቆሮ. 12፥10)

1. የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ

በአሁኑ ዘመን በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መካከል አከራካሪ *(controversial)* መንፈሳዊ ልምምድ ቢኖር፥ *"በልዩ ልዩ ቋንቋ መናገር"* ነው። ሀሳቡን በመደገፍም ሆነ በመቃወም ብዙ መጽሐፍት ተጽፈዋል። በቋንቋ መናገር በሐዋርያት ዘመን እንጂ፥ በአሁን ዘመን አብቅቷል በማለት አጥብቀው ሀሳቡን የሚቃወሙ አሉ። ከነዚህ መካከል በሬዲዮ የመጽሐፍ

ቅዱስ አስተማሪነታቸውና በጻፏቸው አያሌ መጽሐፍት አሜሪካ ውስጥ በጣም የታወቁት ጆን ማካርተር ይገኙበታል። በልዩ ልዩ ልሣን ስለ መናገር ስጦታ ያላቸውን ብርቱ ተቃውሞ ሲገ ልጹ፥ *"በቋንቋ ስለ መናገር የሚሰነዘሩትን አንዳንድ ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ ሰባት ዓመት የፈጀ ሰፊ ጥናት ካደረግሁ በኋላ፥ እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ አማኞችና (charismatics) እንዲሁም ከእንቅስቃሴው ውጪ የሆኑ አማኞች የሚሰጡትን ሀሳብ ከመረመርኩ በኋላ፥ በልዩ ልዩ ልሣን የመናገር ስጦታ በሐዋርያት ዘመን ያበቃ ወይንም ያከተመ እንደሆነ በማያጠራጥር ሁኔታ ተረድቻለሁ"* አሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የታወቁት የቤተ ክርስቲያን መጋቢና ጸሐፊ፥ ሌስሊ ቢ. ፍላይን የጆን ማካርተርን ሀሳብ በመቃወም *"በአሁኑ ዘመን በቋንቋ መናገር በአጠቃላይ ሀሰት (ስህተት) ነው ማለትና ትልቅ ድፍረትና አደገኛ አስተያየት ነው። መንፈስ ቅዱስ ለአገልጋዮቹ የፈለገውን ስጦታ መስጠት የሚችል መሆኑን መካድ ይሆናል"* አሉ።

የመንፈስ ቅዱስ ሙላትና እንቅስቃሴው በዓለም ውስጥ በተለይ በሃያኛው ክፍለ ዘመን ሦስት የተለያየ የዕድገት ደረጃ ዎች ውስጥ እንዳለፈ የሃይማኖት ታሪክ ገምጋሚዎች ይናገራሉ።

(1) የመጀመሪያው ደረጃ፥ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ካሊፎርኒያ ውስጥ በ1906 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) ለመጀመሪያ ጊዜ የታወቀበት ዘመን ነው። ለሃምሣ ዓመት ይዚ እምነት ይታይ የነበረው በአንድ ትንሽ "ቤተ እምነት" ይኸውም *"የፔንቲከስታል ቤተ እምነት"* ውስጥ ብቻ እንደ ነበር ይታወቃል።

(2) በሌሎች *"ቤተ እምነቶች"* *(denominations)* በብዛት ተቀባይነት ያገኘው በ1960 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) ሲሆን፥ ይዚ ሁለተኛው የዕድገት ደረጃው ነው። ይሁን እንጂ፥ በዚህ ወቅት ይህንን እንቅስቃሴ የተቀበሉት አብዛኛዎቹ በኑሮ

ደረጃቸው ዝቅተኛ ሥፍራ የነበራቸው ሰዎች ብቻ እንደ ነበሩ ታሪክ ጸሀፊዎች ይናገራሉ።

(3) ሦስተኛው ደረጃ በ1967 ዓ.ም. በሮማ ካቶሊኮች መካከል ተቀባይነት ያገኘበት ወቅት ነው። በ1973 ዓ.ም. በሰባተኛው *የፔንቴከስታል ዓመታዊ ኮንፍራንስ* ላይ 22 ሺ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ልምምድ ያላቸው ሰዎች *ኖተር ዳም* ላይ ታላቅ ስብሰባ እንዳደረጉና በዚሁ ዘመን በብዙ ሺ የሚቆ ጠሩ ካቶሊኮች የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ልምምድ እንዳገኙ የታወቀበት ጊዜ ነው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እንቅስቃሴው በጣም እያደገ መጣ። በዘመናችን በተለያዩ "ቤተ እምነቶች" (ዲኖሚኔሽን) ውስጥ ያሉ የቤተ ክርስቲያን አባላት ብዙ ዎች በግልም ሆነ፥ ከጥቂት ሰዎች ጋር ሆነው በቋንቋ መናገርን መለማመድ እንደጀመሩ ይታወቃል። ይሁን እንጂ፥ በዚህ ልምምድ ምክንያት ብዙ አብያተ ክርስቲ ያናት እርስ በርሳቸው እንደ ተከፋፈሉ የታወቀ ነው።

2. በልዩ ልዩ ዓይነት ልሣን የመናገር ስጦታ ምንድነው?

"በልዩ ልዩ ዓይነት ልሣን የመናገር" ስጦታ፥ "ገላጭ" *(revelatory)* ተብለው ከሚጠሩት ስጦታዎች መካከል አንደኛው ነው። እነዚህ ስጦታዎች "ገላጭ" የተባሉበት ምክንያት እግዚ አብሔር ለሕዝቡ ያለውን አዲስ ሀሳብ፥ ስጦታው ባላቸው ሰዎች በኩል የሚገልጽ በመሆኑ ነው። እነዚህ "ገላጭ" ተብለው የሚ ጠሩት ስጦታዎች ሦስት ሲሆኑ፥ እነርሱም *ትንቢት መናገር፥ በልዩ ልዩ ዓይነት ልሣን መናገርና በልሳን የተነገረውን መተ ርጎም* ናቸው። *"መገለጥ"* ወይንም *"መግለጫ"* ስንል፥ እግዚአ ብሔር በቃሉ ውስጥ የገለጸውን እውነት የሚቃረን ወይንም ከቃሉ ውጪ የሆነ ሀሳብ ይገልጻል ማለት አይደለም። የእግዚ

አብሔር ቃል (መጽሐፍ ቅዱስ) ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተሞል ተው የጻፉት ሲሆን፥ "ከስህተት ፍጹም ነጻ የሆነና" *(inerant)* እንዲሁም ምትክ የሌለው መጽሐፍ ነው። "የእግዚአብሔር ቃል" እውነተኛ የትንቢት ስጦታ ባላቸው ሰዎች በሚነገር የት ንቢት ቃል የሚተካ ወይንም የሚለወጥ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ "ከስህተት ሁሉ ነጻ ነው" እንደምንለው ያህል፥ ስጦታው ኖሮአቸው ከእግዚአብሔር የሚተላለፈውን መልዕክት የሚያስተ ላልፉ ሰዎች ግን ከስህተት ሁሉ ነጻ አይደሉም። ሊሳሳቱ ይች ላሉ። ለዚህ ነው በትንቢት፥ በልዩ ልዩ ዓይነት ልሣን የሚተላ ለፉ መልዕክቶች (መገለጦች) በእግዚአብሔር ቃል መመርመርና መፈተን ያለባቸው። ትንቢት እውነተኛነቱ የሚታወቀው የእግ ዚአብሔርን ቃል የማይቃረን መሆን አለመሆኑንን በመመልከት ነው። ለምሳሌ፥ "የትንቢት ስጦታ አለኝ" በማለት አንድ አማኝ ተነስቶ "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥ የአሁኗን ሚስትህን ያገባሃት ያለእኔ ፈቃድ ስለሆነ፥ እርሷን ፈትተህ እኔ የፈቀድኩልህን እከሊትን አግባ" ብሎ ቢተነብይ፥ ትንቢቱ የእግዚአብሔርን ቃል ስለሚቃረን ትክክል እንዳልሆነ ግልጽ ነው። እግዚአብሔር በቃሉ *"...ፍቺን እጠላለሁ..."* እንዳለ እናውቃለን። እግዚአብሔር ምን ጊዜም ቢሆን ራሱን ስለማይ ቃረን፥ ከላይ የሰማነው ትንቢት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር አብሮ ስለማይሄድ ስህተት እንደሆነ ግልጽ ነው።

"የመንፈስ መለየት ስጦታ" ያላቸው አማኞች በትን ቢትም ሆነ በልሣን የሚተላለፈው መልዕክት ስህተት መሆኑንና አለመሆኑን መለየት ስለሚችሉ፥ ቤተ ክርስቲያንን ከስህተት ለመጠበቅ፥ በስጦታቸው እንዲጠቀሙበት ማደፋፈር ያስፈል ጋል። ስጦታው የሌለን ሰዎች አልፎ አልፎ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚተላለፈው አንዳንድ መልዕክት ልክ መሆን አለመሆ ኑን መለየት ቢያስቸግረንም፥ አብዛኛውን መልዕክት ግን መለየት ይህን ያህል አያስቸግረንም። አስቸጋሪ ሲሆንብን፥ *"የመንፈስ*

መለየት ስጦታ" ያላቸው አማኞች ሊረዱን ይገባል። ሌላው የሚያሳዝነው ነገር፥ አንዳንድ አማኞች "በልዩ ልዩ ዓይነት ልሣን መናገር" ስጦታ ስላለን፥ መጽሐፍ ቅዱስ አያስፈልገንም በማለት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን ችላ ማለታቸው ነው። የመ ንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በእኛ ዘመን ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ ለአማኞች የሚሰጡ ቢሆኑም፥ አማኞች ያለአግባብ ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ መዘንጋት የለብንም። የእግዚአብሔርን ቃል ለመ ሰረዝና ለመበረዝ የሚሞክር ማንኛውም ኃይል ምንጩ ከሥጋ ወይንም ከሰይጣን መሆኑን መረዳት ይገባናል።

ፒተር ዎግነር ካሊፎርኒያ ውስጥ ያለው *"የፉለር ቲዮሎጂካል ሲሚናሪ"* ፕሮፌሰር ሲሆኑ፥ በፔንቴኮስታል "ቤተ እምነት" (ዲኖሚኔሽን) ውስጥ ተቀባይነት ያላቸው ሰው ናቸው። እኚህን ሰው ከአንባቢዎቼ ጋር በቅድሚያ ለማስተዋወቅ የፈለግ ሁበት ዋናው ምክንያት፥ *ፒተር ዎግነር* "የፔንቲኮስታልን እም ነት" የሚደግፉ አስተማሪ መሆናቸውን ባለማወቅ፥ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ተቃዋሚ መስለውን፥ የሚሰጡትን መልካም አስተያየትና ትምህርት ለመቀበል እንዳንቸገር በማለት ነው። እኚህ ሰው *"በቋንቋ መናገር"* ስጦታ በዘመናችን ለቤተ ክርስ ቲያን እንደሚሰጥ ያምናሉ። ይህ ስጦታ ምን እንደሆነ ሲገልጹ፥ *"በቋንቋ የመናገር ስጦታ፥ እግዚአብሔር በክርስቶስ አካል ውስጥ ላሉ አንዳንድ አባላት የሚሰጠው፥ ከዚህ በፊት ተምረው ባላወቁት ቋንቋ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር መቻልና፥ እንዲሁም ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን መልዕክት፥ በልዩ ቋንቋ በመናገር ለሕዝቡ ማስተላለፍ መቻል ማለት ነው።"* አሉ።

ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሁሉ በአሁኑ ዘመን አማኞች በብዛት የሚጠቀሙበት ስጦታ ቢኖር፥ *"የግል የጸሎት ቋንቋ" (private tongues)* ነው። በዚህ ስጦታ የሚጠቀሙ አንዳንድ

ሰዎች፥ ያለምንም ችግር ሲጠቀሙበት በማየታቸው፥ አማኝ ሁሉ ሊጠቀምበት ወይንም ሥጦታው ሊኖረው ይቻላል ብለው የሚያምኑ አሉ። ይህን የሚሉበት ምክንያት ምን እንደ ሆነ *ፒተር ዋግነር* ሲገልጹ፥ ጳውሎስ *"ሁላችሁም በአዲስ ቋንቋ ብትናገሩ በመደድሁ ነበር"* የሚለውን ቃል በመያዝ ነው (1 ቆሮ. 14፥5) ይላሉ። ይህን የጳውሎስን አባባል በትክክል ባለ መረዳት፥ "በቋንቋ መናገርን" ያለአግባብ ሲጠቀሙበት እናያለን። ጳውሎስ "ሁላችሁም በአዲስ ቋንቋ ብትናገሩ በወደድሁ ነበር" የሚለውን ጥቅስ በመያዝ አንዳንድ ቅንና እውነተኞች ክርስቲያኖች፥ በቋንቋ ለመናገር ብዙ ጊዜ እየፈለጉ፥ መናገር ባለመቻላቸው ስጦታውን ያልሰጣቸው እግዚአብሔር የማይወዳቸው መስሎ ስለሚሰማቸው በጣም ያዝናሉ። በመንፈስ ቅዱስም ያልተሞሉ መስሎ ይሰማቸዋል። ፒተር ዋግነር *"እንደነዚህ ዓይነት ቅንና እውነተኞች ክርስቲያኖች፥ በቋንቋ ስላልተናገሩ ብቻ በመንፈስ ቅዱስ አልተሞሉም ማለት ትክክልና አግባብ ያለው አባባል አይደለም"* ይላሉ።

"በልሳን የመናገር" ስጦታ ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ አንድ ዓይነት መልስ ለማግኘት አንችልም። የተለያዩ የስነ-መለኮት አዋቂዎች የተለያዩ መልስ አላቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቋንቋ ስጦታ የተናገረውን፥ ዛሬ በዘመናችን አንዳንድ አማኞች ሲለ ማመዱት ከምንሰማው የቋንቋ ስጦታ ጋር ለማወዳደር (ለማመሳከር)፥ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያየ ሥፍራ የተጠቀሱትን ሀሳቦች፥ እያንዳንዳቸውን በተናጥል መመልከት ያስፈልጋል። እዚህ ላይ ሁለት ዓይነት ሀሳብ ያላቸው ሰዎች አሉ።

1ኛ) *"በቋንቋ የመናገር"* ስጦታ፥ አንዱን አማኝ ከዚህ በፊት ባልተማረውና በማያውቀው ቋንቋ እንዲናገር የሚያስችል ስጦታ ነው ሲሉ፥

2ኛ) *"በቋንቋ የመናገር"* ስጦታ የሰዋሰውን ሕግ የተከተለ ቋንቋ ሳይሆን፥ *"የፍንደቃ ንግግር"* *(ecstatic utterances)* ነው የሚሉ ናቸው። በሐዋ. 2፥1-42፥ 10፥1-48፥ 19፥1-7 እንዲሁም በ1ኛ ቆሮ. 12-14 ላይ የተጠቀሰው "በቋንቋ መናገር" የፍንደቃ ንግግር ሳይሆን፥ ከዚህ በፊት በማያውቁትና ባልተማሩት ቋንቋ መናገር እንደሆነ መግንዘብ እንችላለን።

ጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ሲዘረዝር፥ *"...ለአንዱም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር ... "* ይሰጠዋል (1 ቆሮ. 12፥10) ሲል ምን ማለቱ ነው? ከላይ ጳውሎስ የተናገረውን ጥቅስ ስንመረምር ሦስት ፍሬ ሀሳቦችን እናያለን።

1ኛ) እንደ ሌሎቹ ስጦታዎች ሁሉ፥ *"በልዩ ዓይነት ልሳን መናገርም"* ከሰብአዊ ባሕርይ ውጪ *(supernatural)* የሆነ፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ መሆኑን እናያለን። *ቲሙቲ ፔን* የተባለው ታዋቂ የሆነ ጸሀፊ *"በልሳን መናገር"* ምን እንደ ሆነ ሲገልጽ፥ "በልዩ ልሳን የመናገር ስጦታ ተአምራዊ ነው። አማኝ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ ከዚህ በፊት ተምሮ በማያውቀው ቋንቋ የሚጠቀምበት በመሆኑ፥ በተአምር የተሞላ መሆን አለበት" አለ።

2ኛ) ስጦታው ቋንቋን እንደሚመለከት እናያለን። ጳውሎስ ይህን ስጦታ በግሪክ ቋንቋ "ግላሳ" ሲለው፥ ትርጉሙ ልሳን (ምላስ) ማለት ነው። ምላስ ሲል "የሰውነት ክፍላችን" የሆነውን ማለቱ ሳይሆን፥ ከዚህ በፊት ሳንማር፥ መንፈስ ቅዱስ እንድንናገርበት የሚሰጠን ቋንቋ ማለቱ ነው።

3ኛ) ስጦታው ያላቸው ሰዎች መንፈስ ቅዱስ እንዲናገሩበት የሚሰጣቸው ቋንቋ አንድ ዓይነት ሳይሆን፥ ልዩ ልዩ

ዓይነት ነው። ይህም ማለት ስጦታው ያላቸው ሰዎች ሁሉም የሚናገሩበት ቋንቋ አንድ ዓይነት እንዳልሆነ እንረዳለን።

2. የተለያየ "የቋንቋ ንግግር" ይኖር ይሆን?

"በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር። ከሰማይም በታች ካሉ ሕዝብ ሁሉ በጸሎት የተገ አይሁድ በኢየሩሳሌም ይኖሩ ነበርI ይህም ድምፅ በሆነ ጊዜ ሕዝብ ሁሉ ተሰበሰቡI እያንዳንዱም በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ ይሰማ ስለ ነበር፥ የሚሉትን አጡ። ተገርመውም ተደንቀውም እንዲህ አሉI እነሆ እነዚህ የሚናገሩት ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? እኛም እያንዳንዳችን የተወለድንበትን የገዛ ቋንቋችንን እንዴት እንሰማለን? ..." (የሐዋ. 2፥4-8)። እዚህ ላይ ሉቃስ አማኞች ከዚህ በፊት ተምረው በማያውቁት ቋንቋ መናገር እንደቻሉ ይገልጻል። ለመጀመሪያ ጊዜ የባለ ሃምሳን በዓል ለማክበር ከዓለም ዙሪያ የመጡ አይሁዳውያን በተሰበሰቡበት ወቅት 120 የሚሆኑ የክርስቶስ ተከታዮች የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ በተለያየ ቋንቋ እንደተናገሩ እናውቃለን። እዚህ ላይ ልብ ማለት የሚገባን ነገር ቢኖር፥ ሰሚዎቹ የማያምኑ ሆነው ድንገት፥ ጆሮአቸው እንዲሰሙ ስለተከፈተላቸው፥ ወይንም ሰማያዊ የሆነ ኃይል ደቀ መዛሙርቱ ይናገሩት የነበረውን ቋንቋ እንደተረጎመ ነው። ስለዚህ በሐዋ. ሥራ 2፥8 መሠረት ከሰብአዊ ባሕርይ ውጪ በሆነ ኃይል አማኞች ባልተማሩትና ከዚህ በፊት በማያውቁት ቋንቋ የመናገር ችሎታ እንደተሰጣቸው እናያለን።

ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 14፥2 *"በልሳን የሚናገርስ ለእግዚአብሔር እንጂ፥ ለሰው አይናገርምና፥ የሚያስተውለው የለምና..."* ሲል፥ በሐዋርያት ሥራ ላይ ከተገለጸው "በልሳን መናገር" የተለየ ሌላ እንዳለ እናያለን። ተርጓሚ ከሌለ አዳማጩ

ሊረዳው እንደማይችል ይገልጻል። የመጀመሪያው "በልሳን መናገር" ተርጓሚ አያስፈልገውምI ተናጋሪዎቹ ከዚህ በፊት ቋንቋውን ተምረው ባያውቁም፥ ሌሎች መስማት የሚችሉትን ቋንቋ መናገር ይችላሉ። ጳውሎስ *"እንግዲያስ በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው እንጂ፥ ለሚያምኑ አይደለም..."* *(1 ቆሮ. 14፥22)* ይላል። በሐዋ. ሥራ ምዕራፍ ሁለት ላይ 120 የሆኑ ሰዎች በልሳን ሲናገሩ፥ ከልዩ ልዩ አገር የመጡ የማያምኑ አይሁዳውያን፥ በራሳቸው ቋንቋ የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ይሰሙ እንደነበረ እናውቃለን። እነዚህን የተለያዩ ጥቅሶች ስናነብ "በቋንቋ መናገር" የተለያየ እንደሆነ እናያለን። "በቋንቋ የመናገርን ስጦታ" *"የግልና"* *(private)* *"የማኅበር"* *(public)* ተብሎ በሁለት ክፍል ይከፈላል።

(1) የግል የሆነ የጸሎት ቋንቋ

"የግል" የሆነ የጸሎት ቋንቋ *(private)* ብለው የሚጠሩት፥ አማኙ በግል የጸሎት ጊዜው ብቻ የሚጠቀምበት፥ *"የጸሎት ቋንቋው"* በመሆኑ ነው። ይህን ዓይነቱ ስጦታ አማኝ ራሱን ያንጽበታል። ጳውሎስ *"በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል..."* ይላል (1 ቆሮ. 14፥4)። ይህን ዓይነቱ ቋንቋ የትርጉም ስጦታ አያስፈልገውም። ይሄን ሀሳብ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚደግፈው ለማረጋገጥ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የጻፈላቸውን መልዕክት መመልከት ይጠቅማል። *"በአዲስ ቋንቋ የሚናገር ለእግዚአ ብሔር እንጂ፥ ለሰው አይናገርምI ምክንያቱም ምስጢር የሆነውን ነገር በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስለሚናገር የሚናገረውን ቃል የሚያውቀው የለም"* ይላል (1 ቆሮ. 14፥2)። እንዲሁም በ1ኛ ቆሮ. 14፥28 ላይ *"የሚተረጉም ሰው ከሌለ ግን በአዲስ ቋንቋ የሚናገሩት በስብሰባ ላይ ዝም ይበሉI ለራሳቸውና ለእ ግዚአብሔር ብቻ ይናገሩ"* ይላል። ሮበርት ተትል የተባሉት

ሌላው የቶለር ቲዮሎጂካል ሴሚናሪ ፕሮፌሰርና፥ የዩናይትድ ሜተዲስት ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሆኑት ሰው ስለ *"ጸሎት ቋንቋቸው"* ሲናገሩ እንዲህ አሉ፥ *"አንዳንድ ጊዜ በግል የጸሎት ጊዜዬ፥ ከውስጤ የሚሰማኝን ነገር ለመግለጽ የምቸገርበት ጊዜ አለ፥ በዚህን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በውስጤ እኔ ከዚህ በፊት ተምሬ በማላውቀው ቋንቋ እንድጸልይ ያደርጋል። ቋንቋ መማር ምን ያህል ከባድ እንደ ሆነ አውቃለሁ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋዎችን (ግሪክና እብራይስጥ) ለማወቅና ለመረዳት በየቀኑ የማደርገውን ጥረትና ትግል አውቃለሁ። ...የጸሎት ቋንቋዬ ልክ እንደ ሌላው ቋንቋ ነጠላ ሠረዝ፥ አራት ነጥብና ቃለ አጋኖ እንዳለበት አውቃለሁ። አስደናቂ የሆነ ስጦታ ነው"* አሉ።

"በልሳን የሚናገርስ ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርምና፤ የሚያስተውለው የለምና በመንፈስ ግን ምስጢርን ይናገራል..." (1 ቆሮ. 14፥2) ይላል። ይህን ዓይነቱ ቋንቋ የሚያመለክተው ወደ እግዚአብሔር እንጂ፥ ወደ ሰው እንዳ ልሆነ እናያለን። አማኝ በጸሎቱ ወቅት ለእግዚአብሔር የሚያ ቀርበውን ምስጋናና አድናቆት ከልቡ አውጥቶ የሚገልጽበት መንገድ ነው። የአድናቆትና የምስጋና ድምጽ እንዲያሰማ የሚ ያደርገው ወይንም የሚያስችለው መንፈስ ቅዱስ እንጂ፥ በሰው ፈቃድ የሚደረግ አይደለም። ይህ ቋንቋ ለሚናገረው ሰው ትር ጉሙ ምን እንደሆነ አይታወቅም። "በልዩ ልዩ ልሳን" ስለ መናገር ልናውቃቸው የሚገቡን አንዳንድ እውነቶች አሉ። ይኸውም፥

1.1. በቋንቋ የሚናገሩ፥ በቋንቋ ከማይናገሩት ሌሎች ክር ስቲያኖች የበለጠ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የበሰሉ እን ዳልሆኑ፥ ወይንም ለእግዚአብሔር ከሌሎች የበለጠ ቅርብ አለመሆናቸውን ማወቅና መቀበል ያስፈልጋቸዋል።

1.2. በቋንቋ መናገር የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ስለሆነ፥ በትም ህርት፥ በልምምድ፥ ወይንም አንዳንድ ዘዴ በመጠቀም የሚገኝ እንዳልሆነ መረዳት ያስፈልጋል። *"መንፈስ ቅዱ ስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል"* (1 ቆሮ. 12፥7) ሲል፥ "በልዩ ዓይነት ልሳን መንገርንም" ያጠ ቃልላል። ትንቢት መናገርን ስጦታው ሳይኖረን፥ በመ ለማመድ እንደማናገኘው ሁሉ፥ በልዩ ዓይነት ልሳን መናገርንም በልምምድ ማግኘት አንችልም።

1.3. በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር ስጦታ ያላቸው፥ የሌላቸ ውን አማኞች "ስጦታው እንዲኖራቸው" ማስጨነቅ አይ ገባቸውም።

1.4. ስጦታውን በተግባር ለማዋል በ1ኛ ቆሮንቶስ 14 ላይ የተጠቀሱትን እውነቶችንና ሥርዓቶች ማወቅና መከተል ያስፈልጋል።

- ስጦታው ለማነጽ መሆን አለበት (14፥26)
- ከሦስት ሰዎች በላይ መናገር የለባቸውም (14፥ 27)
- በማህበር የሚነገረው ቋንቋ፥ ተርጓሚ ከሌለ አስፈላጊ አይደለም (14፥27-28)
- በቋንቋ ተናጋሪዎቹ ከሥርዓት ውጪ እንዳይሆኑ መጠንቀቅ ያስፈልጋል (14፥33፥40)።
- ስጦታውን ያለአግባብ በሚጠቀሙ አንዳንድ ሰዎች ምክንያት በአጠቃላይ በቋንቋ መናገርን መንቀፍ፥ መራራ መሆንና መታገስ ወይንም መቀባበል አለመ ቻል ትልቅ ስህተት ነው።
- መጽሐፍ ቅዱስ "በቋንቋ ስለመናገር" የሚናገረውን ክፍል በጥንቃቄ ማጥናትና መረዳት ተገቢ ነው።

➡ ስጦታው ያላቸው አማኞች ያለአግባብ ቢጠቀሙ በት እንኳን በፍቅር መያዝ እንጂ፥ ስጦታው በቤተ ክርስቲያን እንዳይታይ ማድረግ ትክክል አይደለም። ጳውሎስ *"በልሳኖች ከመናገርም አትከልክሉ ነገር ግን ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን"* በማለት ይመክረናል (1 ቆሮ. 14፥40)።

(2) ትንቢታዊ የሆነ፥ ወይንም የማኅበር ቋንቋ

"በልሳን የሚናገር ቢኖር ሁለት ወይም ቢበዛ ሦስት ሆነው በተራቸው ይናገሩ፥ አንዱም ይተርጕም፤ የሚተረጕም ባይኖር ግን በማኅበር መካከል ዝም ይበልና ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር..." (1 ቆሮ. 14፥27-28) ይላል። ይህን ዓይነቱ ቋንቋ ወደ ላይ ሳይሆን፥ ወደ ጎን፥ ማለትም የሚያተኩረው ወደ ሰው እንጂ ወደ እግዚአብሔር እንዳልሆነ እንገነዘባለን። መንፈስ ቅዱስ ለሕዝቡ እንዲተላለፍ የሚፈልገው መልዕክት ሲኖር በልሳን የመናገር ስጦታ ያለው ሰው ተናግሮ፥ የመተር ጎም ስጦታ ካለው ራሱ እንዲተረጉም፥ ከሌለው ግን ሌላ ስጦ ታው ያለው ሰው እንዲተረጉም ያስፈልጋል። በልዩ ልሳን የተነገረው መልእክት ከተተረጎመ፥ ማሕበሩ ይታነጽበታል። የክርስቶስ ሀሳብ ለቤተ ክርስቲያኑ ምን እንደሆነ በመግለጽ ይመክራል፥ ያንጻል፥ እንዲሁም ያጽናናል።

"የማኅበር ቋንቋ" (public tongues) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በማኅበር ጸሎት ጊዜ የሚነገር ነው። ጳውሎስ *"በአዲስ ቋንቋ የሚናገሩ ቢኖሩ ሁለት ወይም ቢበዛ ሦስት ሆነው በየተራ ይናገሩ፤ እነርሱ የሚናገሩትንም ሌላ ሰው ይተርጕም"* ይላል (1 ቆሮ. 14፥27)። ይህ "በልዩ ቋንቋ የመናገር" ስጦታ ባይኖር ኖሮ ጳውሎስ ከላይ እንዳየነው በቋንቋ ስለመናገር ባልገለጸም ነበር። *"በልሳን መናገር"* እውነተኛ ቋንቋ አይደለም

የሚሉ አሉ። አንዳንድ የቋንቋ ኤክስፐርቶች፥ ስጦታው አለን የሚሉትን አንዳንድ አማኞችን በቋንቋ ሲናገሩ በቴፕ ቀርጸው ከመረመሩ በኋላ፥ "ድምጽ (ጩኸት) ብቻ እንጂ፥ ትክክለኛ የቋንቋነት ተቋም የለውም" ይላሉ። ፒተር ዎግነር፥ የቋንቋ ኤክስፐርቶች የሰጡትን አስተያየት ሲቃወሙ፥ "ይህን ያሉበት ምክንያት ምናልባት የሁሉንም የቋንቋ ንግግር በቴፕ ቀድተው ስላላዳመጡ፥ እንዳጋጣሚ የቀዱት የልሳን ንግግር፥ ስጦታው የሌላቸው ሰዎች ዝም ብለው ያሰሙት ድምጽ ሊሆን ይችላል" አሉ።

3. በቋንቋ መናገራችን ከሁሉም የተሻልን ክርስቲያኖች ያደርገን ይሆን?

ጳውሎስ *"ሁላችሁ በልሳኖች ልትናገሩ እወድ ነበር"* (1 ቆሮ. 14፥5) ሲል፥ እርግጥ ነው በግል የአምልኮትና የጸሎት ጊዜያችን ከእግዚአብሔር ጋር የምንገናኝበት ልዩ ቋንቋ መቀበል ትልቅ ነገር መሆኑን ያሳየናል። ይሁን እንጂ፥ ከሌሎች ክርስቲያኖች የተሻልን መሆናችንን አይገልጽም። ጳውሎስ ይህን ስጦታ በአግባቡ መጠቀም ባለመቻል ሊደርሱ የሚችሉትን አንዳንድ ችግሮች ይገልጻል።

3.1. አንዳንዶች በስጦታው ሊኮሩበት ይችላሉ

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው የመጀመሪያው ደብዳቤ ላይ ከምዕራፍ 12 እስከ 14 ያለውን ብናነብ፥ የቆሮን ቶስ ምዕመናን በቋንቋ በመናገራቸው ብቻ ከሁሉ የተሻሉ ክርስቲያኖች እንደሆኑ መስሎ ይሰማቸው እንደነበረ እናውቃ ለን። በቋንቋ የሚናገሩት "ብርቱ ክርስቲያኖች" በቋንቋ የማይናገሩት ደግሞ "ደካማ ክርስቲያኖች" የሆኑ መስሎ

ይሰማቸው ነበር። ይህንን በመገንዘብ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ሲዘረዝር፥ "በቋንቋ መናገርና መተርጎምን" ከሌሎቹ ስጦታዎች ሁሉ የበለጠ እንዳልሆነ ለማሳየት ይሞክራል።

3.2. በማያምኑት ሰዎች ዘንድ መቀለጃ ሊሆን ይችላል

"ማኅበር ሁሉ አብረው ቢሰበሰቡ፥ ሁሉም በልሳኖች ቢናገሩ፥ ያልተማሩ፥ ወይንም የማያምኑ ሰዎች ቢገቡ፥ አብደዋል አይሉምን..." (1 ቆሮ. 14፥23) ይላል። የማያምኑ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደው በዚያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አማኞች ሁሉም በአንድ ጊዜ በቋንቋ ሲናገሩ ቢሰሙ፥ ዕብዶች እንጂ፥ ጤናማ ሰዎች የተሰበሰቡበት ስብሰባ ነው ብለው እንደ ማይሉ ግልጽ ነው። እውነተኛ አስተማሪ በጠፋበት ቤተ ክርስቲያን፥ አማኞች ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ በመሆን ከሥርዓት ወጥተው እንደ ልባቸው በቋንቋ ቢናገሩ፥ ማኅበሩን በማነጽ ፈንታ ለማያምኑት እንቅፋት እንደሚሆኑ፥ ብዙዎች የተረዱት አይመስሉም። ቢያውቁም፥ አንዳንዶች ስለሌላው ሰው መደና ቀፍ ግድ የላቸውም። ጳውሎስ "በልሳን መናገር" ውስጥ ያለውን እንቅፋት የገለጸው፥ ስጦታው ክፉ ሆኖ ሳይሆን፥ የማያምኑ ሰዎች ከእግዚአብሔር ለመሸሽ ምክንያት አድርገው እንዳይጠቀሙበት በማሰብ ነው።

3.3. ትርጉሙን ሳይሰጡ ብዙዎች በቋንቋ ስለሚናገሩ፥ ዋጋ ያሳጡታል

ጳውሎስ ትርጉም ሳይኖረው ስለሚነገር ቋንቋ ሲገልጽ *"...ወንድሞች ሆይ፤ ወደ እናንተ መጥቼ በልሳኖች ብናገር፥ በመግለጥ ወይም በእውቀት ወይም በትንቢት፥ ወይም በትምህርት ካልነገርኋችሁ ምን እጠቅማችኋለሁ?"* ይላል (1 ቆሮ. 14፥6)። ትርጉም የሌለው ቋንቋ ጩኸት ብቻ ነው

ማለቱ ነው። ማኅበሩን ለማነጽ፥ ከሌላ ስጦታ ጋር አብሮ መሄድ የሚያስፈልገው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ቢኖር "በልዩ ልሳን መናገር" ነው። ተርጓሚ የሌለው ቋንቋ ሰሚውን እንግዳ ያደርጋል። *"እንግዲህ የቋንቋውን ፍች ባላውቅ ለሚናገረው እንግዳ እሆናለሁ፤ የሚናገረውም ለእኔ እንግዳ ይሆናል"* (1 ቆሮ. 14፥11)።

4. በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሁሉ በቋንቋ ይናገራል ወይ?

ከሌሎች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሁሉ የበለጠ "በልዩ ልዩ ዓይነት ልሳን ስለመናገር" ብዙ ተጽፏል። ዋናው ምክንያት ከስጦታዎች ሁሉ የበለጠ አከራካሪ በመሆኑ ነው። አከራካሪ የሆነበትም ትልቁ ምክንያት፥ ሁለት የተለያየ የእምነት አቋም ያላቸው ክፍሎች በመኖራቸው ነው። አንደኛው ክፍል በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላታችን ማረጋገጫው "በልዩ ቋንቋ የተናገርን እንደሆነ ብቻ ነው" የሚለውን እምነት የያዙ ናቸው። ሁለተኛው ክፍል ደግሞ "በቋንቋ ሳንናገር በመንፈስ ቅዱስ መሞላት እንችላለን" የሚለውን የእምነት አቋም የያዙ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ ግን በተለይ አሜሪካ ውስጥ ያሉ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት እንደ ጥንቱ "አንድ አማኝ በቋንቋ ካልተናገረ በመንፈስ ቅዱስ አልተሞላም" የሚለውን ሀሳብ እየተዉት መጥተዋል። በፔንቴኮስታል አካባቢ በጣም ከታወቁና ተቀባይነት ካላቸው አስተማሪዎች መካከል አንደኛው *ጃክ ሄይፈርድ* የተባሉ አሜሪካዊ ፓስተር ናቸው። *"The Beauty of Spiritual Language"* በሚለው መጽሐፋቸው፥ በልዩ ልዩ ልሳን ስለ መናገር ስጦታ በሰፊው ጽፈዋል። አንድ አማኝ "በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላቱ ምልክት እንዲሆነው በቋንቋ መናገር አለበት" የሚለውን ሀሳብ አይደግፉትም። ስለዚህ ሀሳብ ያላቸውን አስተያየት ሲገልጹ፥ ቀደም ሲል *"የፔንቴኮስታል እንቅስቃሴን ይመሩ የነበሩት*

ሰዎች፥ ብዙዎች በልሳን የመናገር ሞግት (ፍላጎት) እንዲያ ድርባቸው በማድረጋቸው በጣም አከብራቸዋለሁ። በሌላ በኩል ግን ሆን ብለውም ባይሆን የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ለሚናፍቁት ሰዎች፥ አንዳንድ እንቅፋቶች መፍጠራቸውን አልክድም። ይህም እንቅፋት አንድ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላቱ ምልክት ወይንም ማረጋገጫ በቋንቋ መናገር አለበት ብለው ማመናቸው ነው" አሉ።

ፒተር ዋግነር በፔንቴኮስታል አማኞች ዘንድ ሌላው ተቀባይነት ያላቸው ሰው ሲሆኑ፥ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሁሉ በቋንቋ መናገር አለባቸው ስለሚለው አባባል እንዲህ አሉ። *"በባህሪያቸው የሚደነቁ፥ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የበሰሉ አንዳንድ ወንድሞችና እህቶች በአዲስ ልሳን ለመናገር በጣም እየፈለጉ አብዛኛዎቹ እንዳልቻሉ እናውቃለን። እንደነዚህ ዓይነቶቹን በቋንቋ ሰላልተናገሩ ብቻ በመንፈስ ቅዱስ አልተሞሳችሁም ማለት ስህተት ከመሆኑም በላይ፥ ለስሚታቸው አለማሰብ ይሆናል። ከነዚህ መካከል ባለቤቴ ዶረስ አንደኛዋ ነች። በልሳን ለመናገር በጣም እየፈለገች፥ መናገር አልቻለ ችም። ይሁን እንጂ ከቅርብም ሆነ ከሩቅ ብዙ ሰዎች፥ በአጋ ንንት ለተሞሉ ሰዎች እንድትጸልይ ይጠይቋታል። ሰዎች ከአጋንንት እሥራት ነጻ እንዲወጡ የማድረግ ስጦታ እንጂ፥ በቋንቋ የመናገር ስጦታ አልተሰጣትም"*።

ይሄ ሃሳብ ብዙ አጠያያቂና አከራካሪ ነው። የራሴን የግል ልምምድ ለመግለጽ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስሞላ፥ በማያጠ ራጥር ሁኔታ፥ ማንም ሳይገፋኝ፥ ማንም "እንዲህ በል" ሳይለኝ በልዩ ቋንቋ ተናግሬአለሁ። አሁንም በግል የጸሎት ሕይወቴ፥ ከጌታ ጋር በማደርገው ግንኙነት በማውቀው ቋንቋ ራሴን መግለጽ ሲያቅተኝ፥ የጌታ ፍቅርና ውለታ ከውስጤ ፈንቅሎ ሲወጣ ለብቻዬ በልዩ ቋንቋ እጸልያለሁ። በዚህም የግል ሕይወቴ

ይታነጽበታል። የሚተረጎም መልዕክት ስለሌለኝ፥ በማኅበር መካ ከል ግን ጮክ ብዬ በቋንቋ አልናገርም። የእግዚአብሔርም ቃል ይህን እንዳደርግ አይፈቅድልኝም (1 ቆሮ. 14፥27-28)። ይሄ የግል ልምምዴ ነው። ይሁን እንጂ፥ እንደ እኔ በቋንቋ ያልተ ናገሩ፥ ለረጅም ዘመን ጌታን የተከተሉ፥ መንፈሳዊ አርአያ የሆኑኝ፥ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ፥ የክርስቶስ ቁንጅና በግልጽ በሕይወታቸው የሚታይባቸው፥ ወንድሞችና እህቶችን አውቃ ለሁ። እንደ እኔ በቋንቋ ባለመናገራቸው ብቻ በመንፈስ ቅዱስ አልተሞሉም ማለት በበኩሌ በጣም ይከብደኛል።

"በቋንቋ የመናገር" ስጦታ፥ በዓለም ውስጥ ለሚታየው የክርስትና እምነት እንቅስቃሴ ከማንኛቸውም "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች" ይበልጥ ከፍተኛ ሥፍራ አለው ብለው የሚያምኑ ክፍሎች አሉ። ይሄን ዓይነቱ ግምት በተለያዩ የክርስትና እም ነት "ቤተ እምነቶች" ውስጥ ከፍተኛ ጥርጣሬና መከፋፈልን፥ ልዩ ልዩ ዓይነት ችግሮችን እንደፈጠረ የታወቀ ነው። አንዳ ንድ ክርስቲያኖች "በቋንቋ የመናገር" ልምምድ ለአማኝ መን ፈሳዊ ሕይወት መሠረት ከመሆኑም በላይ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላቱ ወይንም ለመጠመቁ ማረጋገጫ ነው የሚሉ አሉ። ይህን ሀሳብ አጥብቀው የሚደግፉ፥ "በአዲስ ቋንቋ ባንናገርስ? በቋንቋ ሳንናገር በመንፈስ ቅዱስ ልንሞላ አንችልም?" ለሚለው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ፥ *"ስጦታው "በጥቅል" እንጂ በተናጥል አይሆንም። በቋንቋ መናገር፥ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት ሳይሆን፥ በመንፈስ ቅዱስ ሰንሞላ የሚመጣ ነው"* ይላሉ።

ሌሎች ደግሞ፥ ከላይ ከጠቀስነው ሀሳብ በጣም የራቁ ምዕመኖቻቸውን በቋንቋ እንዳይናገሩ አጥብቀው የሚከለክሉ አሉ። "ይህን ስጦታ በዘመናችን ለማንም አልተሰጠም፤ ስለዚህ በቋንቋ የመናገር ልምምድ ከሰይጣን ወይንም ከሥጋ ነው" ይላሉ። በነዚህ ሁለት የተለያዩ ሀሳቦች ምክንያት ብዙ ዓይነት

ሁከት፥ መከፋፈል፥ እኛ ልክ ነን ባይነት (dogmatism) ሊፈጠር ችሏል። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ "በቋንቋ መናገር" ብቻ ይመስል አንዳንዶች "ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ" መስማትም ሆነ መማር አይፈልጉም። በጥንት ቤተ ክርስቲያን እንደነበረው ሁሉ፥ *"አሰመሰሎ የሚነገር የውሸት (counterfeit) ቋንቋ"* በዘመናችንም እንዳለ የማያጠራጥር እውነት ነው። ይሁን እንጂ፥ በቋንቋ መናገርን የሚለማመዱ እውነተኛ አማኞች፥ ስለ "ቋንቋ መናገር" ያላቸው አቋም፥ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚናገረው ዕውነት ውጪ አይደለም። "በልዩ ልዩ ዓይነት ልሳን የመናገር" ስጦታ፥ ከዚህ በፊት ባልተማሩት ቋንቋ የመናገር ችሎታ (የሐዋ. 2፥1-1) እንደሆነና፥ ስጦታው ለተወሰኑ አማኞች እንጂ ለሁሉም እንደማይሰጥ የሚያምኑ ናቸው (1 ቆሮ. 12፥10፥30)።

5. "በቋንቋ ስለመናገር" ማወቅ የሚገባን መሠረታዊ እውነቶች

5.1. "በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ማንኛውም አማኝ በቋንቋ መናገር አለበትI በቋንቋ ካልተናገረ በመንፈስ ቅዱስ አልተሞላም" የሚለው አቋም አከራካሪና አጠያያቂ ነው። አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ በቋንቋ እንደተናገሩ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ሦስት የተለያየ ሥፍራ በግልጽ ተጠቅሶ እናያለን። ይኸውም፥

(ሀ) *በጰንጠቆስጤ በዓል ላይ፥ "በድንገት ብርቱ ዐውሎ ነፋስ የመሰለ ድምፅ ከሰማይ መጣI የነበሩበትንም ቤት ሞላው። የእሳት ነበልባሎች የሚመስሉ ምላሶች ታዩአቸውI ተከፋፍለውም በእያንዳንዳቸው ላይ ዐረፉባቸው። ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉI መንፈስ ቅዱስ እንዲናገሩ በሰጣቸው ችሎታ*

መጠን በሌሎች ቋንቋዎች መናገር ጀመሩ" (የሐዋ. 2፥1-4)።

(ለ) አረማውያን በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉበት ጊዜ፥ *"ለአረማውያን መንፈስ ቅዱስ እንደተሰጠ ያወቁትም፥ አረማውያን በሌሎች ቋንቋዎች ሲናገሩና እግዚአብሔርን በምስጋና ሲያከብሩ በመስማታቸው ነው"* (የሐዋ. 10፥46)።

(ሐ) የዮሐንስ ደቀመዛሙርት በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉበት ጊዜ፥ *"ጳውሎስ እጆን በጫነባቸውም ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ ወረደና በሌላ ቋንቋዎች ተናገሩI ትንቢትንም መናገር ጀመሩ"* (የሐዋ. 19፥6)። ከላይ እንዳየነው መንፈስ ቅዱስ በወረደበት በእያንዳንዱ ጊዜ ሁሉ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ፥ በቋንቋ እንደተናገሩ እናውቃለን። የተናገሩት ቋንቋ እነርሱ ከዚህ በፊት ተምረውት ባያውቁም፥ የሚያዳምጡት ትርጉሙ ይገባቸው ስለ ነበር፥ በእያንዳንዱ ጊዜ የእግዚአብሔር መልዕክት ለሕዝቡ ይተላለፍ ነበር። አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ከተሞሉ በኋላ በቋንቋ እንደተናገሩ በግልጽ አይተናል። ይህንን ሃሳብ የማይደግፉ ክፍሎች ደግሞ፥ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉበት ጊዜ በቋንቋ መናገራቸው ያልተገለጸበት ጊዜ አለ በማለት ከዚህ በታች የተጠቀሱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ያቀርባሉ።

ሐ.1. ጴጥሮስ በሽማግሌዎችና በካህናት አለቆች ፊት በቆመ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ እንደተሞላ እናያለን። *"...ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ*

እንዲህ አላቸው...” (የሐዋ. 4፥8) ይላል። ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ቢሞላም፥ በቋንቋ ግን ተናገረ አይልም። ይሁን እንጂ፥ ጴጥሮስ በጴን ጠቆስጤ ቀን ለመጀመሪያ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ሲሞላ በቋንቋ እንደተናገረ ግን እናስታውሳለን። ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ሲሞላ ይህ የመጀመሪያ ጊዜው አልነበረም።

ሐ-2. *ያመኑት ለጸሎት በተሰበሰቡ ጊዜ* በመንፈስ ቅዱስ እንደተሞሉ ይናገራል። ግን ቃሉን በድፍረት እን ደተናገሩ እንጂ፥ በቋንቋ መናገራቸውን አይገል ጽም። *“...ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ሰፍራ ተናወጠ፤ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባ ቸው፤ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ”* (የሐዋ. 4፥31)።

ሐ-3. እስጢፋኖስ በመንፈስ ቅዱስ ሲሞላ፥ በቋንቋ እንደተናገረ መጽሐፍ ቅዱስ አይገልጽም። *“...መንፈስ ቅዱስንም ተሞልቶ ወደ ሰማይ ትኩር ብሎ ሲመለከት የእግዚአብሔርን ክብር፥ ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየ...”* (የሐዋ. 7፥55) ይላል። “በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሁሉ በቋንቋ አይናገርም” የሚለውን ሀሳብ የሚ ደግፉ፥ ከላይ ያነበብነውን ጥቅስ መሠረት በማ ድረግ “በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሁሉ፥ በቋንቋ የሚናገር ቢሆን ኖሮ፥ ለማያምኑት ምልክት እን ዲሆን እስጢፋኖስም በተናገረ ነበር” ይላሉ።

ሐ-4. አሁንም በአንጾኪያ የነበሩት ክርስቲያኖች በመን ፈስ ቅዱስ የተሞሉ ቢሆንም በቋንቋ መናገራቸ

ውን አይገልጽም ይላሉ። *“...በደቀ መዛሙርቱም ደስታና መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው”* ይላል (የሐዋ. 13፥52)። ከላይ ያየናቸው ጥቅሶች ትክክለኛ ሃሳቡን ይገልጹ ይሆን? እነዚህ ሰዎች ቀደም ሲል በልሳን የተናገሩ ሊሆኑ አይችሉም? ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስ በወረደበት ወቅት በልዩ ልሳን ከተናገሩት ሰዎች መካከል አልነበረም (የሐዋ. 2)? ይሄ ሃሳብ በጣም የሚያከራክርና የሚያ ጠያይቅ ነው ያልንበት ምክንያት ለዚህ ነው።

5.2. ጳውሎስ ይህንን ስጦታ በ1ኛ ቆሮንቶስ መልዕክቱ ከ 12 እስከ 14 ባሉት ምዕራፎች አንድ ጊዜ ብቻ እንደ ጠቀሰው እናያለን። ጳውሎስ አማኞችን በቋንቋ ባለመናገራቸው፥ ወይንም በመናገራቸው ምክንያት አልወቀሳቸውም። የወቀ ሳቸው ስጦታውን ያለአግባብ በመጠቀማቸውና እንዲሁም ስጦታውን ከሌሎች ስጦታዎች ሁሉ ይበልጥ አጋነው በመናገራቸው ብቻ ነው። *“ነገር ግን በአዲስ ቋንቋ ዐሥር ሺ ቃላት ከምናገር ይልቅ ሌሎችን ለማስተማር ስል በክ ርስቲያኖች መካከል አምስት ቃላትን በሚታወቅ ቋንቋ በአዕምሮዬ መናገር እወዳለሁ* ይላል (1 ቆሮ. 14፥19)።

5.3. አንዳንድ ክርስቲያኖች በቋንቋ ስለመናገር በቃሉ የተደገፈ ሀሳብ በመስጠት ፈንታ፥ በልምምዳቸው ላይ ትኩረት ይሰጣሉ። ብዙዎች በቋንቋ እንናገራለን ይበሉ እንጂ፥ ልምምዳቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ የተደገፈ አድርገው ማቅ ረብ አይችሉም። አንዳንዶች “በቋንቋ መናገር” የሚቻልበ ትን መንገድ በመጽሐፍ ጽፈው አቅርበዋል። በቋንቋ ለመ ናገር ለሚፈልግ ሰው አንዳንድ መመሪያ በቅደም ተከተል ተዘርዝሮ ተሰጥቶታል። “አንዱን ቃል ብቻ እየደጋገምክ በል! ኢየሱስ! ኢየሱስ!... አሜን! አሜን! አሜን...”

የሚለውን ቃል ደጋግመህ በልI ከዚያ በኋላ ምላስህ ይተ ሳሰርና በቋንቋ መናገር ትጀምራለህ" ይሉታል። እንግዲህ፥ በዚህ ዓይነት አንዳንድ ዘዴ ተጠቅመን የምንናገረው ቋንቋ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንደሆነ ምን ያህል እርግጠኞች እንሆናለን?

5.4. "በቋንቋ ስንናገር እምነታችን ያድጋል" የሚሉ አማኞች አሉ። እርግጥ ነው በቋንቋ በመናገር መታነጽ እንዳለ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። *"በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል..."* (1 ቆሮ. 14፥4) ይላል። በቋንቋ ስንናገር ከእግዚአብሔር ጋር ቅርብ እንደ ሆንን ሊሰማን ይችል ይሆናልI ይሁን እንጂ፥ በእርግጥ በቋንቋ በመናገራችን ብቻ እምነታችን ያድጋል? ቢሆን ኖሮ፥ መጽሐፍ ቅዱስ *"እምነት ከመሰማት ነውI መሰማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው"* (ሮሜ 10፥17) ባላለም ነበር።

5.5. በቋንቋ መናገር፥ ከስጦታዎች ሁሉ በቀላሉ "አስመስሎ መናገር፥ ወይንም መዋሸት (counterfeit) የሚቻልበትና እንዲሁም በቋንቋ የሚናገሩት አማኞች ከቁጥጥር ውጪ ሊወጡ የሚችሉበት ስጦታ ነው። በ1ኛ ቆሮንቶስ ከ12 እስከ 14 ባሉት ምዕራፎች ላይ ጳውሎስ የጠቀሰው ወይ ንም ሊያስጠነቅቅ የሞከረው "እውነትነት ስለሌላቸው ቋንቋዎች" ሳይሆን፥ ምዕመናኑ በቋንቋ ሲናገሩ ከሥርዓት ውጪ በመሆናቸው ነው። ጳውሎስ የቆሮንቶስን ምዕመ ናን ሲመክር፥ *"...በልሳኖች ከመናገርም አትከልክሉI ነገር ግን ሁሉ በአግባብና በሥርዓት ይሁን"* ይላቸዋል (1 ቆሮ. 14፥40)። ከሥርዓት ውጪ ከመሆን ሌላ፥ እውነ ተኛነት የሌለውን ቋንቋ አስመስሎ መናገርም ይቻላል።

5.6. አንዳንድ ክርስቲያኖች "በቋንቋ መናገርን" አጥብቀው

በማወጅ የክርስቲያኖችን አንድነትና ሕብረት ሲያፈር ሱና ሲያበላሹ ይታያሉ። እኛ "በመንፈስ ቅዱስ ተሞል ተናል" የምንለው አማኞች፥ በእርግጥ በመንፈስ ቅዱስ ከተሞላን፥ "አልተሞሉምI ደካማ ክርስቲያኖች ናቸው" የምንላቸውን ማቀፍ እንጂ፥ መግፋት እንደሌለብን መጽ ሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይመክረናል። *"...በትሕትናና ሁሉና በየዋህነትና በትዕግሥትም እርስ በርሳችሁ በፍቅር ታገሡI በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ"* ይላቸዋል (ኤፌ. 4፥2-3)። አንዳንድ አማኞች ይህን የጳውሎስን ምክርና ትምህርት ችላ በማለት የራሳ ቸውን ልምምድ በማስተጋባት የክርስቲያኖችን አንድነት ሲያበላሹ እናያለን። መንፈሳዊ ዕድገት የሚገኘው የአማ ኞችን አንድነት በመጠበቅ እንደ ሆነ ጳውሎስ በተለያየ መልዕክቱ ገልጾታል። ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ከሰጣ ቸው ትዕዛዞች ውስጥ አንደኛው፥ *"እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ፥ እንደ ወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ"* (የዮሐ. 13፥34) ያለው ነው። እንደ ማንኛውም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፥ "በቋንቋ መናገርም" በፍቅር የተቀመመ መሆን አለበት። በቋንቋ መናገራችን ሌላውን ወንድም የሚያሰናክል ከሆነ፥ በቋንቋ ለመናገር ነጻነት ቢኖረንም፥ ለዚያ ወንድም ስንል በቋንቋ የምንናገርበትን ጊዜና ሥፍራ መምረጥ ይኖርብናል። *"...እንግዲህ ከዛሬ ጀምሮ እርስ በርሳችን አንፈራረድI ይልቁን ግን ለወንድም እንቅፋትን ወይም ማሰናከያን ማንም እንዳያኖርበት ይህን ቁረጡ"* (ሮሜ 14፥13)። በቋንቋ የመናገር ስጦታው ያለው፥ ተርጓሚ እንዳለ በማወቅ ስጦታውን በጉባኤው መካከል ለመጠቀም ቢፈልግ፥ በመንቀፍ ፈንታ በፍቅር ተሞልተን ስጦታውን እንዲጠቀም መፍቀድ ይገባናል።

በቋንቋ የመናገር ስጦታውን እንዳይጠቀም መከልከል፥ ከፍቅር ውጪ መሆን ነው።

7. በቋንቋ የመናገር ስጦታ ያላቸው አማኞች ሊገነዘቡት የሚገባ አንዳንድ እውነቶች

7.1. "በቋንቋ የመናገር ስጦታ" ከሁሉም ስጦታዎች ይበልጣል ብሎ ማሰብ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚናገረው ውጪ መሆን ነው። ይህ እውነት ቢሆን ኖሮ ጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ሲዘረዝር *"በቋንቋ መናገርን"* ከስጦታዎች ሁሉ ይበልጣል ባለ ነበር (1 ቆሮ. 14፥28)። ጳውሎስ *"... በልሳኖች ከሚናገር፥ ትንቢትን የሚናገር ይበልጣል"* ይላል (1 ቆሮ. 14፥5)። ጳውሎስ ይህን ያለበት ስጦታ ዎችን ለማበላለጥ አስቦ ሳይሆን፥ በወቅቱ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የትንቢት ስጦታ በጣም ያስፈልግ ስለነበረ ብቻ እንደሆነ ቀደም ሲል ገልጸናል።

7.2. "በቋንቋ መናገር" የመተርጎም ስጦታ ባለው አማኝ ካል ተተረጎመ፥ ማኅበሩን ማነጽ እንደማይችል ማወቅ ያስፈል ጋል። ተርጓሚ የሌለው የቋንቋ ንግግር፥ ማኅበሩን ሳይሆን ተናጋሪውን ያንጻል። *"...ማኅበሩ ይታነጽ ዘንድ ንግግሩን ባይተረጉም፥ በልሳኖች ከሚናገር ትንቢትን የሚናገር ይበልጣል"* (1 ቆሮ. 14፥5)። ስለዚህ፥ ማኅበሩ የማይታነ ጽበትን ቋንቋ በጉባኤው መካከል መናገር፥ መጽሐፍ ቅዱስን መቃረን ይሆናል።

7.3. "በቋንቋ መናገር" የተሰጠው የማያምኑትን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ስለሆነ፥ ማህበሩን ለማነጽ ከመጠቀም ይልቅ ያልዳኑትን ወደ ደህንነት እንዲመጡበት መጠቀም ያስፈ ልጋል።

7.4. ቋንቋ በማኅበር ከተነገረ የግድ ተርጓሚ እንዲኖረው ጳውሎስ ያስተምራል። ተርጓሚ ከሌለ በማኅበር መካከል ዝም በሉ ይላል። *"በልሳን የሚናገር ቢኖር፥ ሁለት ወይም ቢበዛ ሦስት ሆነው በተራቸው ይናገሩ፤ አንዱም ይተርጉም፤ የሚተረጉም ባይኖር ግን በማኅበር መካከል ዝም ይበልና ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር"* ይላል (1 ቆሮ. 14፥27-28)።

ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፥8-12 ከዘረዘራቸው ዘጠኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ውስጥ መጨረሻ የተጠቀሰው፥ *"በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም"* ነው። ይሄ ስጦታ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያንጹ ከሚሰጡት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መካከል አንደኛው ቢሆንም፥ ከስጦታዎች ሁሉ ችላ የተባለ ስጦታ ነው። ይህ ስጦታ ከሌላው ስጦታ ጋር አብሮ ካልሄደ ብቻውን ምዕመናኑን ማነጽ አይችልም። *"በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም"* ስንል፥ ህልምን፥ በዓይን የሚታዩትን አንዳንድ ስዕሎችን መተርጎም ማለት አይደለም። ለማህበሩ "በልዩ ልዩ ዓይነት ቋንቋ" የተነገረውን መልዕክት የሚተረጉም ሰው ከሌለ፥ ማህበሩ ሊታነጽበት ስለማይችል፥ በቋንቋ የተላለፈው መልዕክት ዋጋ አይኖረውም። ፒተር ዎሜር *"በልሳኖች የተነገረውን የመ ተርጎም ስጦታ"* ምን እንደሆነ ሲገልጹ፥ እንዲህ አሉ። *"በልሳ ኖች የተነገረውን የመተርጎም ስጦታ"* ማለትም፥ ለቤተ ክርስቲ ያን በልዩ ቋንቋ የተሰጠውን መልዕክትም፥ አንዳንድ አማኞች መተርጎም የሚያስችላቸው ስጦታ ነው።" "የመተርጎም ስጦታ" በልዩ ቋንቋ የተነገረውን መልዕክት፥ ምዕመናኑ በሚገ ባው ቋንቋ መተርጎም ማለት ነው።

አንዳንድ አማኞች "በቋንቋ የመናገር ስጦታ" ሳይኖ ራቸው፥ በቋንቋ የተነገረውን መተርጎም ይችላሉ። ይሁን እንጂ፥ ብዙ ጊዜ እንዲህ ዓይነቱ የተለመደ አይደለም። አብዛ

ኛዎቹ በቋንቋ የመናገር ስጦታ ያላቸው፥ የመተርጎምም ስጦታ ይኖራቸዋል። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ *"በልሳን የሚናገር እንዲተረጉም ይጸልይ"* (1 ቆሮ. 14፥13) ያለው። ይህም ማለት በማኅበር ቆመው በልዩ ቋንቋ የተናገሩትን ራሳቸው ማኅበሩ በሚገባው ቋንቋ ይተረጉሙታል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አንዱ በቋንቋ ሲናገር፥ ሌላው የመተርጎም ስጦታ ያለው ይተረጉማል። ጳውሎስ ሥርዓቱን በደንብ ጽፎልናል። *"በልሳን የሚናገር ቢኖር፥ ሁለት ወይም ቢበዛ ሦስት ሆነው በተራቸው ይናገሩ፤ አንዱም ይተርጉም፤ የሚተረጉም ባይኖር ግን በማኅበር መካከል ዝም ይበል፥ ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር"* ይላል (1 ቆሮ. 14፥27-28)።

በአዲስ ቋንቋ የመናገር ስጦታው ያለው ሰው በማኅበሩ ፊት ሲናገር በአዲስ ቋንቋ የተነገረውን የሚተረጉም ሰው ካለ፥ በቋንቋ የተነገረው መልዕክት "ከትንቢት" ጋር ተመሳሳይነት አለው። ጳውሎስ *"...በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው እንጂ ለሚያምኑ አይደለም"* (1 ቆሮ. 14፥22) ሲል፥ ምን ማለቱ ነው? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። በባለ ሃምሳኛው ቀን 120ዎቹ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው እግዚአብሔርን በልዩ ቋንቋ ሲያመሰግኑ የሰሟቸው ሰዎች አማኞች እንዳልነበሩ እናውቃለን። ለዚህ ነው "በጠዋት ጠጥተው ሰክረዋል" በማለት የተቹአቸው። ይሁን እንጂ የራሳቸውን ቋንቋ በመስማታቸው ትልቅ መደነቅ እንደነበረና ብዙዎች ወደ ክርስትና እምነት እንደ መጡ እናውቃለን።

"ፍላየን" የተባለው ክርስቲያን ጸሐፊ ስለ መተርጎም ስጦታ ሲናገር፥ *"በልዩ ልሳን የተነገረው የባዕድ ቋንቋ ከሆነ፥ የመተርጎም ስጦታ ያለው ሰው ቋንቋውን ከዚህ በፊት ሳይማርና ሳያውቅ እንዲሁ መተርጎም ሲችል ነው። በልዩ ልሳን የተነገረው በመቃተት ድምፅ* (ecstatic utterance) *ብቻ ከሆነ፥*

የመተርጎም ስጦታ ያለው ሰው የቋንቋ መተርጎም ስልትና ሕግ ባልተከተለ ሁኔታ መተርጎም ሲችል ነው" አለ። ይህም ማለት የተነገረው ልሣን፥ የሚተረጎም ቋንቋ ከሆነ፥ ተናጋሪው በቋንቋ የተናገረውን የተሰበሰበው ሕዝብ በሚገባው ቋንቋ ይተረጉማል። የተነገረው ልሣን ቋንቋ ሳይሆን "የመቃተት ድምፅ" ብቻ ከሆነ ደግሞ፥ የመተርጎም ስጦታ ያለው ሰው ያንን የመቃተት ድምፅ የመረዳትና ለተሰበሰበው ሕዝብ የመግለጽ ችሎታ ይኖረዋል። በቋንቋ የሚተላለፈውን መልዕክት ተርጓሚው ጠቅላላ ሀሳቡን ይተረጉማል እንጂ ቃል በቃል አይተረጉምም። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህ ስጦታ ለመግለጽ የሞከረው ዋና ፍሬ ሀሳብ መልዕክቱን "የመረዳት ችሎታ" መሆኑን ልብ ማለት ይገባናል። ትኩረቱ "በቋንቋ የመናገር ልምምዱ" ላይ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር ለማስተላለፍ በሚፈልገው መልዕክት ላይ ነው።

ጳውሎስ "የመተርጎም ስጦታ" ሲል፥ አንዱን ቋንቋ ወደ ሌላው ቋንቋ መተርጎም ማለቱ አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሔር ሊያስተላልፈው የሚፈልገውን መልዕክት ቋንቋውን በሚናገረውና በሚያስተረጉመው ሰው አማካኝነት መረዳት መቻል ነው። የዚህ ስጦታ ዋና ዓላማ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ ነው። ለዚህ ነው በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 14 ላይ በተደጋጋሚ ሀሳቡ የተገለጸው። *"...በልሳን መናገር አለውን መተርጎምም አለውን ሁሉ ለማነጽ ይሁን"* ይላል (1 ቆሮ. 14፥26)። በዚህ ቃል መሠረት ቤተ ክርስቲያን ልትታነጽ የምትችለው፥ ስጦታውን በሥርዓትና በአግባቡ መጠቀም የቻልን እንደሆነ ብቻ ነው። ጳውሎስ *"...በልሳኖች ከመናገርም አትከልክሉን ነገር ግን ሁሉ በአግባቡና በሥርዓት ይሁን"* (1 ቆር. 14፥40) ብሎ የሚመክረን ለዚህ ነው። ብዙ ጩኸት፥ ከሥርዓት የወጣ ልምምድ የአምላኪውን ሀሳብ የሚበታትን ከመሆኑም በላይ፥ እግዚአብሔር ሊያስተላልፍ የሚፈልገውን መልዕክት ማኅበሩ እንዳይ

ረዳ ዕንቅፋት ይሆናል። በቋንቋ የመናገር ስጦታ፥ ተናጋሪውን ከሥርዓትና ከቁጥጥር ውጪ እንዲወጣ አያደርገውም። ስጦታው ያለው ሰው ራሱን መቆጣጠርና መግታት ይችላል። ጳውሎስ *"በልሳን የሚናገር ቢኖር ሁለት ወይም ቢበዛ ሦስት ሆነው በተራቸው ይናገሩ! አንዱም ይተርጉም"* (1 ቆሮ. 14፥27) ይላል። ተናጋሪዎቹ ከሦስት እንዳይበልጡ፥ እነርሱም ተራ በተራ እንዲናገሩ ይሁን ያለበት ዋናው ምክንያት ሥርዓት ለመጠበቅ እንዲችሉ ነው። ማጎበሩ መታነጽ የሚችለውም ተርጓሚ ካለ ብቻ እንደሆነ ተናግሯል።

በልዩ ልሣን የሚናገረው ሰው የመተርጎም ስጦታ ከሌለው፥ ማጎበሩ ከእግዚአብሔር መልዕክት ለመቀበል የሚጠብቀው ከአንድ ሰው ብቻ ስለሚሆን፥ አደገኛ ነው። ለምሳሌ መጋቢው የሰበከው፥ ወይንም ያስተማረው ትምህርት ልክ መሆኑን ለመ መዘን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እናመሳክራለን! በቋንቋ የተነገ ረውን መልዕክት ግን የምንጠብቀው ከተርጓሚው ብቻ ነው። ብዙ ጊዜ አንዳንድ አማኞች ይህንን ስጦታ ያለአግባብ ሲጠቀ ሙበት ይታያሉ። ስለዚህ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። መንፈስ ቅዱስ የአንድነት እንጂ የመከፋፈል (የመለያየት) መን ፈስ አይደለም። የመንፈስ ቅዱስ ባህሪው ሁሉን ማፍቀር ነው። የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን የፈሰሰው በመንፈስ ቅዱስ አማ ካኝነት ነው። "ፍቅር የለሽ" መሆን፥ መከፋፈል፥ የቡድን መንፈስ ሁሉ ከእርሱ የመነጨ አይደለም። እነዚህ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ይገታሉ። ለመንፈስ ቅዱስ ነፃነት ስንሰጠው፥ ሕይወታ ችንን በነጻነት ይመራል! ይቆጣጠራል። የራሱን ፈቃድ ይፈጽ ማል! በሕይወታችንም ይሠራል።

☆ ☆ ☆ ☆

ምዕራፍ
8

ትንቢት የመናገር ስጦታ

"...ለሌላው የትንቢትን ቃል የመናገር ችሎታን ይሰጠዋል..."
(1 ቆሮ. 12፥10)

ጳውሎስ ከዘረዘራቸው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መካ ከል ደጋግሞ የጠቀሳቸው ስጦታዎች፥ *"በልዩ ልዩ ልሣን መናገርንና ትንቢትን"* ነው። ደጋግሞ የጠቀሰበት ዋናው ምክንያት አንዳንድ አማኞች "በቋንቋ መናገርን" ያለአግባብ ሲጠቀሙበት፥ "ትንቢትን" ደግሞ ችላ ሲሉት በማየቱ ነበር። አንዳንድ አማኞች "በቋንቋ የመናገር" ስጦታን ከመጠን በላይ ሲያጋንኑ፥ "ትንቢትን" ግን ችላ ሲሉ በመመልከቱ፥ በወቅቱ በመካከላቸው ተፈጥሮ የነበረውን ችግር ለማቃለል፥ *"...ሁላችሁ በልሳኖች ልትናገሩ እወድ ነበር! ትንቢትን ልትናገሩ ግን ከዚህ ይልቅ እወዳለሁ! ማጎበሩ ይታነጽ ዘንድ ንግግሩን ባይ ተረጉም በልሳኖች ከሚናገር ትንቢትን የሚናገር ይበልጣል"*

(1 ቆሮ. 14፥5) ሲል ጻፈላቸው። በዘመናችንም ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መካከል የበለጠ ትኩረት የሚሰጠው፥ "የትን ቢትና በልዩ ልዩ ልሣን የመናገር" ስጦታዎች ናቸው። ዋናው ምክንያት በነዚህ ስጦታዎች የሚገለገሉ አብያተ ክርስቲያናት ቁጥራቸው እየጨመረ በመምጣቱ እንደ ሆነ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይናገራሉ። እርግጥ ነው ብዙዎች በነዚህ ስጦታዎች አማካኝነት ብዙ በረከትን ከእግዚአብሔር ተቀብለ ዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ስጦታው ሳይኖራቸው "ስጦታው አለን" በሚሉ "ውሸተኞች" ምክንያት የተጎዱ ብዙ እንደሆኑ እናውቃለን። ስጦታው "እውነት" ከሆነ፥ ቤተ ክርስቲያን ትታ ነጽበታለች። ስጦታው እውነት ካልሆነ ግን፥ ቤተ ክርስቲያን እንድትታወክና እንድትረበሽ ዓይነተኛ ምክንያት ይሆናል። ስጦታው ሳይኖራቸው ትንቢት በሚናገሩ አንዳንድ አማኞች ምክንያት፥ በአጠቃላይ የትንቢትን ስጦታ መቀበል የሚያቅተን ጊዜ አለ። ለዚህ ነው ጳውሎስ *"ትንቢትን ሁሉ አትናቁ"* በማለት የሚያስጠነቅቀን።

የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በሁለተኛው የሐዋርያው ጳውሎስ ሚሲዮናዊ ጉዞ ወቅት፥ ጳውሎስ አቴንስን ለቅቆ ከወጣ በኋላ እንደሆነ ይታወቃል። በዚያን ዘመን ቆሮን ቶስ በጣም በኃጢአት የረከሰች ከተማ ነበረች። በቆሮንቶስ ከተማ የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን የነበረችበትን ሁኔታ መመልከት፥ ጳውሎስ ሁለቱን ደብዳቤዎቹን ለምን እንደጻፈ መረዳት ያስችለናል። በተለይ *"የትንቢትን"* ስጦታ በቤተ ክር ስቲያኒቱ ውስጥ ከሌሎች ስጦታዎች የበለጠ መለማመድ አለባ ችሁ ያለበትን ምክንያት እንድናውቅ ይረዳናል። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12 ላይ በሰፊው ተንትኖ ከጻፈ በኋላ፥ ስጦታዎቹን በፍቅር ልብ መለማመድ እንዳለባቸው ለማስተማር 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 13ን ጻፈ።

ስለ ፍቅር የጻፈውን መልዕክት ደምድሞ ምዕራፍ 14ን ሲጀ ምር፥ *"ፍቅርን ተከታተሉ፤ መንፈሳዊ ስጦታንም ይልቁንም ትንቢት መናገርን በብርቱ ፈልጉ"* አለ (1 ቆሮ. 14፥1)። ይህን ያለበት ምክንያት "ፍቅር" ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ጋር አብሮ መሄድ እንዳለበት ለመግለጽ ነው።

1. ትንቢት የመናገር ስጦታ ምንድነው?

ፒተር ዋግነር "ትንቢት የመናገር ስጦታ" ምን እንደ ሆነ ሲገልጹ *"የትንቢት መናገር ስጦታ ማለትም፥ የቤተ ክርስ ቲያን አካል ለሆኑት አንዳንድ አማኞች፥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሊያስተላልፈው የሚፈልገውን መልዕክት ተቀብለው እንዲያ ስተላልፉ የሚያስችል ስጦታ ነው"* አሉ። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12 ላይ *"...ለአንዱም ትንቢትን መናገር..."* ይሰጠዋል ይላል። ጳውሎስ እዚህ ላይ *"ትንቢት"* ሲል ምን ማለቱ ይሆን? በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መካከል *"ትንቢት"* የሚለውን ሀሳብ አንዳንድ ክርስቲያኖች የተሳሳተ ትርጉም ሲሰጡት እናያለን። ሁለት ጎልተው የሚታዩ ስህተቶች አሉ።

(1) አንዳንድ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ አማኞች፥ ወይንም ተከታዮች "ትንቢት" ማለት *"የወደፊቱን መተንበይ"* ብቻ እንደሆነ አድርገው የሚወስዱ አሉ። *"ትንቢት"* የወደፊትን ማወቅ ወይንም መተንበይ ቢሆንም፥ አገልግሎቱ ያ ብቻ ነው ማለት ግን ትልቅ ስህተት ነው። "ትንቢት" የወደ ፊቱን ብቻ ሳይሆን በጊዜውም ያለውን ሁኔታ ያመለክታል።

(2) ሌላው ስህተት ደግሞ፥ "ትንቢት" "የእግዚአብሔርን ሀሳብ መግለጽ ወይንም፥ ማወጅ ነው" የሚለውን ሀሳብ ስለያዘ፥ *"ትንቢትን"* ከስብከት ጋር አንድ ዓይነት አድርገው የሚመ

ለክቱ አማኞች መኖራቸው ነው። "ስብከት" በጽሁፍ ያለ ውን የእግዚአብሔርን ሀሳብ ለሕዝቡ ማወጅ ወይንም ማሳ ወቅ ስለሆነ፥ "ስብከት" ሌላ ነገር ሳይሆን "ትንቢት ነው" ብለው የሚከራከሩ ክርስቲያኖች አሉ። በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ ስብከት "ትንቢታዊ ቃል" ሊኖረው ቢችልም፥ መጽሐፍ ቅዱስ "ትንቢትን" ከማስተማር ወይንም ከመስበክ ጋር አንድ ዓይነት ነው ብሎ አያቀርብልንም። ትንቢት፥ ከስብከት ወይንም ከማስተማር ጋር አንድ ዓይነት ቢሆን ኖሮ፥ ጳውሎስ ስጦታዎችን ሲዘረዝር፥ "የማስተማር ስጦታ"፥ "የትንቢት ስጦታ..." እያለ ለየብቻቸው ባልዘረዘራቸውም ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ሲዘረዝር፥ *"እግዚአብሔርም በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን አስቀድሞ ሐዋርያትን፥ ሁለተኛም ነቢያትን፥ ሦስተኛም አስተማሪዎችን፥ ቀጥሎም ተአምራት ማድረ ግን፥ ቀጥሎም የመፈወስን ስጦታ፥ እርዳታንም፥ አገዛዝ ንም፥ የልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖችንም አድርጓል"* (1 ቆሮ. 12፥28) ይላል።

ለጊዜው የእኛን ግምትና አስተያየት ትተን ጳውሎስ *"የትንቢት ስጦታ"* ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ በጥንቃቄ መመርመር ያስፈልገናል። "በማስተማርና" በትንቢት መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። "የማስተማር ስጦታ" ማለት ስጦታው ያለው ሰው ከእግዚአብሔር ቃል ውስጥ፥ ልዩ የሆነ መገለጥ ወይንም አዲስ የሆነ መረዳት ሲያገኝ ነው። "ትንቢት" ግን ስጦታው ባለው ሰው እግዚአብሔር በቀጥታ መልዕክቱን በአንድ በተለየ ሁኔታ ውስጥ ላሉ አማኞች ወይንም አንድ አማኝ መልዕ ክቱን ሲያስተላልፍ ነው። የትንቢትም ሆነ የማስተማር ስጦታ፥ ሰው በተፈጥሮው የሚያገኘው ችሎታ አይደለም። ሁለቱም የጸጋ ስጦታዎች ስለሆኑ፥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች እንደ ሆኑ ማወቅ ያስፈልገናል። ጳውሎስ "ትንቢት" ሲል፥ እግዚ

አብሔር የሚሰጠውን "መገለጥ" ወይንም "ራዕይ" በቃላት ማወጅ ማለቱ ነው። "ትንቢት" ቀደም ሲል ሰው አዘጋጅቶ የሚሰብከው ስብከት፥ ወይንም አማኝ በትምህርት፥ ወይንም በልምምድ የሚያገኘው ችሎታ አይደለም።

የትንቢት ቃል ለአማኞች የሚተላለፈው በምን ዓይነት ሁኔታ ነው? አንዳንድ ክርስቲያኖች ይህንን ባለማወቅ፥ ትንቢት ሲናገሩ በኃይል ሲወጣጠሩና ቁና ቁና ሲተነፍሱ ይታያሉ። ፊኛ በዓየር እንደሚሞላው እነርሱም በትንቢት ቃል የሚሞሉ ስለሚመስላቸው፥ መልዕክቱ ውስጣቸውን በግድ እየፈነቀለ የሚወጣ በማስመሰል፥ ትንቢት ለመተንበይ ሲወጣጠሩና ሥራ ቸው ሲግተረተር ይታያሉ። ትንቢት ሌላ ነገር ሳይሆን *"የመገ ለጥ ቃል"* እንደሆነ ጳውሎስ ይናገራል። *"ነቢያትም ሁለት ወይም ሦስት ሆነው ይናገሩ ሌሎችም ይለዩአቸው"* ይልና፥ ቀጥሎ *"በዚያ ለሚቀመጥ ለሌላ ግን አንድ ነገር ቢገለጥለት ፊተኛው ዝም ይበል"* ይላል (1 ቆሮ. 14፥30)። *"አንድ ነገር ቢገለጥለት"* ሲል፥ የትንቢት ስጦታ "የመገለጥ ቃል" እንደ ሆነ እናያለን። በዚህ ዓይነት "ትንቢት" ድንገት ከእግዚአብሔር የሚሰጥ እንጂ፥ የተዘጋጀ ስብከት፥ ወይንም ትምህርት እንዳል ሆነ እንገነዘባለን። ስጦታው ያላቸው አማኞች "መገለጥን" የሚያ ገኙት በምን ዓይነት መልክ ነው? መልዕክቱን የሚቀበሉት በራዕይ፥ በህልም፥ በቃላት፥ በስሜት ይሆን? ወይንስ በጆሮአ ቸው ይሰማሉ? ጳውሎስ ጥቃቅኑን ሀሳብ ሁሉ አይተነትንም። ይሁን እንጂ፥ መልዕክቱ የሚያምኑትም ሆነ የማያምኑት ሊረ ዱት የሚችሉት ሀሳብ እንደሆነ እርግጠኞች ነን። የትንቢት ስጦታ ላላቸው ሰዎች "የትንቢት ቃል" በሦስት ዓይነት ሁኔታ እንደሚመጣላቸውና መልዕክቱን እንደሚያስተላልፉ የሰነ መለኮት ምሁራን ያስተምራሉ። ይኸውም፥

1ኛ/ የትንቢት ስጦታ ያለው ሰው መልዕክቱን እግዚአብሔር ወደ አዕምሮው ሲያመጣለት፤ ለሚመለከታቸው ሰዎች መልዕክቱን ወዲያው አያስተላልፍም። መልዕክቱን ከእግዚአብሔር ቀደም ሲል ቢቀበልም፥ ከማስተላለፉ በፊት ሰዓታት፥ ወይንም ቀናት ሊያልፉ ይችላሉ።

2ኛ/ የትንቢት ስጦታ ያለው አማኝ ከእግዚአብሔር መልዕክቱን በከፊል ተቀብሎ፥ በእምነት ማስተላለፍ ሲጀምር የተቀረውን መልዕክት ይቀበላል።

3ኛ/ የትንቢት ስጦታ ያለው ሰው ከእግዚአብሔር መልዕክት ሲመጣለት፥ ወዲያው ተነስቶ "እንዲናገር የሚገፋ ስሜት" በውስጡ ይሰማዋል። መናገር ሲጀምር ከእግዚአብሔር የተሰጠውን መልዕክት በሙላት ይቀበልና ያስተላልፋል።

የትንቢት ስጦታ ያላቸው አማኞች የእግዚአብሔር ዓላማ ምን እንደሆነ ግልጥ ባለ ሁኔታ የመረዳት ችሎታ ይሰጣቸዋል። ይሁን እንጂ፥ ነብያት ሊሳሳቱ ስለሚችሉ፥ የቤተ ክርስቲያኒቱ አካል የሆኑ አማኞች ሲያርሟቸው፥ እርማቱን መቀበል አለባቸው። እውነተኛ ነብይ፥ በሚስትበት ወቅት "እርማት አልቀበልም" አይልም። የሚተነብዩት ትንቢት፥ በእግዚአብሔር ቃልና በእግዚአብሔር ሕዝብ መፈተን እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። *"ነቢያትም ሁለት ወይም ሦስት ሆነው ይናገሩ፤ ሌሎችም ይለዩአቸው"* ይላል (1 ቆሮ. 14፥29)። በዚህ ቃል መሠረት ነብያት የተነበዩትን ሁሉ ሳንፈትን መቀበል እንደሌለ ብን እንረዳለን። ነብያትም ከሳቱ፥ ስህተታቸውን በደስታ መቀበል አለባቸው።

"ትንቢት" የሚለው ቃል *"ፕሮፌሚ"* ከሚለው የግሪክ

ማለት ነው። ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ እንዲያወጣ እግዚአብሔር ሲጠራው፥ "መናገር አልችልም" በማለት ጥሪውን ላለመቀበል ሞክሮ እግዚአብሔርን አስቆጥቶት እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ዘጸ. 4፥14)። ሙሴ በወቅቱ የነበረበትን ችግር ለማቃለል እግዚአብሔር *"...ሌዋዊው ወንድምህ አሮን አለ አይደለምን? እርሱ ደህና እንዲናገር አውቃለሁ፤ እነሆም ደግሞ ሊገናኝህ ይመጣል፤ ባየህም ጊዜ በልቡ ደስ ይለዋል። አንተም ትናገረዋለህ፤ ቃሉንም በአፉ ታደርገዋለህ። እኔ ከአፍህና ከአፉ ጋር እሆናለሁ፤ የምታደርጉትንም አስተምራችኋለሁ። እርሱ ስለ አንተ ከሕዝቡ ጋር ይናገራል፤ እንዲህም ይሆናል፤ እርሱ አፍ ይሆንልሃል፤ አንተም በእግዚአብሔር ፈንታ ትሆንለታለህ* አለው (ዘጸ. 4፥14-16)። ከላይ በተመለከትነው መሠረት "ነብይ" የእግዚአብሔር *"ቃል አቀባይ" (spokesman)* እንደሆነ እናያለን። አሮን የሙሴ "ቃል አቀባይ" እንዲሆን እግዚአብሔር እንደጠራው እናውቃለን።

2. የነብያት አገልግሎት ምንድነው?

"ብሉይ ኪዳን" ከሙሴ እስከ ሚልክያስ ድረስ የነበሩት ነብያት የጻፉትን መጽሐፍት ያጠቃለለ ነው። እነዚህ ነብያት የጻፉት ወደ ፊት ሊሆኑ ስለሚችሉ ነገሮች ብቻ ሳይሆን፥ ስላ ለፈውና በወቅቱ ይታይ ስለነበረውም ሁኔታ ጭምር ነበር። ነብይ በህልም፥ በራዕይ፥ ወይንም በንግግር እግዚአብሔር የገ ለጠለትን ራዕይ ለሕዝቡ ያስተላልፋል። እውነተኛ ነብይ እግዚ አብሔር እንዲናገር በአፉ ያደረገለትን መልዕክት ብቻ ይናገ ራል። የሚያስተላልፈውንም መልዕክት ሰው ሊገባው እንዲችል "በትምህርተ-ምሳሌ" የሚያስተላልፍበትም ጊዜ እንዳለ እናው ቃለን። በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ነብያት የሕዝቡን መንፈሳዊ ይዞታ የሚቆጣጠሩ ነበሩ። ሕዝቡ በወቅቱ ያለበትን መንፈሳዊ

ሁኔታ ከመረመሩ በኋላ፥ በኃጢአት ውስጥ ካሉ ንስሀ እንዲ ገቡ ይመክሯቸው ነበር። በአጠቃላይ ነብያት መመሪያ ይሰጣሉI ያስጠነቅቃሉI ይመክራሉI እንዲሁም የእግዚአብሔርን ተስፋ ለሕዝቡ ይገልጻሉ። ሕዝቡ እውነተኛ የልብ ለውጥ ሳይኖረው ሥርዓት ብቻ ሲሆን፥ ወይንም ታዛዥ ልብ ሳይኖረው መሥዋዕት ሲያቀርብ፥ ነብያት ፊት ለፊት ይገስጹትና ማስጠንቀቂያ ይሰጡት ነበር። ሕዝቡ ያለበትን የግብረ ገብ ኃላፊነት በመጥቀስ ቅድስናን ይሰብኩ ነበር። በማይታዘዙት፥ ወይንም በክፉዎች ላይ የሚደርሰውን ቅጣት፥ ንስሐ ገብተው ለሚመለሱት ደግሞ ወደፊት የሚያገኙትን የእግዚአብሔርን የፀጋ ስጦታ ያውጁ ነበር።

2.ሀ. የትንቢት ስጦታ ያላቸው የወደፊቱን ይተነብያሉ

ነብያት ከሚሰጡት አገልግሎት ውስጥ አንደኛው ወደ ፊት የሚሆነውን መተንበይ ነው። ማንኛውም "የትንቢት" አገልግሎት ወይንም ስጦታ ያለው ሰው እውነተኛነቱ ወይንም የተነበየው ትንቢት ትክክለኛ መሆኑና አለመሆኑ የሚለካበት መንገድ አለ። ያም "ነብይ ነኝ" የሚል አማኝ የሚተነብየው ትንቢት፥ በተለይ ስለ ወደ ፊቱ የተነበየ ከሆነ፥ ልክ እንደተነበየው የተፈጸመ እንደሆነ ነው። የተነበየው ትንቢት ሳይፈጸም ቢቀር ግን ያ ሰው የተነበየው ትንቢት ከእግዚአብሔር የመጣ ሳይሆን፥ ከሥጋ ወይንም ከሰይጣን መሆኑን እናውቃለን። *"በልብህም እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል እናውቅ ዘንድ እንዴት ይቻለናል? ብትል ነቢዩ በእግዚአብሔር ሰም በተናገረ ጊዜ የተናገረው ነገር ባይሆን፥ ባይመጣም፥ ያ ነገር እግዚአብሔር ያልተናገረው ነውI ነብዩ በድፍረቱ ተናግሮታልI እርሱን አትፍራው"* (ዘዳ. 18፥21-22)። የነብያትን እውነተኛነት መፈተን፥ ወይንም መመርመር፥ ትንቢትን መናቅ አይደለም። የምንለማ

ውን ሁሉ ሳንመረምር መቀበል እንደሌለብን መጽሐፍ ቅዱስ ይመክረናል። ሐዋርያው ዮሐንስ ስለ ሀሰተኛ ነብያት ሲያስጠነቅቀን እንዲህ ይላል *"ወዳጆች ሆይ! መንፈስን ሁሉ አትመኑI ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩI ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና"* (1 ዮሐ. 4፥1)። ይህን የመሰለ ማስጠንቀቂያ ከእግዚአብሔር ቃል በግልጽ ቢያነቡም፥ አንዳንድ ሰዎች ትንቢቱ በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ልክ ባይሆንም፥ ዝም ብለው ይቀበላሉ። በዚህ ምክንያት በግል ሕይወታቸውም ሆነ፥ እንዲሁም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ጉዳት የደረሰባቸው ብዙ ናቸው።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ "ነብያት" ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሱት፥ በሐዋ. 11፥27-28 ላይ ነው። *"በዚያም ወራት ነብያት ከኢየሩሳሌም ወደ አንጾኪያ ወረዱI ከነርሱም አጋቦስ የሚሉት አንድ ሰው ተነሥቶ በዓለም ሁሉ ታላቅ ራብ ሊሆን እንዳለው በመንፈስ አመለከተ..."* ይላል። በሌላ ጊዜ ይኸው ነብይ ሐዋርያው ጳውሎስ ስደት እንደሚያጋጥመው ተንብዮ ነበር። *"ወደ እኛም መጣና የጳውሎስን መታጠቂያ ወስዶ የገዛ እጁንና እግሩን አሰሮቶ እንዲሁ መንፈስ ቅዱስ ይህ መታጠቂያ ያለውን ሰው አይሁድ በኢየሩሳሌም እንደዚህ ያስሩታልI በአሕዛብም እጅ አሳልፈው ይሰጡታል ይላል አሉ"* (የሐዋ. ሥራ 21፥11)። የጳውሎስን ሕይወት ስንመረምር፥ ይህ አጋቦስ የተናገረው ትንቢት እንደ ተፈጸመ እናውቃለን።

2.ለ. ነብያት በወቅቱ ያለውን ሁኔታ ገልጸው ይናገራሉ

"ትንቢት" የሚለውን ቃል ስንሰማ ወደ አዕምሮአችን ቶሎ የሚመጣው "የወደፊቱን ማወቅ" ወይንም ስለ ወደፊቱ መናገር" የሚለው ሀሳብ ነው። ነብያት "የወደፊቱን ቢተነብዩም"፥ ወይንም "ወደ ፊት ስለሚሆነው" ነገር ቢናገሩም፥ አገልግሎታቸው ያ

ብቻ አይደለም። ስላለፈውና እንዲሁም በአሁኑ ጊዜ ስላለው ሁኔታም ገልጠው ይናገራሉ። አማኞች በወቅቱ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ያሉበትን ሁኔታ ማየት እንዲችሉ፥ ነብያት መን ፈሳዊ አቋማቸውን ገላልጠው ይናገራሉ። በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ነብያት፥ እስራኤልና ይሁዳ በወቅቱ ልባቸው ከእግዚአ ብሔር የሸፈተ መሆኑን ስላወቁ፥ ንስሐ ገብተው ካልተመለሱ፥ ወደ ፊት በሶርያና በባቢሎን እንደሚወረሩ ማስጠንቀቂያ ሰጥ ተዋቸው እንደነበር እናውቃለን። እንዲሁም ዮሐንስ መጥምቁ ሄሮድስ የወንድሙን ሚስት በማግባቱ በድፍረት ተሞልቶ *"የወ ንድምህን ሚስት ማግባት አልተፈቀደልህም"* (የሉቃ. 3፥19) በማለት የነቢይነት ተግባር እንደፈጸመ እናያለን። አጋቦስ ወደ ፊት ስለሚሆነው ነገር ትንቢት ይናገር እንጂ፥ በአዲስ ኪዳን ዘመን የነበሩት ነብያት ሁልጊዜ ወደ ፊት ስለሚሆነው ነገር ብቻ የሚተነብዩ አልነበሩም።

የነብያት ሌላው አገልግሎታቸው የእግዚአብሔርን ራዕይ (መገለጥ) ማወጅ ነው። ይሁዳና ሲላስ ነብያት ስለነበሩ፥ በመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን መማክርት ጉባኤ ላይ ተገኝ ተው ወንድሞችን በምክራቸው እንዳጸኑ እናውቃለን። *"ይሁዳና ሲላስም ደግሞ ነቢያት ነበሩና ወንድሞችን በብዙ ቃል መክረው አጸኑአቸው"* ይላል (የሐዋ. 15፥32)። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ብዙ ነብያት እንደነበሩ እናውቃለን። *"በአንጾኪያም ባለችው ቤተ ክርስቲያን ነቢያትና መምህራን ነበሩ..."* (የሐዋ. 13፥1) በማለት ስማቸውን ይዘረዝራል። በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ትንቢት የሚናገሩ ሴቶችም እንደነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገ ራል። ትንቢት የሚናገሩ ሴቶች ባይኖሩ ኖሮ *"...ራስዋን ሳት ሸፍን ግን የምትጸልይ፥ ወይም ትንቢት የምትናገር ሴት ሁሉ ራስዋን ታዋርዳለች"* (1 ቆሮ. 11፥5) ባላለም ነበር። ከብዙ ሴት ነብያት መካከል ከአሴር ወገን የነበረች የ84 ዓመት ዕድሜ የነበራት ሐና የምትባል ሴት ትገኛለች (የሉቃ. 2፥36)። ኢየ

ሱስ በሕጻንነቱ ወላጆቹ ወደ ቤተ መቅደስ ይዘውት በመጡበት ወቅት ይህቺው ሴት ቀርባ እግዚአብሔርን እንዳመሰገነች እና ውቃለን (የሉቃ. 2፥38)። ፊልጶስም *"ትንቢት የሚናገሩ አራት ደናግል ሴቶች ልጆች ነበሩት"* (የሐዋ. 21፥9)።

ሐዋርያው ጳውሎስ የትንቢት ዓላማ ምን እንደሆነ ለቆ ሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በጻፈው መልዕክት ላይ ይዘረዝራል። *"..ትንቢትን የሚናገር ግን ለማነጽና ለመምከር፥ ለማጽናናትም ለሰው ይናገራል"* (1 ቆሮ. 14፥3) ይላል። ጳውሎስ *"በሐዋር ያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል"* (ኤፌ. 2፥20) ሲል፥ ቤተ ክርስቲያን ነብያት ከእግዚአብሔር በሚቀበሉት የመገለጥ መልዕክት የምትታነጽ እንደሆነች እንረዳለን። ነብያት ከእግዚአብሔር የሚቀበሉትን መልዕክት ለሕዝቡ ያስተላልፋሉ። አንዳንድ ጊዜ መልዕክቱ በቀጥታ ከእግዚአብሔር ቃል የመነጨ ሊሆን ይችላል። ሐዋርያው ጴጥሮስ ብሉይ ኪዳን ውስጥ ያሉ ትን ነብያትን፥ እንዲሁም የሙሴን ሕግ እየጠቀሰ በመናገር ብዙዎች ወደ ንስሀ እንዲመጡ እንዳደረገ እናውቃለን (የሐዋ. 2፥3)። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ነብያት ከእግዚአብሔር የሚቀበ ሉት አዲስ የሆነ ራዕይ ወይንም መልዕክት ሊኖር ይችላል። አዲስ መገለጥን (ራዕይን) ይሰጣል ስንል፥ "ያለፈውን እየሻረ፥ ወይንም መጽሐፍ ቅዱስን እየተቃረነ ልዩ መልዕክት ይሰጣል" ማለታችን አይደለም። "አዲስ ራዕይ ከእግዚአብሔር ተቀብ ያለሁ" የሚል፥ የተቀበለው ራዕይ መጽሐፍ ቅዱስን የሚቃረን ከሆነ፥ ራዕዩ እውነትነት ስለሌለው ልንቀበለው አይገባም።

3. "ትንቢት" ምን ዓይነት ኃይልና ሥልጣን አለው?

እግዚአብሔር በሰዎች አንደበት የሚናገር መሆኑን ካመ ንን፥ በዘመናችን ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚናገሩት ትንቢት ምን ያህል ኃይልና ሥልጣን አለው? እውነተኛ ትንቢት

በመንፈስ ቅዱስ የተቀባና ከእግዚአብሔር የተላከ ቃል ከሆነ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ያለውን ዓይነት ኃይልና ሥልጣን አለው ማለት ነው? "የትንቢት ቃል" በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ ከሆነ፥ ነብዩ የሚናገረው እያንዳንዱ ቃል ሥልጣን አለው ማለት ነው?

ትንቢት፥ ስጦታው ያላቸው ሰዎች መንፈስ ቅዱስ ወደ አዕምሮአቸው የሚያመጣውን መልዕክት ሲናገሩ እንደ ሆነ ከላይ ገልጸናል። "የትንቢት ቃል" ክርስቲያኖች "በመለኮታዊ ስልጣን" የሚናገሩት ሳይሆን፥ እግዚአብሔር በልባቸው ያኖረውን ወይንም በአዕምሮአቸው ላይ ያስቀመጠውን "ሀሳብ" ሰሚዎች በሚገባቸው ቋንቋ ሲናገሩ ነው። "ትንቢት" አማኞች ልዩ የሆነ መገለጥ ከእግዚአብሔር ሲያገኙ የሚናገሩት ቢሆንም፥ "ከስህተት ሁሉ ነጻ ነው" ብለን ልንቀበለው አንችልም። ነብያት የሚናገሩት ትንቢት በከፊል እንጂ ሙሉ መልዕክት የያዘ እንዳልሆነ ጳውሎስ ይናገራል። *"...ከእውቀት ከፍለን እናውቃለንና፥ ከትንቢትም ከፍለን እንናገራለንና..."* (1 ቆሮ. 13፥9) ይላል። *"...ከትንቢት ከፍለን እንናገራለን"* ሲል፥ መልዕክቱ ሙሉ እንዳልሆነ እንረዳለን። "ትንቢት" ስጦታው ያለው ሰው የሚናገረው "የሰው ቃል" እንጂ፥ ቃል በቃል "መለኮታዊ" የሆነ አይደለም። ትንቢት ተናጋሪው የሚናገረው ትንቢት፥ የመልዕክቱን አጠቃላይ ሀሳብ ይዞ እንጂ "ቃል በቃል" አይደለም። ጳውሎስ *"ነቢያትም ሁለት ወይም ሦስት ሆነው ይናገሩ፤ ሌሎችም ይለዩአቸው"* (1 ቆሮ. 14፥29) ሲል፥ ትንቢት ከስህተት ፍጹም ነጻ እንዳልሆነ እናያለን። ስለዚህ በዘመናችን የሚነገሩትን ትንቢቶች ሁሉ፥ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር እኩል ልናደርጋቸው አንችልም። ይህንን ባለመረዳት አንዳንድ አማኞች፥ የእግዚአብሔርን ቃል ችላ ብለው ትንቢትን ብቻ ሲያሳድዱ ወይንም ሲፈልጉ እናያለን። የእግዚአብሔርን ቃል ከመቀበል ይልቅ ነብይ የሚነግራቸውን ሀሳብ መቀበል

የሚቀላቸው አሉ።

የዘመኑ የትንቢት ቃል መጽሐፍ ቅዱስን የማይተካ፥ ወይንም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እኩል እንዳልሆነ እንወቅ። ምክንያቱም፥

1) መጽሐፍ ቅዱስ አጠቃቀሙ ዓለም አቀፍ ነው። ትንቢት ግን ለተወሰነ ጊዜና ሁኔታ ብቻ ነው።

2) መጽሐፍ ቅዱስ ከስህተት ሁሉ ነጻ ስለሆነ በማንም አይፈተንምI ትንቢት ግን እውነተኛነቱ በእግዚአብሔር ቃል ይመረመራል (1 ቆሮ. 14፥29)።

3) መጽሐፍ ቅዱስ ስልጣን አለውI ትንቢት ግን "ለቅዱስ ቃሉ" ብቻ የተሰጠውን ኃይልና ሥልጣን አይዝም። ይሁን እንጂ፥ እውነተኛ ትንቢት ከሆነ፥ የክርስቶስን ፍላጎት የሚገልጽ ስለሆነ፥ ትንቢቱን አለመቀበልና አለመታዘዝ ስህተት ነው። ያልታዘዝነው ትንቢቱን የተናገረውን ሰው ሳይሆን፥ የትንቢቱን ቃል የሰጠውን ጌታ ነው። ስልጣኑ ያለው ስጦታው ባለው ሰው ላይ ሳይሆን፥ ስጦታውን በሰጠው ጌታ ላይ ነው።

4) መጽሐፍ ቅዱስ ዘላለማዊ ሲሆን፥ ትንቢት ግን ጊዜያዊ ነው።

4. የትንቢትን ስጦታ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምንለማመደው እንዴት ነው?

4.1. የትንቢት ስጦታ ያለው ሰው ስጦታውን መጠቀም ያለበት በትህትና፥ ወይንም ራስን ዝቅ በማድረግ መንፈስ ተሞልቶ እንጂ፥ ያለአግባብ ልዩ ኃይልና ሥልጣን እንዳለው አድርጎ ራሱን በማቅረብ አይደለም። በልቡ ውስጥ እግዚ

አብሔር ለሕዝቡ እንዲተላለፍ መልዕክት የሰጠው መስሎ የተሰማው አማኝ፥ "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" ባይልም፥ "እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነት መልዕክት በልቤ ውስጥ እንዳኖረ ይሰማኛል" ብሎ ቢያቀርብ ስህተት አይሆንም። እርግጥ ነው "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" ብሎ እንደሚያቀርበው መልዕክቱ ኃይለኛ መስሎ ላይታይ ይችላል። ይሁን እንጂ፥ መልዕክቱ በእርግጥ ከእግዚአብሔር ከሆነ፥ መሰማት ላለባቸው ሰዎች ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በኃይል ይናገራል።

4.2. የትንቢት ስጦታ ያለው ሰው ስጦታውን መጠቀም ያለበት በፍቅር ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 13 ላይ ማንኛውም ስጦታ ፍቅር ከሌለበት ዋጋ ቢስ እንደ ሆነ በሰፊው ጽፏል። ዋጋ ቢስ የሚሆነው "ስጦታው" ሳይሆን፥ ስጦታው አለኝ የሚለው አማኝ ነው። *"...ትን ቢት ቢኖረኝ ... ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ"* (1 ቆሮ. 13፥2)። ፍቅር የሌለው ሰው ተናግሮን መነዳትን የቀ መስን ሰዎች፥ በፍቅር ያልተቀመመ ትንቢት ምን ያህል ጎጂ እንደሆነ መረዳት አያቅተንም። አንድ አማኝ የትን ቢት ስጦታ አለኝ ብሎ የአንዳንድ ደካማ ሰዎችን አዕምሮ ለመጠምዘዝ፥ ወይንም የቤተ ክርስቲያን መሪዎቹን ወደ ራሱ ለመሳብ ትንቢትን ቢጠቀም፥ ያ ትንቢት ሀሰተኛ ትንቢት እንደ ሆነ ለመረዳት አያስቸግርም። *"እነሆ! ሐሰ ትን በሚያልሙት በሚናገሩም በሐሰታቸውና በድፍረታ ቸውም ሕዝቤን በሚያስቱ በነቢያት ላይ ነኝ ይላል እግ ዚአብሔርI እኔም አልላክኋቸውምት አላዘዝኋቸውም ለእነዚህም ሕዝብ በማናቸውም አይረቡአቸውምት ይላል እግዚአብሔር"* (ኤር. 23፥32)።

4.3. የትንቢት ስጦታ ያለው ሰው እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ስጦ ታውን ለመጠቀም ከፈለገ፥ ከእርሱ በላይ ሥልጣን ላላቸው ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ራሱን ማስገዛት የሚ ችል መሆን አለበት። አንዳንድ የትንቢት ስጦታ አለን የሚሉ አማኞች ራሳቸውን ከፍ አድርገው ስለሚያዩና ስለሚያቀርቡ፥ ራሳቸውን ማስገዛትና መታረም አይፈል ጉም። ይህንን ስንል አልፎ አልፎ ነብዩ በፍቅር የቤተ ክርስቲያን መሪውን አይመክርም፥ ለመሪዎች የሚሆን የትንቢት ቃል አያመጣም ማለት አይደለም። ነብዩ ናታን፥ ዳዊት በሳተበት ጊዜ በጥበብ ቀርቦ እግዚአብሔር እንዲያ ስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት ለዳዊት እንዳስተላለፈ እናውቃለን። የትንቢት ስጦታ ያለው ሰው መልዕክቱን ለሚመለከተው ሰው ሲያስተላልፍ በትዕቢት፥ "እኔ ከሁሉም ሰው በላይ ነኝ" በሚል ስሜት ሳይሆን፥ ራሱን ዝቅ በማድረግና ራሱን በማስገዛት መሆን አለበት። አንዳንድ የትንቢት ስጦታ አለን የሚሉ አማኞች ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ራሳችንን አናስገዛም ብለው ሲያስቸግሩ ማየት በዘመናችን አዲስ ነገር አይደለም። "ነብይ ነኝና ምክርና ትዕዛዝ ከማንም አልሰማም" ለሚሉት አማኞች ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሰጠ ውን ሥልጣን ማወቅ እንዳለባቸው ሲጽፍ እንዲህ ይላል *"ማንም ነቢይ ወይም መንፈሳዊ የሆነ ቢመስለውት ይህች የጻፍሁላችሁ የጌታ ትእዛዝ እንደ ሆነች ይወቅI ማንም የማያውቅ ቢኖር ግን አይወቅ"* (1 ቆሮ. 14፥37-38)።

4.4. የትንቢት ስጦታ ያለው ሰው ስጦታውን ሲጠቀም ራሱን በመቆጣጠር መሆን አለበት። ጳውሎስ *"የነቢያትም መና ፍስት ለነቢያት ይገዛሉ"* ይላል (1 ቆሮ. 14፥32)። "የነቢያትም መናፍስት ለነቢያት ይገዛሉ" ሲል፥ የትን ቢቱን ቃል ሲያስተላልፍ አዕምሮውን ስቶ፥ ወይንም

ከቁጥጥር ውጪ ሆኖ አይደለም ማለቱ ነው። አንዳንድ የትንቢት ስጦታ አለን የሚሉ ክርስቲያኖች፥ ሲተነብዩ ያለ አግባብ ሲንቀጠቀጡ፥ መሬት ላይ ሲንከባለሉ፥ በስ ብከት መካከል ተነስተው ትንቢት ሲተነብዩ ይታያሉ። አንዳንዶቹ ከላይ በገለጽነው ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ካል ሆኑ፥ የሚተነብዩትን ትንቢት ሰዎች የማይቀበሉ መስሎ ይሰማቸዋል። መንቀጥቀጡም ሆነ መሬት ላይ መንከባለሉ፥ "ትንቢቱን" ኃይለኛ አያደርገውምI ወይንም ትንቢት ተናጋሪው "የበለጠ መንፈሳዊ ነው" አያሰኘውም። "የነብ ያት መናፍስት ለነቢያት" ይገዛሉ ሲል፥ ነብዩ ራሱን መቆጣጠር ይችላል ማለቱ ነው። በኃይል ገፍቶ መሬት ላይ አያንከባልለውምI ወይንም መልዕክቱ አፉን ፈልቅቆ ተናጋሪው ሳይፈልግ በኃይልና በግድ አይወጣም። ስለዚህ ትንቢት የሚናገሩ ሰዎች ራሳቸውን መግዛት ስለሚችሉ፥ መወራጨት፥ መሬት ለመሬት መንከባለል፥ ያለአግባብ መጮህ አያስፈልጋቸውም። የነብዩ መንፈስ፥ ለነብዩ ይገዛል።

5. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊያውቁት የሚገባ እውነት

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ትልቁ ኃላፊነታቸው፥ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ያሉት ምዕመናን መንፈስ ቅዱስ የሰጣቸውን ስጦታ ለይተው እንዲያውቁ፥ እንዲሁም ሌሎችን ለማነጽ ስጦ ታቸውን በአግባቡና በሥርዓቱ እንዲጠቀሙና እንዲለማመዱ ማስተማር ነው። የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ በደንብ እንዲታይ፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጤናማ ብልቶች ያሉት አካል መገንባትና እንዲሁም በምዕመናኑ መካ ከል በመንፈስ ቅዱስ ስም የሚፈጠረውን ሁከትና ረብሻ መስመር ማስያዝ መቻል አለባቸው። ቅዱስ የሆነ መንፈሳዊ ሥርዓት፥

ተራው ዓለም መስማት የሚወደውን፥ የእግዚአብሔር ቃል የሚደግፈውን በፍቅር የተሞላውን አንድነት ይፈጥራል። *"እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ"* (የዮሐ. 13፥35) ይላል። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን፥ በተለይ "የትንቢት ስጦታን" በአግባቡ ለመጠቀም፥ ጥሩ መንፈሳዊ መሪ ያስፈልጋል። ይሁን እንጂ፥ ኃላፊነቱ ቀላል አይደለም። የትንቢት ስጦታ ያላቸውን ጠበቅ አድርጎ ከያዘ፥ አንዳንዶቹ የማይፈለጉና የማይወደዱ፥ ስጦታቸ ውን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳይለማመዱ የሚከለክሉ መስሎ ይሰማቸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ላላ ካሉ፥ ቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ሥርዓት ስለሚጠፋ፥ ብዙ ሁከትና ረብሻ ይፈጠራል። አንዳንድ ከሥርዓት ውጪ የሆነውን ልምምድ የሚመለከቱ ክርስቲያኖች ደግሞ ትንቢትን በአጠቃላይ መቀበል ያቅታቸ ዋል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊያውቁት የሚገባ እውነት፥

5.1. የትንቢት ስጦታን ችላ ማለት የለባቸውም

ጳውሎስ "ትንቢት" ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጠውን አገ ልግሎት በመጥቀስ አማኞች ትንቢትን እንዲናገሩ ያደፋፍራል። ትንቢት የሚያምኑትን ብቻ ሳይሆን፥ የማያምኑትንም ይወቅሳልI ይመረምራልI እንዲሁም በልባቸው የተሰወረውንም ይገልጣል። *"...ሁሉ ትንቢት ሲናገሩ ግን የማያምን ወይም ያልተማረ ሰው ቢገባ፥ በሁሉ ይወቀሳልI በሁሉም ይመረመራልI በልቡም የተሰወረ ይገለጣል..."* ይላል (1 ቆሮ. 14፥24)። የትንቢት ስጦታ የተሰጠው በሐዋርያት ዘመን ብቻ ሳይሆን፥ በእኛም ዘመን ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽበት መንፈስ ቅዱስ ለምዕ መናን ይህን የጸጋ ስጦታ እንደሚሰጥ እንወቅ። ጳውሎስ ለቆ ሮንቶስ ምዕምናን ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ ሲገልጽላቸው፥ እነዚህ ስጦታዎች በእነርሱ ዘመን ብቻ ሳይሆን፥ ክርስቶስ

ዳግመኛ እስኪመለስ ድረስ እንደሚሠራ በማመን ነው። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፥ ማኅበሩ እንዲታነጽበት የትንቢት ስጦታ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአግባቡ እንዲሠራ ማደፋፈር እንጂ፥ ችላ ማለት አይገባቸውም።

5.2. ስለ "ትንቢት ስጦታ" ምዕመናኑን ማስተማር አለባቸው

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁከትና ረብሻ የሚፈጠረው ብዙ ጊዜ ምዕመናኑ በቂ ትምህርት ስለማይሰጣቸው ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የማስተማር ተግባራቸውን ችላ ሲሉ፥ ምዕመናን ካላቸው መንፈሳዊ ጥማት የተነሳ፥ ሳያውቁት አንዳንድ ትክክል ያልሆኑ ትምህርቶችን ከውጪ መቃረም ይጀምራሉ። የበሰለ መሪ ከሌለበት ከአንዳንድ ስብሰባዎች ላይ በመገኘት መጽሐፍ ቅዱስ ከሚለው ውጪ አዳዲስ ልምምዶችንና ትምህርቶችን ተምረው ይመጣሉ። እንዲሁም የጸሐፊዎቹን ማንነትና ያላቸውን የእምነት አቋም በትክክል ባለመረዳት፥ አንዳንድ ጤናማ ያልሆኑ መጽሐፎችን በማንበብ፥ የተሳሳተ ትምህርቶችን መሰብሰብ ይጀምራሉ። ብዙዎቹ በተሳሳተ ትምህርት ውስጥ አንዴ ከገቡ፥ ከዚያ ለመውጣት ፈቃደኞች አይሆኑም። ከስህተታቸው ሊመልሳቸው ከሚሞክረውም ሰው ጋር ይጋጫሉ።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች "በትንቢት ስጦታ" ምክንያት ምዕመኖቻቸው እንግዳ ትምህርት ውስጥ እንዳይገቡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ትንቢት የሚናገረውን በጥንቃቄና በትጋት ማስተማር አለባቸው። "የትንቢት ስጦታ" የጸጋ ስጦታ እንጂ፥ ማንኛውም ሰው እየተነሳ እንደ ልቡ "ከሕገ-ተፈጥሮ-ውጭ" (psychic) በሆነ ሁኔታ የወደፊቱን የሚናገርበት እንዳልሆነ፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መጽሐፍ ቅዱስ እየጠቀሱ ማስተማር አለባቸው። ሰዎች በግል ያላቸውን ልምምድ ከመናገር ይልቅ፥ መጽሐፍ

ቅዱስ ስለ "ትንቢት ስጦታ" የሚናገረውን እየጠቀሱ ቢያስተምሩ፥ ብዙዎች ስጦታውን እንዳይጠራጠሩ ይረዳቸዋል።

5.3. ምዕመናኑ "የትንቢት ስጦታን" እንዲመኙ ማደፋፈር አለባቸው

ሐዋርያው ጳውሎስ *"...መንፈሳዊ ስጦታንም ይልቁንም ትንቢት መናገርን በብርቱ ፈልጉ"* (1 ቆሮ. 14፥1) በማለት ይመክራል። በዚህ ቃል መሠረት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምዕመኖቻቸው ይህንን ስጦታ በብርቱ እንዲፈልጉ ማደፋፈር አለባቸው። ጳውሎስ *"..እያንዳንዳችሁ ትንቢት ልትናገሩ ትችላላችሁ"* (1 ቆሮ. 14፥31) ሲል፥ ሌላ ጊዜ ደግሞ *"...ሁሉስ ነቢያት ናቸውን?..."* (1 ቆሮ. 12፥29) ብሎ ይጠይቃል። እነዚህ ሁለት ሀሳቦች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስላሉ። ይሁን እንጂ፥ የሚቃረኑ አይደሉም። አንደኛው ሀሳብ *"የትንቢት አገልግሎት"* ሲሆን፥ የትንቢት አገልግሎት ያላቸው አማኞች "በነብይነት" የታወቁ ናቸው። *"የትንቢት አገልግሎት"* የሚኖራቸው የተወሰኑ አማኞች እንጂ፥ ሁሉም አይደሉም።፥ ሁለተኛው ግን *"የትንቢት ስጦታ"* ነው። የትንቢት ስጦታ በመንፈስ ቅዱስ ስንሞላ ለብዙዎች ሊሰጥ የሚችል ነው። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ *"...እያንዳንዳችሁ ትንቢት ልትናገሩ ትችላላችሁ"* እንዲሁም *"...ይልቁንም ትንቢት መናገርን በብርቱ ፈልጉ"* (1 ቆሮ. 14፥1) ያለው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በዚህ ቃል መሠረት ምዕመናን "የትንቢት ስጦታን" እንዲመኙ ማደፋፈር አለባቸው።

5.4. ትንቢትን መመርመር አለባቸው

ሐዋርያው ጳውሎስ *"...ትንቢት መናገርን በብርቱ ፈልጉ"* (1 ቆሮ. 14፥1) በማለት ማደፋፈር ብቻ ሳይሆን፥ አልፎ አልፎ የስህተት ትንቢት ሊኖር ስለሚችል ትንቢትን ሁሉ መመርመር

እንዳለብን ይመክረናል። *"መንፈስን አታጥፉ፥ ትንቢትን አትናቁ፤ ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ"* (1 ተሰ. 5፥19-21) ይላል። የትንቢት ስጦታ ያላቸው አማኞች የሚናገሩት ትንቢት መመርመር አለበት። በአምልኮት ወቅት ሁሉም እየተነሳ ትን ቢት ከተናገረና ትንቢቱ በየጊዜው ካልተመረመረ፥ ሰዎች ልባ ቸው ይደነድንና ለትንቢት ስጦታ ያላቸው አስተያየት በጣም ይቀንሳል። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በአንድ የአምልኮት ስብሰባ ላይ ምን ያህል ሰው የትንቢትን ቃል መስጠት እንዳለ በት ወስኖ የተናገረው። *"...አቢያትም ሁለት ወይም ሦስት ሆነው ይናገሩ..."* (1 ቆሮ. 14፥29) ይላል። ትንቢቱ ትክክል መሆኑን መመርመር ያለባቸው ሌሎች የትንቢት ስጦታ ያላቸ ውና እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ናቸው። ትንቢት ተናጋሪው ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ የሆነ መልዕክት ሲያቀ ርብ፥ ወይንም በሥጋው ሲናገር፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጥበብ ተናጋሪውን ማረምና ለምዕመናኑም የሰሙት ትንቢት ልክ እንዳልሆነ ማሳወቅ አለባቸው።

አልፎ አልፎ በዘመናችን የምንሰማቸው ትንቢቶች አን ዳንዶቹ ከሥጋ የሚወጡ እንደሆኑ ለይቶ ማወቅ ይህን ያህል ከባድ አይደለም። ከረጅም ዓመታት በፊት አንዳንድ እንግዳ ትምህርቶች በአገራችን በየቤቱ ብቅ ማለት ሲጀምሩ፥ በወቅቱ የነበርነው መሪዎች ሁኔታውን ለማስተካከል የአዳር ጸሎት ወደ ሚደረግበት ቤት ሄድን። አምልኮቱ እንደተጀመረ፥ ስብሰባውን ይመሩ ከነበሩት ወንድሞች መካከል አንደኛው ትንቢት በእኛ ላይ መናገር ጀመረ። ትንቢቱም *"እናንተ ልጆቼን ልትበጠብጡ የመጣችሁ፥ ተጠንቀቁ ይላል የሠራዊት ጌታ"* የሚል ነበር። በትንቢቱ እየተደነቅን ሳለን፥ ሌላ ሁለተኛ የሚያስደንቀን ትን ቢት መጣ። ሁለተኛው ትንቢት ከአርሱ አቅጣጫ ሳይሆን፥ ከእኛው ከመሪዎቹ መካከል፥ የትንቢት ስጦታ አለኝ ከሚል ወንድም ነበር። ትንቢቱም፥ *"ልጆቼን የምትበጠብጡ እናንተ*

ራሳችሁ ናችሁ እንጂ ሌላ ሰው አይደለም ይላል የሠራዊት ጌታ" የሚል ነበር። በዚህ ዓይነት መጀመሪያ ለተተነበየው ትንቢት አስፈላጊውን ዓይነት መልስ ሰጠ። ሁለቱም ነብያት መልዕክቱ መጣ ያሉት "ከሠራዊት ጌታ" ነበር። ታዲያ የሠራ ዊት ጌታ ራሱን ይቃረናል? ወይንስ ሁለት ዓይነት የሠራዊት ጌታ ስላለ ነው። ይህን ዓይነቱ ትንቢት ከሥጋ የመነጨ እንደ ሆነ መለየት ይህን ያህል ከባድ አይደለም። በሌላ ሥፍራ ደግሞ አንዱ ሲተነብይ፥ *"የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥ አብርሃም ልጆቼን በቀይ ባህር ውስጥ እየመራ እንዳወ ጣቸውና እኔም እናንተን ካሳችሁበት ችግር አወጣችኋለሁ"* አለ። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ፥ መሳሳቱን ተገንዝቦ ቀደም ሲል ለተናገረው ትንቢት ማረሚያ እንዲሆን ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ *"የሠራዊት ጌታ እንዲህ ይላል፤ ተሳስቻለሁ፥ አብርሃም ሳይሆን፥ ሙሴ ነው"* አለ። እንዲህ ዓይነቱ ትንቢት ያስቃል እንጂ፥ ይህን ያህል የአማኞችን እምነት የሚያናውጥ፥ ወይንም ከፍተኛ ስህተት ላይ የሚጥል እንዳልሆነ እናውቃለን። ይሁን እንጂ፥ ይህን ዓይነቱ ሁኔታ ሲደጋገም፥ "የትንቢት ስጦታን" ብዙ ዎች ክብደት እንዳይሰጡት ወይንም ችላ እንዲሉት ስለሚያ ደርግ፥ ይህን ዓይነት ስህተት እንዳይደረግ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

በዘመናችን "በትንቢት ስጦታ" ምክንያት ትልቅ ሁከት በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ ሲፈጠር እናያለን። አንዳ ንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔርን ሕዝብ በቃሉ በመምራት ፈንታ "በትንቢት" ሊመሩት ሲሞክሩ እናያለን። ሽማግሌና ዲያቆናት የሚመረጡት በትንቢት ነው። መጋቢ የሚሾሙት፥ ወይንም መጋቢውን ከቤተ ክርስቲያን የሚያባርሩት በትንቢት ነው። የሚያጋቡትና የሚያፋቱትም በትንቢት ነው። "እከሌን የኑሮ ጓደኛሽ እንዲሆን ሰጥቼሻለሁ..." ሲላት፥ ትን ቢቱን መጠራጠር እግዚአብሔርን መጠራጠር ስለሚመስላት ልቧ ያልፈቀደውን ሰው ታገባለች። ወይንም "እከሌን ያገባሽው

ያለእኔ ፈቃድ ነውና እርሱን ፍቺና እኔ የማዘጋጅልሽን በእም ነት ጠብቂ" ሲላት፥ "ትንቢት" ከስህተት ሁሉ ነጻ ነው ብላ ስለምታምን፥ የሞቀ ትዳሯን ታፈርሳለች። የሰውን ሕይወት ምስ ቅልቅል የሚያደርጉ፥ የእግዚአብሔርን ቤት የሚያውኩ ሀሰተኛ ነብያት በዘመናችን ቁጥራቸው እየጨመረ ነው።

የዘመኑ አማኞች የእግዚአብሔር ቃል ሳይሆን ትንቢት የጠማቸው ናቸው። ይህንን የተረዱ ብልጣብልጦች፥ ለመቀመ ጣቸውና ለመነሳታቸው ሁሉ ትንቢት ይተንብዩላቸዋል። መን ፈስ ቅዱስ "የትንቢት ስጦታን" ለቤተ ክርስቲያን የሰጠው የእግዚአብሔርን ሕዝብ፥ እንድንመራበትና እንድናስተዳድርበት፥ ወይንም የእግዚአብሔርን ቃል እንዲተካ አይደለም። አንዳንዶች ትንቢት ከስህተት ሁሉ ነጻ ነው *(infallible)* ብለው ስለሚያ ምኑ፥ በግልጽ የእግዚአብሔርን ቃል የሚቃወም ትንቢት እን ኳን ሲሰሙ፥ ያለምንም ጥያቄና ጥርጣሬ "አሜን" ብለው ይቀበላሉ። በዚህ ምክንያት ራሳቸውን ትልቅ ችግር ውስጥ ይከታሉ። ሀሰተኛ ነብያት ዛሬ ብቻ ሳይሆን ጥንትም ነበሩ። *"... ትንቢታችሁ ከንቱ፥ ራእያችሁም ሐሰት ስለሆነ በእናንተ ላይ በቁጣ እነሣለሁ። እናንተ የሐሰት ራእይ የምታዩና ግራ የሚያጋባ ትንቢት የምትናገሩ ነቢያት ከእኔ ቅጣት አታመልጡም"* ይላል (ሕዝ. 13፥8-9)። እውነተኛ ነብያት እንዳሉ ሁሉ፥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከመስመር ሊያስወጡ የሚችሉ፥ እግዚአብሔር ተናገሩ ሳይላቸው የሚናገሩ፥ ሀሰተኛ ነብያትም አሉ። እንደነዚህ ዓይነቶቹን እንዴት ለይተን እናውቃለን? መልሱን ከእግዚአብሔር ቃል እናገኛለን። *"አንድ ነቢይ የሚ ናገረው የትንቢት ቃል ከእግዚአብሔር ያልተሰጠ መሆኑን በምን ለይተን እናውቃለን?"* በማለት ትደነቁ ይሆናል። *"አንድ ነቢይ በእግዚአብሔር ስም ትንቢት ተናግሮ ትንቢቱ ሳይፈጸም ቢቀር ያ ትንቢት ከእግዚአብሔር የተሰጠ አይደለምI ያም ነቢይ ትንቢቱን የተናገረው በገዛ ሥልጣኑ ስለ ሆነ ልትፈሩት*

አይገባም" ይላል (ዘዳግም 18፥21-22)። እንዲህ ዓይነቱንም እግዚአብሔር እንደሚቀጣው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። *"ነገር ግን ሌላ ነቢይ እኔ ሳላዘዘው በስሜ ትንቢት ለመናገር ቢደፍር በሞት ይቀጣልI እንዲሁም በባዕዳን አማልክት ስም ትንቢት ለመናገር የሚሞክር ማናቸውም ነቢይ እንዲሁ በሞት ይቀጣል"* (ዘዳግም 18፥20)።

☆ ☆ ☆ ☆



የወንጌል ሰባኪነት ስጦታ

"...አንዳንዶቹ የወንጌል ሰባኪዎች...እንዲሆኑ ስጦታዎችን ሰጠ...።"
(ኤፌሶን 4፥11)

"የወንጌል ሰባኪነት" ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መካከል አንደኛው እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። *"እርሱም አን ዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ"* (ኤፌሶን 4፥11) ይላል። በስብከት አማካኝነት ከተመሠረቱትና ከአደጉት የዓለም ሃይማኖቶች መካከል አንደኛው የክርስትና ሃይማኖት ነው። ይሄም የሆነበት ዋናው ምክንያት አማኞች ሁሉ *"በታላቁ ተልዕኮ"* ውስጥ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ክርስቶስ ስላዘዘ ነው። ክርስቶስ ወደ አብ ለመጨረሻ ጊዜ ከመሄዱ በፊት ደቀ መዛሙርቱን *"ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረታት*

ሁሉ ስበኩ" (የማር. 16፥15) ብሎ እንዳዘዛቸው እናስታው ሳለን። *"ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ"* ሲል፥ ይህ የወንጌል መልዕክት ለሁሉም እንዲደርስ መፍቀዱን ያሳያል። ደቀ መዛሙርቱን ያዘዘው ሀብታም፥ ድሃ፥ የተማረ፥ ያልተማረ፥ አይሁድ ወይንም አህዛብ በማለት ሰው ሳይመርጡ ለሁሉም እንዲሰብኩ ነው (ሮሜ 3፥29፣ ገላት. 3፥28)። መላው ዓለም የምሥራቹን ቃል መስማት ስላለበት፥ በሁለት ዓይነት መንገድ እንዲሰራጭ አደረገ።

እንደኛው፥ አማኝ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝ እንደሆነ እንዲመሰክር ትዕዛዝ በመስጠት ነው። *"...መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፤ በዚያን ጊዜ በኢየሩሳሌም፥ በይሁዳ አገር ሁሉ፥ በሰማርያ፥ እስከ ምድርም ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ"* (የሐዋ. 1፥8) ይላል። ይህ ትዕዛዝ የሚመለከተው የተወሰኑትን ጥቂት ሰዎች ብቻ ሳይሆን፥ በጠቅላላው አማኞችን ሁሉ ነው። ኢየሱስ *"...በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፤ በሰው ፊትም የሚክደኝን ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ"* (የማቴ. 10፥ 32-33) ሲል እያንዳንዱ አማኝ ስለ ክርስቶስ አዳ ኝነት መመ ስከር እንዳለበት እንረዳለን።

ሁለተኛው፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በዓለም ዙሪያ እን ዲሰራጭ ያደረገበት መንገድ፥ የወንጌል ሰባኪነትን ስጦታ ለአ ንዳንድ አማኞች በመስጠት ነው። ጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ሲዘረዝር፥ *"... አንዳንዶቹ ወንጌል ሰባኪዎች እን ዲሆኑ ሰጠ"* ይላል (ኤፌ. 4፥11)። *"ወንጌል ሰባኪዎች"* የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው ሦስት ጊዜ ብቻ እንደሆነ እናውቃለን (የሐዋ. 21፥8፥ ኤፌ. 4፥11፥ 2ኛ ጢሞቴዎስ 4፥5)። በአዲስ ኪዳን ውስጥ "ወንጌላዊ" ተብሎ የተጠራ ፊልጶስ ብቻ ነው። *"...ከሰባቱ ዲያቆናት አንዱ ወደ*

ሆነው ወደ ወንጌላዊው ፊልጶስ ቤት ገብንና ከእርሱ ጋር ተቀመጥን...” (የሐዋ. 21፥8)። ማንኛውም አማኝ ወንጌል ላልዳኑት ሰዎች እንዲደርስ ኃላፊነት ተሰምቶት ይመስከር እንጂ፥ አማኞች ሁሉ *“የወንጌል ሰባኪነት”* ስጦታ አላቸው ማለት እንዳልሆነ እናውቃለን። ፒተር ዋግነር “የወንጌል ሰባኪነት” ስጦታ ምን እንደሆነ ሲገልጹ *“የወንጌል ሰባኪነት ስጦታ እግዚአብሔር ለአንዳንድ አማኞች ወንጌልን፥ የክርስቶስን አዳኝነት ላልዳኑት ሰዎች በመስበክ ወደ ደህንነት እንዲመጡና የክርስቶስ ደቀ መዝሙር እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችላቸው ስጦታ ነው”* አሉ። ሌሰሊ ፍላየን የተባሉ ጸሐፊ ደግሞ *“ወደ ደህንነት የሚያመጣውን የምሥራቹን ቃል ላልዳኑት ሰዎች ጥሩ አድርገው በመስበክ፥ ወደ ክርስቶስ ማምጣት የሚችሉበት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው”* አሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ “ወንጌላዊ” ብዙ ባይናገርም፥ ስለ “ወንጌል ስብከት” ግን በሰፊው ይናገራል። *“ወንጌላዊ”* የሚለው ቃል፥ *“ወንጌል”* ወይንም *“የምሰራች ቃል”* ከሚለው የወጣ ነው። ጳውሎስና ጴጥሮስ ሐዋርያት፥ ጢሞቴዎስና ቲቶ፥ የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች፥ አጋቦስ ደግሞ ነብይ እንደነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። *“የወንጌል ሰበካ”* ሥራን በዚያን ወቅት ይሠሩ የነበሩት ተራ አማኞች ነበሩ። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ *“ወንጌላዊ”* ተብሎ ይጠራ የነበረው ፊልጶስ ብቻ እንደ ነበረ እናውቃለን። ፊልጶስ ለዲቁና ከተመረጡት ሰባት ሰዎች መካከል አንደኛው ሰው ሲሆን፥ በዚያን ጊዜ በድቁና አገልግሎቱ ላይ በተጨማሪ “የወንጌል ሰባኪነት” አገልግሎት ይሰጥ እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርም። ይሁን እንጂ፥ ፊልጶስ በታማኝነት ማዕድን እያገለገለ የተከፈተ በር ሲያጋጥመው፥ ወንጌልን ይሰብክ እንደ ነበረ እንገምታለን። *“ፊልጶስም ወደ ሰማርያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው“ (የሐዋ. 8፥1)* ይላል።

ፊልጶስና እንዲሁም ሌሎች አማኞች የክርስቶስን አዳኝነት በመመስከራቸው ምክንያት፥ ብዙዎች ወደ ክርስትና እምነት ይመጡ ነበር። ይሄን ዓይነቱ እንቅስቃሴ ያላስደሰታቸው የሃይማኖት መሪዎች፥ በክርስቲያኖች ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ አስነሱባቸው። በዚያን ጊዜ ነው *የተርሴሱ* ሳውል ክርስቲያኖችን ለማሳደድ ታጥቆ የተነሳው። የመጀመሪያው ሰማዕት እስጢፋኖስም በድንጋይ ተወግሮ የሞተው በዚያን ወቅት ነው (የሐዋ 7)። በወቅቱ የነበረው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ባየለ ቁጥር፥ በክርስቲያኖች ላይ የሚደርሰው መከራና ስደትም በዚያው መጠን ይበረታ ነበር። አንዳንዶቹ ከመከራው ለማምለጥ ኢየሩሳሌምን እየለቀቁ በመውጣት በይሁዳና በሰማርያ መኖር ጀመሩ። የሚያስደንቀው በሄዱበት ሥፍራ ሁሉ አርፈው በመቀመጥ ፈንታ፥ ቃሉን በድፍረት ይሰብኩ ነበር። የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ስምንትን ስናነብ፥ ሐዋርያቱ ግን ኢየሩሳሌምን ለቀው እንዳልወጡ እንረዳለን።

1. ወንጌል ሰባኪነት ምንድነው?

(ሀ) ወንጌልን በቃላት ማወጅ ነው

“የወንጌል ሰባኪነት” ስጦታ ዋና ዓላማ የማያምኑትን ሰዎች የወንጌልን ቃል በመንገር ከክርስቶስ ጋር እንዲታረቁና እንዲሁም ከተቀሩት አማኞች ጋር የተቀራረበ አንድነት ወይንም ግንኙነት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። ይህንንም ለማድረግ ወንጌልን በቃላት መግለጽ ወይንም ማወጅን ይጠይቃል። ወንጌል ባልተሰበከባቸው ሥፍራዎች፥ ክርስቲያኖች በማያምኑት ሰዎች መካከል በመኖር በክርስትና ሕይወት አኗኗራቸው ብቻ መመስከር ይበቃል የሚሉ ሰዎች አሉ። “ቅዱስ የሆነ አኗኗር በመኖር ክርስቶስን ለማያምኑት ሰዎች ማስተዋወቅ እንችላለን”

በማለት የወንጌል ሰበካውን አገልግሎት ችላ የሚሉ የሃይማኖት ክፍሎች እንዳሉ እናውቃለን። *"የወንጌል ሰባኪነት"* ስጦታ፥ በሕይወት ብቻ ሳይሆን በቃላትም መግለጽን ይጠይቃል። በሽ ተኞችን ማከም፥ የተራቡትን መመገብ፥ የተራቆቱትን ማልበስ፥ ከወንጌል ሰበካ ጋር እኩል ነው፥ ወይንም የወንጌል ሰበካን ይተካል የሚሉ ክፍሎች አሉ። ከላይ የጠቀስናቸው አገልግሎቶች መልካም ቢሆኑም፥ ወንጌልን በቃላት ከመግለጽ ጋር ይመሳሰላሉ ወይም እኩል ናቸው አንልም። ጌታን የማያውቁ ብዙ በጎ አድራጊዎች አሉ። የማያውቁትን ወንጌል እየሰበኩ ነው ማለት አንችልም። *"የወንጌል ሰባኪነት ስጦታ"* በቃላትና እንዲሁም በተግባር የሚገለጽ ነው። ማንኛውም ሰው ከእግዚአ ብሔር ጋር እንዴት መታረቅ እንደሚችል በሚገባው ቋንቋ ሊገለጽለት ይገባል። የክርስቶስ የምሥራቹ ቃል፥ ሞትና ትንሳኤው እንዲሁም ቤዛነቱ በቃላት ሊገለጽ ይገባል። *"የወንጌል ሰባኪነት"* ስጦታ፥ በንግግር ከሚገለጹ ስጦታዎች መካከል አንደኛው ነው። ወንጌል በቃላት ሳይገለጽለት፥ የሌሎችን መልካም ሕይወት በማየት ብቻ ደህንነትን ያገኘ ሰው የለም። እር ግጥ ነው የክርስቲያኖች የተቀደሰ ሕይወት፥ አማኝ ያልሆኑ ሰዎች ወንጌልን እንዲሰሙ ልባቸውን ያዘጋጃል። ነገር ግን ብቻውን ማንንም ወደ ክርስቶስ አያመጣም። ለዚህ ነው የወንጌል ሰበካ "በቃል ማወጅ" የሚያስፈልገው።

(ለ) የወንጌል ሰበካ "መልካም ዜና" ያለበት ነው

"ወንጌል" የሚለው ቃል ከግሪክ የመጣ ቃል ሲሆን፥ ትርጉሙም "መልካም ዜና" ወይንም "የምሥራች" ማለት ነው። "የወንጌል ሰባኪነት" ስጦታ ያለው ሰው፥ "የምሥራቹን ቃል" አብሳሪ ነው። መልካም ዜና ምንድነው? በታሪክ ውስጥ ቀደም ብሎ የተፈጸመውን ሁኔታ በማወጅ ከሰው አዕምሮ

በላይ የሆነውን መንፈሳዊ ብልጽግና በወቅቱ እንዲያገኝ የሚያስችል ነው። "መልካም ዜና" ፍጹም ሰው፥ ፍጹም አምላክ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ከ2 ሺ ዓመት በፊት በመስቀል ላይ ስለ ኃጢአታችን ሞቶ፥ በሦስተኛው ቀን ከሞት በመነሳቱ፥ ለኃጢአታችን የከፈለው መስዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዳገኘ የሚያበስር ነው። በእምነት ይህንን ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛችን አድርገን ስንቀበለው፥ በእኛ በጎ ሥራ ሳይሆን እርሱ ስለ ኃጢአታችን ሲል ካፈሰሰው ደም የተነሳ እንቀደሳለን። ከዚህ በኋላ ሕግ አይገዛንም። ወንጌል ምንና ምን እንደያዘ ስንረዳ፥ ቀደም ሲል ለተፈጸመው ነገር "ደስታ"፥ በወቅቱ ላለው ሕይወታችን "ብርታት"፥ እንዲሁም ለወደፊቱ "ፍጹም የሆነ ተስፋ" ይኖረናል። እንግዲህ "የምሥራች ቃል" ከላይ የገለጽነውን ሁሉ ያጠቃልላል።

(ሐ) ነፍሳት የሚድኑበት ነው

"የወንጌል ሰባኪነት" ስጦታ ያለው ሰው የምሥራቹን ቃል በጥሩ ሁኔታ ማወጅ መቻል ብቻ ሳይሆን፥ ውጤታማም ነው! ይኸውም፥ የተሰበከላቸው ሰዎች ወደ ደህንነት ሲመጡ ይታያሉ። ይህም ማለት ሁልጊዜ ስንሰብክ ነፍሳት ይድናሉ ማለት አይደለም። ይሁን እንጂ፥ ብዙ ጊዜ "የወንጌል ሰባኪነት" ስጦታ ያላቸው ሰዎች ሲሰብኩ ነፍሳት እንደሚድኑ ግልጽ ነው። ጴጥሮስ በባለ ሃምሳ ቀን ሲሰብክ ከሦስት ሺ በላይ የሆኑ ሰዎች ዳኑ። *"ሰዎቹም ይህን በሰሙ ጊዜ ልባቸው በህዘን ተነክቶ ጴጥሮስንና ሌሎችን ሐዋርያት ወንድሞች ሆይ! እንግዲህ ምን እናድርግ አሉአቸው"* (የሐዋ. 2፥37)። እንዲሁም ጳውሎስና በርናባስም በስብከታቸው ተመሳሳይ ውጤት እንዳገኙ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል *"በኢቆንዮም ጳውሎስና በርናባስ አብረው ወደ አይሁዳውያን ምኩራብ ገቡ በዚያም በታላቅ ኃይል ስለተናገሩ ብዙ አይሁዳውያንና ግሪኮች አመኑ"* ይላል (የሐዋ. 14፥1)።

2. የወንጌል ሰባኪነት ስጦታ ያለው ሰው የሚለይበት

(ሀ) አገልግሎቱ በአንድ ስፍራ ብቻ አይወሰንም

በኢየሩሳሌም ባለችው ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት በተነሳበት ወቅት ከሐዋርያት በስተቀር ሁሉም ወደ ይሁዳና ወደ ሰማርያ አገሮች ተበትነው ነበር (የሐዋ. 8፥1)። በወንጌላዊነቱ ይታወቅ የነበረው ፊልጶስ አገልግሎቱን ለመስጠት ከቦታ ወደ ቦታ ይዘዋወር እንደነበረ እናውቃለን። በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጋቢ ሆኖ የተቀመጠ አገልጋይ አልነበረም። ለጥቂት ሳምንታት ያህል ሰማርያ ውስጥ ካገለገለ በኋላ ወደ ጋዛ እንደሄደ እናውቃለን። *"...ፊልጶስም ወደ ሰማርያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው"* ይላል (የሐዋ. 8፥5)። በሌላ ጊዜ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው ምድረ በዳ እንደወሰደው እናውቃለን (የሐዋ. 8፥26)። ለመ ጨረሻ ጊዜ የወንጌላዊ ፊልጶስ ስም ተጠቅሶ የምናየው ቂሣሪያ እንደነበረ ሲገለጽ ነው (የሐዋ. 21፥8)። በዚህ ዓይነት የወንጌላ ዊነት ስጦታ ያለው ሰው አገልግሎቱ በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብቻ ተወስኖ የሚቀር አለመሆኑን እንረዳለን። የሚያምኑ ሰዎች ወዳሉበት ሥፍራ ይሄዳል። ከከተማ ወደ ከተማ፥ ከቤተ ክርስቲያን ወደ ቤተ ክርስቲያን፥ በየግል ቤቱ፥ በየወህኒ ቤቱ፥ በየሆስፒታሉ ይዞራል። ለብዙዎች ብቻ ሳይሆን በነፍስ ወከፍም ወንጌልን ይሰብካል።

(ለ) ለሚጠፉት ነፍሳት በጣም ያስባል

ሁልጊዜ ዓይኖቹ ያልዳኑትን ሰዎች ይመለከታልI ለእነ ርሱም ብዙ መቆርቆርና መጨነቅ ያሳያል። ፊልጶስ ወደ ሰማ ርያ ሲሄድ፥ ያልዳኑ ሰዎች መሆናቸውን አውቆ ነው። ሰማርያ

ውስጥ አይሁዶችና አህዛቦችም ይኖሩ ነበር። ከአይሁድ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሃይማኖት የነበራቸው፥ መሲህ ይመጣል ብለው የሚጠብቁ ክፍሎች ነበሩ (ዮሐ. 4፥25)። ሃይማኖተኞችም ቢሆኑ ወንጌል እንደሚያስፈልጋቸው ስለሚያውቅ ወንጌልን ሰበከላቸ ው።

(ሐ) የሚሰብከው ብዙ ጊዜ የደህንነት መልዕክት ነው

ፊልጶስ ጥሪው አማኞችን ማነጽና ማሳደግ አልነበረም። እንደ ጳውሎስ አማኞችን በማስተማር የሚተጋ ሳይሆን፥ በልቡ የሚቃጠለው መልዕክት ላልዳኑት የምሥራቹን ቃል መስበክ ነበር። *"ነገር ግን ስለ እግዚአብሔር መንግሥትና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም እየሰበከላቸው ፊልጶስን ባመኑት ጊዜ ወንዶችም ሴቶችም አምነው ተጠመቁ"* (የሐዋ. 8፥12)። ፊልጶስ ለኢትዮ ጵያዊው ጃንደረባ ደህንነት ለማግኘት የሚያስችለውን መልዕ ክት ሰበከለት። *"ፊልጶስም አፉን ከፈተI ከዚህም መጽሐፍ ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ወንጌልን ሰበከለት"* ይላል (የሐዋ. 8፥35)። የወንጌላዊ ዋና ዓላማ ያልዳኑትን ነፍሳት ወደ ክርስቶስ ማምጣት ነው። እዚህ ላይ መረዳት ያለብን የወንጌል ሰባኪነት ስጦታ ያለው አማኝ፥ የቤተ ክርስቲያን መጋቢም መሆን አይ ችልም ማለት አይደለም። አንዳንድ መጋቢዎችም በተለያየ ሥፍራ እየተዘዋወሩ መስበክ እንደሚችሉ እናምናለን። አንዳንድ ወንጌላዊያን ከደህንነት መልዕክት ውጪ በተለያየ አርዕስት ማስተማር እንደሚችሉ ሁሉ፥ አንዳንድ መጋቢዎችም በደህንነት መልዕክት ላይ የበለጠ ትኩረት ሲሰጡ ይታያሉ።

3. የወንጌል ሰበካ ስጦታ እንዳለን በምን እናውቃለን?

ለዚህ ጥያቄ መልስ ለማግኘት ምዕራፍ አሥራ ሦስት ላይ በሰፊው የተጠቀሰ ስለሆነ፥ ምዕራፉን በጥንቃቄ ማንበቡ

ይጠቅማል። ከዚህ በታች ለተጠቀሱት ሁለት ጥያቄዎች መል ሳችን "አዎን!" ከሆነ፥ ስጦታው እንዳለን እናውቃለን፥

☞ አንደኛ፥ በክርስቶስ ውስጥ ስላለው ደህንነት ላልዳኑት ሰዎች ለመናገር በውስጣችን ከፍተኛ ፍላጎት አለን? ይህ ጥያቄ ሰዎች ወደ ክርስቶስ ሲመጡ ደስ ይለናል ወይ? ብሎ የሚጠይቅ አይደለም። የጠፉ ነፍሳት ወደ ጌታ ሲመጡ ደስ የማይለው እውነተኛ ክርስቲያን እንደሌለ እናውቃለን። ሌሎች ክርስቲያኖች በሚያደርጉት ጥረት ብቻ ሳይሆን፥ በግላችን ለጠፉት ሰዎች መመስከርና ወደ ጌታ እንዲመጡ ማድረግ ደስ ይለናል ወይ? ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ መስጠት የሚችል ሌላ ሰው ሳይሆን እኛው ራሳችን ነን።

☞ ሁለተኛው ጥያቄ፥ ለነፍሳት ስንመሰክር በአገልግሎታችን ውጤት እናያለን ወይ? ስንሰብክ፥ ወይንም ስንመሰክር ያልዳኑት ነፍሳት ወደ ጌታ ይመጣሉ ወይ? የሰብኩት ችሎታ ሳያንሳቸው፥ ምንም ያህል ቃሉን በሚገባ መልክ ቢያቀርቡ አንዳንድ አማኞች ነፍሳትን ወደ ጌታ በማምጣት በኩል አጥጋቢ ውጤት አያገኙም። ዋናው ምክንያት መንፈሳዊነት ጎድሏቸው ሳይሆን፥ *"የወንጌል ሰባኪነት"* ስጦታ ስለሌ ላቸው ብቻ ነው። አንዳንድ አማኞች ስጦታውም ቢኖራ ቸው፥ በተለይ በተወሰነ የዕድሜ ክልል ውስጥ ላሉት ሲሰ ብኩ የበለጠ ፍሬያማ የሚሆኑበት ሁኔታ አለ። አንዳንዶች በዕድሜያቸው "ሙሉ ሰው" ለሆኑት ወንጌልን ሲሰብኩ የበለጠ ፍሬያማ ይሆናሉ። አንዳንዶች ደግሞ ህጻናትን ማስተማር ደስ ይላቸዋልI ሌሎች ደግሞ ለአንድ ሰው ብቻ መመስከር ደስ የሚላቸው፥ ብዙ ሕዝብ ፊት ቀርበው መና ገር ግን የሚያስፈራቸው ናቸውI ሌሎች ደግሞ መድረክ ላይ ቆመው ለብዙ ሕዝብ መስበክ ደስ ሲላቸው፥ ግላዊ የወንጌል ሥርጭት ውስጥ ገብቶ መሳተፍ ግን ተራራ ይሆ ንባቸዋል። መንፈሳዊነታችን የሚለካው ጌታ የሰጠንን ስጦታ

እንደሚገባው በመጠቀማችን እንጂ፥ ወደ ጌታ ባመጣናቸው ነፍሳት ቁጥር አለመሆኑን ማወቅ ይገባናል።

4. ስጦታችንን የምንጠቀመው የት ነው?

"ጌታ የመሰበክ ስጦታ ሰጥቶኛል፥ የመሰበክ ዕድል ግን አላገኘሁም" የሚሉ ክርስቲያኖች አሉ። እግዚአብሔር ከጠራን፥ ስጦታውንም ከሰጠን፥ የአገልግሎቱንም በር ይሰጠናል። ስጦ ታን የሚሰጥ እግዚአብሔር ከሆነ፥ የምናገለግልበትንም ሰፊ በር ይከፍትልናል። የሰባኪ አገልግሎት ቤተ ክርስቲያን መድ ረክ ላይ ብቻ አይደለም። ብዙ በሮች አሉን። ተማሪው፥ ትም ሕርት ቤት፥ ነጋዴው ሱቁ፥ የቤት እመቤቷ ጎረቤቶቿ የተከ ፈቱ በሮቻቸው ወይንም መድረክቻቸው ናቸው። ስጦታው ያለው ሰው፥ ቦታና ጊዜ አይወስነውም። ማንም ሰው ፈቃድ እስኪሰጠው ድረስ አይጠብቅም።

5. ስጦታው ባይኖረንም፥ ላልዳኑት ነፍሳት መመስከር የለብንም ማለት አይደለም

የመስበክ ስጦታ ባይኖረንም ለሚጠፉት ነፍሳት በክርስ ቶስ ውስጥ ስለሚገኘው ደህንነት ልንነግራቸው ይገባል። ኢየሱስ *"...እስከ ምድርም ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ"* ብሎናል (የሐዋ. 1፥8)። ቀደም ሲልም *"...ለዚህ ምስክሮች ናችሁ"* ብሎናል (የሉቃ. 24፥48)። ኢየሱስ ለዚህ ምስክሮች ናችሁ ሲል ምን ማለቱ ነው? ምስክርነታችን ስለምን እንደሆነ ሲገልጽ እንዲህ ይላል *"ክርስቶስ መከራ ይቀበላልI በሦስተኛ ውም ቀን ከሙታን ይነሣል በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰብካል ተብሎ እንዲሁ ተጽፎአል"* ይላል (የሉቃ. 24፥46-47)። ሁላችንም የወንጌሉ

ምስክሮች ነን። በክርስቶስ ኢየሱስ ለጎጢአታችን ይቅርታን እንዳገኘን ያመንን በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ለኃጢአት ይቅርታ እንደሚገኝ ምስክሮች ነን። ጢሞቴዎስ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ቢሆንም ጳውሎስ ወንጌልን እንዲሰብክ ይመክረው ነበር። *"አንተ ግን ነገርን ሁሉ በልክ አድርግ መከራን ተቀበል፤ የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ፥ አገልግሎትህን ፈጽም"* (2 ጢሞ. 4፥5)።

☆ ☆ ☆ ☆

ምዕራፍ
10

የማስተማር ስጦታ

"...ስጦታችን ማስተማር ከሆነ፥ በማስተማር እናስተምር።"
(ሮሜ 12፥7)
"...አንዳንዶቹ አስተማሪዎች እንዲሆኑ ስጦታዎችን ሰጠ።"
(ኤፌሶን 4፥11)

"እግዚአብሔርም በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን አስ ቀድሞ ሐዋርያትን፥ ሁለተኛም ነቢያትን፥ ሦስተኛም አስተማሪዎችን፥ ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን፥ ቀጥሎም የመፈወስን ስጦታ፥ እርዳታንም፥ አገዛዝንም፥ የልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖችንም አድርጓል" (1 ቆሮ. 12፥28)። ሐዋርያው ጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ሲዘረዝር፥ *"የማስተማር ስጦታን"* በሦስተኛነት ደረጃ ጠቅሶት እናያለን። *"የማስተማር ስጦታ"* ማለት ምን ማለት ነው? "የማስተማር ስጦታ" ማለት የእግዚአብሔርን ቃል ጥሩ አድርጎ ለማስተላለፍ፥ ወይንም ለማስተማር

የሚያበቃ መለኮታዊ ችሎታ ማለት ነው። ፒተር ዋግነር የማስ ተማር ስጦታን ሲገልጹ፥ *"የማስተማር ስጦታ እግዚአብሔር ለክርስቶስ አካል ለሆኑት አንዳንድ አማኞች፥ ቤተ ክርስቲያን ጤናማ ሆና የምታድግበትን የእውነትን ቃል ማስተላለፍ እን ዲችሉ የሚሰጠው ስጦታ ነው"* አሉ። መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች ቤተ ክርስቲያን የምትታነጽበትን ልዩ ልዩ ስጦታ መስጠት ብቻ ሳይሆን፥ የተሰጣቸውን ስጦታ ተጠቅመውበት እንደሆነም በመ ጨረሻው ቀን የሚጠይቃቸው እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገ ራል። በሮሜ 12፥6-8 ላይ የማነቃቂያ ስጦታዎች *(motivational gifts)* ተብለው ከተዘረዘሩት ስጦታዎች መካከል *"የማስተማር ስጦታ"* አንደኛው ነው። ይህ "ማስተማር" የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ *"ዲዳስኮ"* ሲሆን፥ ቀጥታ ትርጉሙ *"ማስተማር ወይንም መመሪያ መስጠት"* ማለት ነው።

"የማስተማር ስጦታ" ዋና ዓላማው ለሌሎች "የእውነትን ቃል" ማሳወቅ ወይንም ማስተማር ነው። የሚያሳዝነው ግን አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፥ በየሳምንቱ በቤተ ክርስ ቲያን መድረክ ላይ መሰበኩን፥ ወይንም ትምህርት መሰጠቱን እንጂ፥ የተሰጠው ትምህርት በምዕመናኑ ልብ ውስጥ ትክክለኛ ፍሬ እንዳፈራ የማይጠይቁ መሆናቸው ነው። በዘመናችን፥ በተ ለይ በኢትዮጵያውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የማስተማር ስጦታ እንደሌላቸው በግልጽ እየታየ፥ መድረክ ላይ ለመውጣት የሚፈልጉትን አንዳንድ ክርስቲያኖችን ላለማስቀየም፥ ወይንም ቅር ላለማሰኘት ሲባል ብቻ፥ ወይንም በንግግር ቀልጣፋ ስለ ሆኑ ብቻ እንዲያስተምሩ ማድረግ ትልቅ ስህተት ነው። እንደ "ዕቁብ" ለሁሉም የመሰበክ ዕድል ይድረሰው በማለት፥ የማስተ ማር ስጦታ ሳይኖራቸው እንዲያስተምሩ መድረክ ላይ እንዲወጡ ማድረግ የእግዚአብሔርን ሕዝብ "በመንፈሳዊ ረሀብ" ምክንያት እንዲቀጭጭ፥ ወይንም እንዲሞት ማድረግ ነው። ሽማግሌዎች

ወይንም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለየ ስልጣን ያላቸው ሁሉ፥ ስጦታው ባይኖራቸውም መስበክ፥ ወይንም ማስተማር አለባቸው በማለት ዕድል መስጠት፥ አሁንም ምዕመናኑን መጉዳት ነው። የማስተማር ስጦታ ሳይኖረው በሚያስተምር ሰው ምክንያት የሚ ጎዳው፥ በየሳምንቱ ትልቅ መስዋዕት ከፍሎ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጣው ሕዝብ መሆኑን መረዳት ይኖርብናል።

ሁሉም መስበክና ማስተማር ካለበት፥ ከላይ እንዳነበብነው መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ለቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ባላከፋ ፈለም ነበር። *"...አንዳንዶቹን..."* ሲል፥ ሁሉም ማለት አይደ ለም። የእግዚአብሔርን ቃል በመጣስ አንድን አማኝ ያለስጦታው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአገልግሎት ላይ ስናሰልፍ፥ ምዕመ ናኑን ብቻ ሳይሆን፥ እንዲያስተምር ዕድል የሰጠነውንም ሰው እንጎዳለን። በዘመናችን በተለይ በአንዳንድ ኢትዮጵያውያን ቤተ ክርስቲያን በመድረክ ላይ የሚሰጠው ትምህርት በጣም የሚያሳ ዝን ነው። ከምዕመናኑ አንዱን "ዛሬ ምን ተማርክ? ከትምህርቱ ምን አገኘህ" ተብሎ ቢጠየቅ፥ "ይሀን ተማርኩ፥ ይህን አገኘሁ" ማለት አይችልም። የሚያጠነክረው፥ ወይንም የሚያሳድገው "መንፈሳዊ ምግብ" መስጠት ስለማንችል ነው ብዙ ጊዜ በመዝ ሙርና በጭብጨባ ስሜቱን አግለን ወደ ቤቱ እንዲመለስ የም ናደርገው። ዛሬ ክርስቲያኖች በጎጢአት የሚጫወቱት፥ ትንሽ ነገር ነካ ሲያደርጋቸው ፍንግል ብለው የሚወድቁት፥ በቂ መን ፈሳዊ ስንቅ ስለማንሰጣቸው፥ እንዴት በቅድስና መኖር እንደ ሚችሉ፥ ፈተና ሲያጋጥማቸው ፈተናውን እንዴት መቋቋም እንደሚችሉ ስለማናስተምራቸው ነው።

የማስተማር ስጦታ ካለን፥ በምናስተምረውም ሆነ በጽ ሑፍ በምናቀርበው መልዕክት ሰዎች ሊማሩበት ይችላሉ። ከም ናስተምረው ትምህርት አማኞች ምንም ፍሬ ያለው ነገር የማያገ ኙበት ከሆነ፥ የማስተማር ስጦታ አለን ማለት አንችልም። በተ

ለያየ መንገድ ባቀረብነው መንፈሳዊ ትምህርት ብዙዎች እንዳ ደንበትና እንደታነጹበት በቃልም ሆነ በደብዳቤ የሚገልጹልን ከሆነ፥ *"የማስተማር ስጦታ"* እንዳለን ማወቅ እንችላለን። ይህን ስንል የምናስተምረው ትምህርት ሁሉንም ያስደስታል ማለታችን አይደለም።

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ከተጠቀሱበት ሦስት የመጽ ሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፥ ማለትም ሮሜ 12፥ 1ኛ ቆሮንቶስ 12ና እንዲሁም ኤፌሶን 4 ላይ፥ *"የማስተማር ስጦታ"* ሦስቱም ላይ ተጠቅሶ እናነባለን። *"የማስተማር ስጦታ"* ሦስቱም ላይ በመጠ ቀሱ ብቻ ከሌሎች ስጦታዎች ሁሉ ይበልጣል ማለት አይ ደለም። *"የማስተማር ስጦታ"* በተለያየ መልክ በአማኞች አገልግሎት ውስጥ ይታያል። አንዳንድ ሰዎች የወንጌልን እው ነት ለሕጻናት ጥሩ አድርገው ማስተማር ወይንም ማስተላለፍ ይችላሉ። አንዳንዶች ደግሞ ብዙ ሕዝብ ከማስተማር ይልቅ ለአንድ ሰው የወንጌሉን ቃል ሲያስተምሩ የበለጠ ፍሬ ያፈ ራሉ። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ብቻ በማስተማር ጥሩ ውጤት እንዳመጣ እናውቃለን። አቂላና ጵርስቅላ ደግሞ እጵሎስን በማስተማር ጥሩ ውጤት ማግኘታቸውን እናስታውሳለን (የሐዋ. 18፥26)። የማስተማር ስጦታ እያላቸው፥ በብዙ ሕዝብ ፊት ቆመው ማስተማር የማይሆንላቸውም አሉ። የማስተማር ስጦታ፥ ስጦታው ባለው ሰው ሕይወት የሚታየው አንዳንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን፥ ሁልጊዜ ነው። የማስተማር ስጦታ ያላቸው አማኞች "መልዕክት ከላይ ይወርድልናል" በማለት እጆቻቸውን አጣም ረው የሚቀመጡ ሳይሆኑ፥ በማንበብና በማጥናት ብዙ ጊዜ ያሳልፋሉ። ከማስተማራቸው በፊት በቂ የሆነ ዝግጅት ያደር ጋሉ። የሚያስተምሩትን ትምህርት ሌሎች እንዲገባቸውና እንዲ ጣፍጣቸው፥ ብዙ ምሳሌዎችን ይሰበስባሉ።

"የወንጌል ሰባኪነት" ስጦታ ያለው አማኝ ነፍሳትን ወደ

እግዚአብሔር መንግሥት እንዲመጡ ሲያደርግ፥ "የማስተማር ስጦታ" ያለው ደግሞ አማኞች በጌታ ቤት ጸንተው እንዲቆሙና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ የሚረዳ ነው። ያመኑትን ደቀ መዝሙር ለማድረግ፥ ማስተማር አስፈላጊ ሲሆን፥ ማስ ተማር ደግሞ ስጦታ ያለው አስተማሪን ይጠይቃል። ስሜታዊ በሆነው ነገር ላይ የበለጠ ትኩረት ሰጥተን ትምህርትን ችላ ስንል፥ ለምዕመናኑ መንፈሳዊ ዕድገትን መከልከላችን ይሆናል። ጳውሎስ *"... ሰውን ሁሉ እየገሠጽን፥ ሰውንም ሁሉ በጥበብ ሁሉ እያስተማርን የምንሰብከው እርሱ ነው"* ይላል (ቆላስይስ 1፥28)። በዘመናችን የብዙ አብያተ ክርስቲያናት የችግራቸው ዋና ምክንያት በቂ ትምህርት ለምዕመናኖቻቸው መስጠት ባለ መቻላቸው የሚመጣ ነው። ስለ ክርስቶስ አዳኝነት የተመሰከረለት ሰው፥ ጌታን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ከተቀበለ በኋላ "ከዛሬ ጀምሮ ድነሃልI ኃጢአትህም ይቅር ተብሎልሃልI ዕርዳታ ቢያስፈልግህ እግዚአብሔርን ስትጠይቀው ይሰጥሃል። በፀጋውም ጸንተህ እንድትቆም ያደርግሃል" ተብሎ ከተነገረው በኋላ፥ የክርስትና ሕይወትን ብቻውን መታገል ይጀምራል። ቤተ ክር ስቲያን ሲሄድ ሁልጊዜ የሚሰማው የደህንነት መልዕክት ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወደሚደረግበት ስብሰባ ሲሄድ ደግሞ የሚያገኘው አዲስ ትምህርት የለምI ሕጻን ሆኖ የተማ ረውን የሰንበት ትምህርት ነው። በሁኔታው ግራ ሲጋባ "የክር ስትና ሕይወት ማለት ይሄ ብቻ ነው? ይህን የመሰለ ሕይወት ኖሬ ነው መንግሥተ ሰማይ የምሄደው? አሁን ስላለሁበት ሕይ ወት እግዚአብሔር ግድ የለውም ማለት ነው? በልዩ ልዩ ውጥረት ውስጥ በማልፍበት ወቅት እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል? ለእኔ የሚሆን መልዕክት የለውም? የምሰማው ስብከት አብርሃም እንዲህ ሆኖ ኖረI ዳዊት ጎልያድን ገደለI ጌዴዎን በ300 ወታደሮች ብቻ ጠላቶቹን አሸነፈ የሚል ብቻ ነው። በየቀኑ በሕይወቴ የሚገጥመኝን ልዩ ልዩ ፈተና የማሸንፍበትን

መንገድ ግን የሚነግረኝ የለም" በማለት ሲያማርር ይሰማል። የዚህ ሁሉ ችግር፥ ቤተ ክርስቲያኑን የሚያንጽ ትምህርት የሚሰጡ ስጦታ ያላቸው አስተማሪዎች ስለሌሉ ወይም ቢኖሩም ቤተ ክርስቲያን ስለማትጠቀምባቸውና ስለማታሳድጋቸው ነው።

ማስተማር ማለት ሌላው ሰው የማያውቀውን ማሳወቅ ማለት ነው። ከዚህ በፊት ለፈጸመው ኃጢአት ይቅርታ እንደ ተሰጠው ባለማወቅ ለሚጨነቀው አማኝ፥ 1ኛ ዮሐንስ 1፥9ን አውጥቶ *"በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከአመጻም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው"* ብሎ ለመንገር፥ የማስተማር ስጦታ ያለውን ሰው አይጠይቅም። ጳውሎስ ቲቶን *"አሮጊቶች ሴቶች...በጎ የሆነውን ነገር የሚያስተምሩ ይሁኑ..."* (ቲቶ 2፥3-5) በማለት እንዲመክራቸው ሲነግረው፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቆች ሆነው ያስተምሩ ማለቱ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። መሠረታዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል ለሌሎች ለመናገር የማስተማር ስጦታ አያስፈልገውም። ጳውሎስ በቆላስያስ መልዕክቱ አማኞቹን *"የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገስጹ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ..."* በማለት ይመክራል (ቆላ. 3፥16)። የቤተ ክርስቲያን አባሎች የጳውሎስን ምክር ሰምተው በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳቸው ቢማሩና አንዱ ሌላውን እንደ እግዚአብሔር ቃል መገሰጽ ቢችል፥ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በመቀጨጭ ፈንታ ያድጋሉ።

ይህን ስንል "የማስተማር ስጦታ" ያላቸው ሰዎች ለቤተ ክርስቲያን አያስፈልጉም ለማለት አይደለም። ሐዋርያው ጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን በ1ኛ ቆሮ. 12፥28 ላይ ሲዘረዝር፥ *የማስተማር ስጦታን* ሦስተኛ አድርጎ ጠቅሶታል።

"... እግዚአብሔር አንዳንዶቹን አስቀድሞ ሐዋርያትን፥ ሁለተኛም ነብያትን፥ ሦስተኛም አስተማሪዎችን.... አድርጓል" ይላል። በቀድሞ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ደህንነትን ካገኙ በኋላ ወዲያው በእምነታቸው የሚያጸናቸውን ትምህርት ይሰጣቸው ነበር። *"ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ፤ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ፤ በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር"* (የሐዋ. 2፥41-42)። የማስተማሩን ተግባር ይዘው የነበሩት የማስተማር ስጦታ የነበራቸው ሐዋርያት ነበሩ። እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑ በቂ የሆኑ አስተማሪዎች ሰጥቶ ነበር። ጳውሎስ *"እኔ ሰባኪና ሐዋርያ፥ አሕዛብንም አስተማሪ እንድሆን በተሾምሁበት በወንጌል ሕይወትንና አለመጥፋትን ወደ ብርሃን አውጥቷል"* (2 ጢሞ. 1፥11) ሲል፥ የማስተማር ስጦታ የነበረው ሰው መሆኑን እንረዳለን። በርናባስም የማስተማርና የመምከር ስጦታ እንደነበረው ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ላይ ገልጾታል (የሐዋ. 15፥35)። አጵሎስም ከአስተማሪዎች መካከል አንደኛው እንደነበረ እናውቃለን (የሐዋ. 18፥24-25)። እንዲያውም ለሽምግልና የሚመረጡት "ማስተማር የሚችሉ" መሆን እንዳለባቸው መጽሐፍ ቅዱስ ያዛል (1 ጢሞ. 3፥2)።

1. የማስተማር ስጦታ፥ መለኮታዊ ነው

"መለኮታዊ" የተባለበት ምክንያት ለምንድነው? መለኮታዊ ስጦታ ነው ያልንበት ዋናው ምክንያት፥ አንድ አማኝ የማስተማር ችሎታ ስላለው ብቻ "የማስተማር ስጦታ" አለው ማለት እንዳልሆነ ለመግለጽ ነው። ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽ መንፈስ ቅዱስ ለአንዳንድ አማኞች "የማስተማር ስጦታ" ይሰጣል። ቀደም ሲል በተፈጥሮ የማስተማር ችሎታ ያለውን መንፈስ ቅዱስ ለማስተማር አይቀባውም ማለት አይደለም።

በተፈጥሮ የማስተማር ችሎታ ያለውን መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ የሆነ የማስተማር ስጦታ በመስጠት የበለጠ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያንጽ ማድረግ ይችላል። "በተፈጥሮ የማስተማር ችሎታና" እንዲሁም "የማስተማር ስጦታ" መካከል ያለው ልዩነት ምንድ ነው?

የቀለም ትምህርት ጠቃሚ ቢሆንም፥ ትምህርት የሌለው አማኝ መለኮታዊ የሆነ የማስተማር ስጦታ በማግኘት ጥሩ አስ ተማሪ ሊሆን ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ መንፈስ ቅዱስ የማስተማር ስጦታ ሳይሰጠው ክርስቲያን ቀደም ሲል ባለው የተፈጥሮ ችሎታ አስተማሪ መሆን ይችላል። የተፈጥሮ የማስ ተማር ችሎታ ኖሮት፥ በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው የማስተማር ስጦታ ግን ሳይኖረው ቢያስተምር፥ ጥሩ አድርጎ ማስተማር ይችላል። ይሁን እንጂ፥ ትምህርቱ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስለማይኖረው የሚያስተምራቸውን ሰዎች ሕይወት የሚለውጥና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የሚያሳድጋቸው ላይሆን ይችላል።

2. የማስተማር ስጦታ ያለው አማኝ የወንጌልን ቃል ጥሩ አድርጎ ማስተላለፍ ይችላል

የወንጌልን እውነት ሕዝቡ በሚገባው መንገድ በማስተ ላለፍ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ከኢየሱስ ክርስቶስ የበለጠ አናገኝም። ኢየሱስ ሊያስተላልፍ የሚፈልገውን መልዕክት ለማስተላለፍ በቅድሚያ አድማጮቹ ያሉበትን ሁኔታ ካወቀ በኋላ ከዚያ ይጀምራል። በደንብ እንዲገባቸው በምሳሌ ያስረዳቸዋል። ምሳ ሌዎቹ ከአዕምሮአቸው በላይ ሳይሆኑ በጣም ቀላሎች ናቸው። ከምሳሌዎቹ አንዳንዶቹን ለመጥቀስ፥ (ስውር መብራት፥ የዘሪው ምሳሌ፥ ሉቃስ 8፥16-18፣ ሉቃስ 8፥4-8)። ብዙ ጊዜ ደግሞ ጥያቄ በመጠየቅ ማስተማሩን ይጀምራል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ጥያቄያቸውን በጥያቄ ሲመልስ እናያለን። አንድ ጠቃሚ

ነገር ለማስተላለፍ ሲፈልግ፥ የጊዜውን ሁኔታ ይጠቀማል። ትምህርት በምሳሌ (*object lesson*) መስጠት አንደኛው የማስ ተማሪያ መንገዱ ነው። ጎንበስ ብሎ የደቀ መዛሙርቱን እግር ሲያጥብ ትህትናን ሊያስተምራቸው ፈልጎ እንደሆነ ግልጽ ነው። የማስተማር ስጦታ ያለው ሰው በግሉ ምንም ዓይነት ዝግጅት፥ ወይንም ጥረት አያደርግም ማለት አይደለም።

የምሥራቹን ወይንም የእውነትን ቃል ጥሩ አድርጎ ለማስተላለፍ፥ የንግግርን ስጦታ ይጠይቃል። የወንጌላዊነት ስጦታ ያለው አማኝ የደህንነትን መልዕክት ሲያስተላልፍ፥ የቤተ ክርስቲያን መጋቢው ደግሞ ምዕመናኑን ከሕያው ቃል ሲመ ግብ፥ ሁሉም ጥረታቸው "የእውነትን ቃል" አድማጮቻቸው እንዲገባቸው ለማድረግ ነው። የማስተማር ስጦታ ሁልጊዜ ከት ንቢት ጋር የተያያዘ ነው። ለዚህ ነው አንዳንዶች "የትንቢት ስጦታ" የማስተማር ስጦታ ነው ብለው የሚደመድሙት። *"... ዕለት ዕለትም በመቅደስና በቤታቸው ስለ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ ማስተማርንና መሰበክን አይተውም ነበር"* ይላል (የሐዋ. 5፥42)። እንዲሁም *"በአንጾኪያም ባለችው ቤተ ክርስቲያን ነብያትና መምህራን ነበሩ"* (የሐዋ. 13፥1) የሚለ ውን ቃል ስናነብ ማስተማርና ትንቢት አብረው እንደሚሄዱ እናያለን። ጳውሎስ የሚተነብዩና የሚያስተምሩ ብዙ ረዳቶች በዙሪያው እንዲኖሩ ያደረገው አንዳንዶቹ እውነትን በማወጅ፥ ሌሎቹ ደግም እውነትን ገልጾ በማስረዳት ችሎታ እንዳላቸው ስለሚያውቅ ነበር። *"ጸሎት ቤቶች በሆኑት ምኩራቦች እያስተ ማረና የእግዚአብሔርን መንግሥት የምሥራች ቃል እያበሠረ በገሊላ ሁሉ ይዘዋወር ነበር"* ይላል (የማቴ. 4፥23)።

የማስተማር ስጦታ ያለው አማኝ የተረዳውን የእውነት ቃል በተለያየ መንገድና ዘዴ ለሌሎች ያስተላልፋል። ኢየሱስ

ኒቆዲሞስን ስለ አዲስ ልደት ሲያስተምረው፥ ኒቆዲሞስ ሁለት ጥያቄ ለመጠየቅ ብቻ ኢየሱስን አቋረጠው እንጂ፥ ሰፊውን ጊዜ የወሰደው ኢየሱስ ነበር (ዮሐ. 3፥4፥9)። ሳምራዊቷን ሴት ስለ ሕይወት ውሃ ለማስረዳት በተዘዋዋሪ እንጂ ፊት ለፊት አልቀረባትም። *"አንቺ ሴት ደሀንነት ያስፈልግሻል"* በማለት ፊት ለፊት አልተናገራትም። ኢየሱስ ንግግሩን የጀመረው *"ውሃ ሰጪኝ"* (ዮሐ. 4፥7) በማለት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ አይሁዶችን፥ አረማውያንን፥ የግሪክ ፈላስፋዎችን፥ ንጉሥ አግሪጳን፥ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ወዘተ. አስተምሯል። አንዳንድ ጊዜ በስልጣን (የሐዋ. 13፥16-41)፥ ሌላ ጊዜ ደግሞ በጥበብ (ገላት. 3፥1-5)፥ በለስላሰ ሁኔታ (የሐዋ. 20፥17-35) እንዲሁም በኃይል ቃል (የሐዋ. 23፥1-3) ያስተምር እንደነበረ እናውቃለን። የማስተማር ስጦታ ያለው አማኝ፥ መልዕክቱን የሚያስተላልፈው የሰሚዎቹ ጥማትና ፍላጎት ምን እንደ ሆነ እየተመለከተና፥ እንዲሁም የተፈጥሮ ባህሪያቸውን እየመዘነ ነው።

የተፈጥሮ የማስተማር ችሎታ	የማስተማር ስጦታ
1. ሲወለድ የተሰጠው የተፈጥሮ ችሎታ ነው።	1. በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንደገና ከተወለደ በኋላ የሚሰጠው ነው።
2. ባለበት ሕብረተሰብ ውስጥ ይጠቀምበታል።	2. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይጠቀምበታል።
3. በማንኛውም የዕውቀት ዘርፍ ይጠቀምበታል።	3. የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ይገልጥበታል።

3. የማስተማር ስጦታ ያለው፥ የሚያስተምረውን "የእውነት ቃል" ለማወቅ ይጥራል

ወደ ጌታ የሚመጣ ማንኛውም ሰው፥ በክርስትና ሕይወት ውስጥ ልዩ ደስታ እንዳለ ያውቃል፤ ያ ብቻ ሳይሆን የማስተማር ስጦታ ካላቸው ሰዎች እግር ሥር ቁጭ ብሎ መማር እንዳለበትም ማወቅ አለበት። መንፈሳዊ ትምህርት ሳያገኝ በደስታ ስሜት ብቻ መጋል፥ ከመለኮታዊ መገለጥ ጋር አብሮ አይሄድም። ስሜታችን ትክክለኛውን አቋም መያዝ የሚችለው፥ በእግዚአብሔር ቃል አማካኝነት ነው። በአሁኑ ዘመን አንዳንድ ክርስቲያኖች ከቃሉ ይልቅ *"ስሜታዊ"* ነገር ላይ የበለጠ ትኩረት ሲሰጡ ያታያሉ። የታወቁት የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁር፥ ዶክተር ጆን ስታት፥ *"እውነት የሌለበት የግል ልምምድ፥ አዕምሮአቸውን ለማይጠቀሙ ክርስቲያኖች ጠንቅ ነው"* አሉ። ክርስትና በእውነት ቃል ላይ የተመሠረተ ስለሆነ፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ "ትምህርት" መካከላዊ ሥፍራ ሊይዝ ይገባል። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠው ትዕዛዝ፥ *"ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲፈጽሙ አስተምሯቸው"* (የማቴ. 28፥20) የሚል ነው።

4. የማስተማር ስጦታ ያለው የሚያስተምረውን ትምህርት በቅደም ተከተል ማቅረብ ይችላል

የሚያስተምረውን ትምህርት በቅደም ተከተልና በሥርዓት ስለሚያስተምር፥ ተማሪዎቹ እርሱን መከተል አይከብዳቸውም። ትምህርቱ ብዙ ተጨባጭ የሆኑ እውነቶችን፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን የያዙ ናቸው። የሚያስተምራቸው ትምህርቶች በመጽሐፍ ቅዱስና እውነት ላይ የተመሠረቱ ናቸው። የማስተማር ስጦታ ያለው ሰው በቀላሉ ማመን ያስችግረዋል። ተጨባጭ

የሆነ ነገር ማየትና መያዝ ይፈልጋል። ለዚህ ጥሩ ምሳሌያችን ቶማስ ነው። ክርስቶስ ከሞት መነሳቱን ደቀ መዛሙርቱ ጥሩ አድርገው ቢነግሩትም፥ *"...የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ፥ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ፥ እጄንም በጎኑ ካላገባሁ አላምንም"* አላቸው (የዮሐ. 20፥25)። ከአንድ ሳምንት በኋላ ኢየሱስን ካየ በኋላ ግን *"..አምላኬና ጌታዬ"* ብሎ ጮኸ (የዮሐ. 20፥28)። እንዲሁም የማስተማር ስጦታ ያላቸው ሰዎች አንድን "እውነት ነው" ተብሎ የቀረበላቸውን ነገር ከመቀበላቸው በፊት ተጨባጭነት እንዳላቸው ማወቅ ይፈ ልጋሉ። በዚህ ዓይነት የሚያስተምሯቸውንም ተጨባጭ በሆነ የእግዚአብሔር እውነት ለማስታጠቅ ብቃት አላቸው።

☆ ☆ ☆ ☆

ምዕራፍ
11

የመምከር ስጦታ

"...እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን... የሚመምከርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ..."
(ሮሜ 12፥6-8)

1. "መምከር" ምዕመናንን ለማነጽ አስፈላጊ ነው

ኢየሱስ በቅርብ ጊዜ ስለሚቀምሰው የሞት ጽዋ፥ ስለ ትንሳኤውና እንዲሁም በመጨረሻ ወደ አብ ዘንድ እንደሚሄድ ለደቀ መዛሙርቱ ሲነግራቸው፥ ተደናግጠውና ልባቸው በሀዘን ተሞልቶ፥ *"ጌታ ሆይ! እኛስ ወደ ማን እንሄዳለን?"* ብለው ጠየቁት። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ በወቅቱ የተሰማቸውን ፍር ሃት ለማጥፋት *"ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል"* (የዮሐ. 14፥16) አላቸው። በዚህ ጥቅስ ውስጥ

መንፈስ ቅዱስን "ፓራክሌት" ይለዋል። ትርጉሙም "የሚያጽናናቱ የሚመክር" ማለት ነው። "መምከር" የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁለት ትርጉም እንዳለው እናያለን። አንደኛው፥ "ማጽናናት" ሲሆን፥ ሁለተኛው፥ "መምከር" ነው። እነዚህን ሁለት ትርጉሞች ሳናበላልጥ እኩል መያዝ ጠቃሚነት አለው። ለምሳሌ፥ አባት በልጁ ላይ አንድ ከፋ ነገር ቢደርስበት፥ ማጽናናት ብቻ ሳይሆን፥ ምክርም የሚሰጥበት ጊዜም እንዳለ እናውቃለን። ሐዋርያው ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረውን የመሪነት ስልጣን በሚጠቀምበት ወቅት፥ የአባትነትን አቋም ይዞ ምዕመናንንና የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ሲመክርና ሲያጽናና እናየዋለን። "ወደ መንግሥቱ ወደ ክብሩም ለጠራችሁ ለእግዚአብሔር እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እየመከርንና እያጸናን፥ እየመሰከርንላችሁም፥ አባት ለልጆቹ እንደሚሆን ለእያንዳንዳችሁ እንደ ሆንን ታውቃላችሁና" ይላል (1 ተሰሎ. 2፥11-12)።

የምዕመናንን መንፈሳዊ ሕይወት ለመጠበቅ፥ የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ ብዙ ጊዜ ምዕመናኑን በየጊዜው በሚያቀርበው ስብከት "መምከር" እንዳለበት እናውቃለን። በቀድሞ ዘመን ሐዋርያት "ምክርን" በአገልግሎታቸው ውስጥ በጣም ይጠቀሙበት እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያየ ሥፍራ እናነባለን። በርናባስ "...መጥቶ የእግዚአብሔርን ጸጋ ባየ ጊዜ ደስ አለውና ሁሉንም በልባቸው ፈቃድ በጌታ ጸንተው ይኖሩ ዘንድ መከራቸው..." (የሐዋ. 11፥23)። "... በዚያችም ኩታማ ወንጌልን ሰብከው እጅግ ደቀ መዛሙርትን ካደረጉ በኋላ፥ የደቀ መዛሙርቱን ልብ እያጸኑ በሃይማኖትም ጸንተው እንዲኖሩ እየመከሩና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል እያሉ ወደ ልስጥራን ወደ ኢቆንዮንም፥ ወደ አንጾኪያም ተመለሱ" (የሐዋ. 14፥22)።

2. የመምከር አገልግሎት ያሉት ክፍሎች

2.1. እምነትን ተግባራዊ ለማድረግ፥ የአማኞችን ፍላጎት መቀስቀስ

ሐዋርያው ጳውሎስ እምነታቸውን ተግባራዊ እንዲ ያደርጉ ብዙ ጊዜ የአማኞችን ፍላጎት "በመምከር" ይቀሰቅስ እንደ ነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናነባለን። ክርስቲያኖች ራሳቸውን ለእግዚአብሔር የተቀደሰ መስዋዕት አድርገው እንዲያቀ ርቡ ሲመክር "እንግዲህ ወንድሞቼ ሆይ! ሁለንተናችሁን እግዚአ ብሔርን ደስ የሚያሰኝ፥ ሕያውና የተቀደሰ መሥዋዕት አድር ጋችሁ እንድታቀርቡ በእግዚአብሔር ርኅራሄ እለምናችኋለሁ፤ ይህም ማቅረብ የሚገባችሁ ቅንነት ያለው እውነተኛ አገል ግሎት ነው" ይላቸው ነበር (ሮሜ 12፥1)። እንዲሁም የቆሮን ቶስ ቤተ ክርስቲያን አባላትን ከዚህ በፊት በገቡት ቃል ኪዳን መሠረት ድሃ የሆኑ ክርስቲያኖችን ለመርዳት የገንዘብ መዋጮ አቸውን እንዲሰጡ ይቀሰቅሳቸው ነበር። "ስለዚህ ልትሰጡ ቃል የገባችሁበትን በቅድሚያ እንድታዘጋጁ እንዲያስታውሱአ ችሁ በማለት እነዚህ ወንድሞች ከእኔ ቀድመው ወደ እናንተ እንዲመጡ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ.." (2 ቆሮ. 9፥5) ይላቸዋል። ጳውሎስ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ምዕመ ናንን ማሳሰብ የፈለገው ከዚህ በፊት የገቡትን ቃል ኪዳን እንዲ ያስታውሱ ነው። ቃል የገቡት በፈቃዳቸው እንጂ፥ ማንም አስ ገድዷቸው አልነበረም። አሁንም ጳውሎስ ደብዳቤ ሲጽፍላቸው፥ ቃል ኪዳናቸውን አስታውሰው እንዲሰጡ ለማሳሰብ እንጂ፥ "ድሃ የሆኑትን ክርስቲያኖች መርዳት አለባችሁ" በማለት አስ ጨንቆ መያዙ አይደለም። ጳውሎስ በምክሩ፥ ቃል ኪዳናቸውን እንዲያስታውሱ ሲቀሰቅስ እናያለን። ይሁዳም በደብዳቤው አማኞች በእምነት መጋደል እንዳለባቸው በምክር ሲቀሰቅ እና ያለን። "...ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ስለተሰጠው እምነት በብርቱ

እንድትጋደሉ ለመምከር ልጽፍላችሁ ግድ ሆነብኝ (የይሁዳ መልዕክት ቁ. 3)። ከላይ ባነበብናቸው ጥቅሶች ውስጥ ሁሉ *"መምከር"* የሚለውን ቃል በግልጽ እናያለን።

"በራስ ወዳድነት" ሕይወት ውስጥ የሚኖረውን ክርስቲያን፥ ክርስቶስ በሕይወቱ ዋናውን ሥፍራ እንዲይዝ እንዲ ፈቅድለት መካሪው የእግዚአብሔርን ቃል በመጠቀም ፍላጎቱን ለመቀስቀስ ይሞክራል። "ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ ሕይወትህን እንዲቆጣጠር ፍቀድለትI እስካሁን በራስህ መንገድ ሄደህ ምንም አላተረፍክም። አሁን ግን የፈቀድከውን አድርግ ብለህ ራስህን ስጠው። በሰጠህም ተስፋ ላይ ጸንተህ ቁም" ሲል ይመክረዋል። ክርስቲያኑ ምክሩን ከተቀበለ፥ ፍጹም የተለወጠ ሰው ሊሆን ይችላል። በሕይወቱ የሚኖረውንም ለውጥ እርሱ ብቻ ሳይ ሆን፥ ሌሎችም ያዩታል። "መካሪው" በዚያ ሰው ሕይወት ውስጥ የሆነውን ለውጥ አይቶ እግዚአብሔር በሰጠው ስጦታ የሌላውን ሰው ሕይወት ለመለወጥ እንደተጠቀመበት ሲያይ ልቡ በደስታ ይሞላል። "የምክር" ስጦታ የሚጠቅመው ብዙ ሕዝብ በአንድ ላይ በማገልገል ብቻ ሳይሆን፥ አንዱን ሰው በተናጠል በማገልገልም መሥራት ይችላል። "የመምከር ስጦታ" የሚኖራቸው ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥልጣን፥ ወይንም ደረጃ ያላቸው ብቻ አይደሉም። ተራ ምዕመናንም "የመምከር ስጦታ" ሊኖራቸው ይችላል።

2.2. ማበረታታት፥ ወይንም ማደፋፈር

"ማደፋፈር" ወይም *"ማበረታታት"* ከመምከር ስጦታ ውስጥ ሌላው ክፍል ነው። ጳውሎስ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናንን አንድ ጊዜ "ወደ ኋላ" የተመለሱትን ወንድሞች እንዴት መቀበል እንዳለባቸው ሲመክር እንዲህ አላቸው፥

"... እንደዚህ ላለ ሰው ይህ ከእናንተ የምትበዙት የቀጣችሁት ቅጣት ይበቃዋልና እንደዚህ ያለው ከልክ በሚበዛ ኀዘን እንዳይዋጥ ይልቅ ተመልሳችሁ ይቅር ማለትና ማጽናናት ይገባችኋል" አላቸው (2 ቆሮ. 2፥6-7)። ጳውሎስ የገለጸው ሰው፥ ቀደም ሲል በጉጢአት ላይ የወደቀ ሰው እንደነበረ እና ያለን። የሠራውን በደል አማኞች ሁሉ ያውቁት ነበር። በሠራው ጉጢአት መጠን ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊውን ቅጣት ሰጥታው ነበር። ይሁን እንጂ፥ ቅጣቱን ሲጨርስ ቤተ ክርስቲያን ያንን ሰው መልሳ በመቀበል ፈንታ፥ ቅጣቱን አራዘመችበት። ይህን ዓይቶ ጳውሎስ ዝም ማለት ስላልፈለገ፥ ያን ሰው ቤተ ክርስቲ ያን በይቅርታ መልሳ መቀበልና በእምነቱ እንዲጸና ማበረታታ ትና ማደፋፈር እንዳለባት ምክር ሰጠ። ይሄ ችግር በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ብቻ የነበረ ሳይሆን፥ በእኛም ዘመን በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ይታያል። ክርስቲያኖች በጉጢአት ሲወድቁ፥ አስፈላጊውን ቅጣት ሰጥቶ እንደገና በእምነታቸው እንዲያድጉና እንዲጸኑ በማደፋፈርና በማበረታታት ፈንታ፥ ከወደቁበት እንዳይነሱ የሚደረግበት ጊዜ አለ። ለእንደነዚህ ዓይነቶቹ ወገኖቻችን ግድ የማይለን ቸልተኞች ብንሆን፥ ሕሊ ናችን ፈጽሞ ካልደነዘዘ በስተቀር "ወንድምህ የት ነው?" ከሚለው ጥያቄ ምንጊዜም ቢሆን ነጻ መሆን አንችልም።

የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች፥ የጋብቻ አማካሪዎች፥ የሥነ ልቦና ምሁሮች፥ እንዲሁም ሌሎች የተለያየ ሙያ ያላ ቸው ሰዎች "የመምከር ስጦታ" ሊኖራቸው ይችላል። ስጦታው ያለው መካሪ፥ ልቡ በርህራሄና በፍቅር የተሞላ ስለሆነ ዕርዳታ በመፈለግ ወደ እርሱ የመጣውን ሰው በድካሙ አይፈርድምI ወይንም አይኮንንም። "ተመካሪው" የልቡን ሲያፈስለት፥ በጸጥታ የማዳመጥ ችሎታ አለው። የሰውየውን አቋም በጥንቃቄ ይመ ረምራል። መስማት ብቻ ሳይሆን፥ እርሱ ራሱ በምን ዓይነት

ችግር ውስጥ ሕይወቱ ተጠላልፎ እንደነበረና ከዚያም እንዴት መውጣት እንደቻለ ሳይፈራ ይገልጽለታል። ተሰፋቢስነቱን ሳይ ሆን በሕይወቱ እግዚአብሔር ከፍተኛ ዓላማ እንዳለው፥ ፈቃደኛ ከሆነ የሕይወቱ አቅጣጫ መለወጥ እንደሚችል በመግለጽ የወ ደቀውን ስሜቱን ከፍ ያደርግለታል። በጌታ ላይ የበለጠ እምነ ትና ትምክህት እንዲኖረው ያበረታታዋል። ለጥያቄው መልስ እንዲያገኝ ፊቱን ወደ እግዚአብሔር ቃል እንዲያነሳ ያደፋ ፍረዋል።

2.3. ግሳጼ

መገሰጽ የሚገባቸውን መገሰጽ፥ የእግዚአብሔር ቃል የሚደግፈው አሳብ ነው። የመምከር ስጦታ ያላቸው አማኞች መገሰጽ የሚገባውን ሲገስጹ፥ ያንጻሉ እንጂ፥ አይሠብሩም። ጳውሎስ የፊልጵስዩስ ምዕመናንን በጣም ያደንቃል። ዕርዳታ በሚያስፈልገው ሰዓት ተገኝተው በገንዘብ የረዱት ናቸው። በአገልግሎቱ ፍሬያማ እንዲሆን፥ በመንገዱ መሰናክል እንዳያ ጋጥመው አጥብቀው የጸለዩለት የጸሎት ጓደኞቹ ነበሩ። ይሁን እንጂ፥ ድካም ሲያይባቸው ዝም አላለም። የፊጵሲዮስ ቤተ ክርስቲያን አባል የነበሩት *ኤፆድያና ሲንጢኪ* እርስ በርሳቸው መስማማት ስላቃታቸው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንዳንድ ችግሮች ይታዩ ነበር። ስለዚህ እነዚህ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ጎልተው የሚታዩ ሁለት ሴቶች እንዲታረሙ ፊት ለፊት መገ ሰጽ ነበረበት። *"ኤፆድያና ሲንጢኪ እርስ በርሳቸው ተስማም ተው በጌታ ያላቸውን አንድነት እንዲያድሱ እለምናቸዋለሁ። አንተም እዚያ ያለኸው ታማኝ የሥራ ጓደኛዬ እነዚህን ሴቶች በቅርብ ሆነህ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንድትረዳቸው አሳስብ ሃለሁ! ምክንያቱም እነዚህ ሴቶች ክቀሌምንጦስና ሰምቻቸው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት ከሌሎችም የሥራ ጓደኞቼ ጋር በመሆን የምሥራቹን ቃል በማዳረስ ረገድ ተጋድለዋል"* (ፊል. 4፥2-3)።

ሐናንያና ሰጲራ መንፈስ ቅዱስን ለመዋሸት በመሞከራ ቸው ምክንያት ጴጥሮስ በኃይል እንደገሰጻቸው እናውቃለን (የሐዋ. 5፥1-11)። *"...ሰይጣን ስለምን ወደ ልብህ ገባ? ... የዋሸኸው በእግዚአብሔር ላይ ነው እንጂ በሰው ላይ አይደ ለም... የእግዚአብሔርን መንፈስ ለመፈታተን እንዴት ተስማማ ችሁ?..."* በማለት ጴጥሮስ በኃይል ባለና ሚስቱን ሲገስጽ እና ያለን። ዛሬ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ክርስቲያኖች በኃጢአት ሲጫወቱ፥ በእግዚአብሔር ቃል ሲነግዱና ሲሸቃቅጡ በግልጽ እየታዩ በድፍረት የሚገስጽ ሰው በመጥፋቱ ኃጢአት በቤተ ክርስቲያን ሲሰለጥን፥ የክርስቶስ ስም ሲሰደብ መስማት እየተለ መደ መጥቷል። ከመስመር ሲወጡ መገሰጽ ያለባቸው በአመራር ላይ ያልሆኑት ምዕመናን ብቻ ሳይሆኑ፥ ቤተ ክርስቲያንን የሚመሩና የሚያስተዳድሩም እንደአስፈላጊነቱ መገሰጽ አለባ ቸው። ከሐዋርያት መካከል ጴጥሮስ በአንድ ነጥብ ላይ የሳተበት ጊዜ ነበር። ያም የግብዝነት ጠባይ ያሳየበት ወቅት ነው። ሌሎቹ ሐዋርያት ዝም ቢሉ፥ ጳውሎስ ግን የጴጥሮስን ግብዝነት እያየ ዝም ማለት ስላልፈለገ ፊት ለፊት እንደገሰጸው እናው ቃለን። ጳውሎስ *"ጴጥሮስ ወደ አንጾኪያ በመጣ ጊዜ በግልጥ ተሳስቶ ስለ ነበር ፊት ለፊት ተቃወምሁት"* ይላል (ገላት. 2፥ 11)። ጳውሎስ ጴጥሮስን የገሰጸው ዝም ብሎ ሳይሆን፥ "ተሳስቶ ስለ ነበር" ብቻ ነው።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምናያቸው አማኞች ሁሉ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የበሰሉ አይደሉም። አንዳንዶቹ ልክ እንደ ሕጻን ልጅ ጥቂት ክፉ የሆነ ነገር ሲደርስባቸው ተስፋ የሚቆርጡ፥ የሚፈልጉት ነገር እንዳሰቡት፥ ወይንም እነርሱ እንደሚፈልጉት ካልሆነላቸው የሚጮሁ፥ የሚወራጩ፥ የሚነጫ ነጩና የሚያጉረመርሙ ናቸው። ትንሹን ነገር ተራራ አድርገው የሚያዩና ለማሳየት የሚሞክሩ፥ ሁልጊዜ "እሹሩሩ" በሉኝ፥

"በቀላሉ እሠበራለሁና በጥንቃቄ ያዙኝ" የሚሉም ይገኙበታል። መጋቢው ሁልጊዜ የሚፈልጉትን መስጠት ካልቻለ፥ ወይንም እንደሚፈልጉት ካልሆነላቸው "ጥሩ አገልጋይ" አይደለም ይላሉ። ከቤተ ክርስቲያን አንድ ቀን ቀርተው "የት ነበርክ" የሚል ጥያቄ ካልቀረበላቸው፥ ከቤተ ክርስቲያ ማፈግፈግና መሸሽ፥ "ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፍቅር የለም" ማለት ይጀም ራሉ። እንደነዚህ ዓይነቶቹ እንደ እግዚአብሔር ቃል የሚገሰ ጹበት ምክንያት ኖሮ ቢገሰጹ፥ በቀላሉ ስብርብራቸው ይወጣል። መገሰጽና መመከር የማይፈልጉ ናቸው። *"ልጆች በማይለሽነት ተሳስተው ጥንቃቄ የጎደለው ነገር ያደርጋሉ፤ ነገር ግን በአ ርጩሜ መቅጣት ጨዋ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል"* (ምሳሌ 22፥15)። በዘመናችን እንደ እግዚአብሔር ቃል አማኞችን የሚመክር ብቻ ሳይሆን የሚገስጽም "የመምከር ስጦታ" ያለው አማኝ በመጥፋቱ፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ከሥርዓት ውጪ የሆኑ ክርስቲያኖች እንዳሉ እናውቃለን። ችግሩን ያባሰው መካሪ መጥፋቱ ብቻ ሳይሆን፥ ሲመክሩ፥ ሲገሰጹ "እሺ!" ብለው ምክሩንና ግሳጼውን ሰምተው ራሳቸውን ማረም የሚፈልጉ አማኞች ቁጥራቸው ማነሱ ነው።

"መገሰጽ" ማለት፥ አማኙን እንዳይሞት እንዳይሽር አድርጎ ስብርብሩን ማውጣት ማለት አይደለም። ፍቅር በጎደለው መንፈስ የአማኞቻቸውን ልብ የሚሰባብሩ አንዳንድ የቤተ ክር ስቲያን መሪዎች እንዳሉ አንክድም። መገሰጽ ማለት የማይደ ግፉንን፥ ከእኛ አሳብ ጋር የማይሄዱትን አማኞችን መቃወም፥ ማስፈራራት አይደለም። ፍቅርና ርህራሄ በጎደለው መንፈስ የሌላውን ስሜት ከጎዱ በኋላ፥ "የጌታ ሥራ ግድ ብሎኝ ነውI እኔ ከእርሱ ጋር የግል ቂም የለኝም" ማለት በዘመናችን በጣም የተለመደ ሆኗል። ፍቅር በጎደለው መንፈስ ማንንም እንድን ገስጽ የእግዚአብሔር ቃል ነጻነት አይሰጠንም። "የመገሰጽ"

ዋና ዓላማ መጥፎ ባህሪን ለማረም እንጂ፥ ቁጣችንን በሌላው ላይ ለመግለጽ አይደለም። መገሰጽ ድካሙን ማውራት ብቻ ሳይሆን፥ ከድካሙም የሚወጣበትን ሀሳብ መስጠትንም ያጠቃል ላል። የምንገስጸውም፥ አማኙ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያዘው ውጪ የሆነ ሕይወት ሲኖር ብቻ ነው። ከእኛ የተለየ አሳብ ስላለው ብቻ ዝም ብለን እንገስጻለን ማለት አይደለም። ጳውሎስ ጴጥሮ ስን የገሰጸው ያለምክንያት፥ ወይንም ከጴጥሮስ የበለጠ ሰዎች እርሱን እንዲያከብሩት ብሎ አይደለም። ጴጥሮስ በዚያን ወቅት ግብዝነት ይታይበት ስለነበረ ብቻ ነው። ግብዝነትን መጽሐፍ ቅዱስ አይደግፈውም።

በሕግና በቃል ኪዳን ካላገባት ሴት ጋር አንድ አማኝ የሩካቤ ሥጋ እየፈጸመ አንድ ላይ ቢኖር፥ ትክክል ስላልሆነ ሊገ ሰጽ ይገባል። "የመምከር ስጦታ" ያለው አማኝ፥ ያንን ሰው በፍ ቅር ተሞልቶ ሊገሰጸው ያስፈልጋል። ሀሊናው ካልደነዘዘ በቀር ካላገባት ሴት ጋር የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ኃጢአት እንደ ሆነ ሀሊናው፥ እንዲሁም የእግዚአብሔር ቃል ይነግረዋል። *"ስለዚህ ከዝሙት ራቁI ሰው የሚያደርገው ሌላው ኃጢአት ሁሉ ከሰውነቱ ውጪ የሚደረግ ነውI ዝሙትን የሚ ፈጽም ሰው ግን በገዛ ሰውነቱ ላይ ኃጢአት ያደርጋል"* ይላል (1ኛ ቆሮ. 6፥18)። ስለዚህ በዚህ ቃል መሠረት "መካሪው" ያ አማኝ ሕይወቱን እንዲያስተካክል ፊት ለፊት ሊገስጸው ይገባል። አማኙ ግሳጼውን ሰምቶ እግዚአብሔርን ይቅርታ ከጠየቀና ንስሀ ከገባ፥ "ግሳጼው" እዚያው ላይ ማብቃት አለበት። ንስሀ ገብቶ ሕይወ ቱን ካስተካከለ በኋላ፥ ያለፈውን በመርሳት ወደፊት እንዲ ራመድ በማጽናናትና በማበረታታት ፈንታ፥ ያለፈውን እያነሱ ሁልጊዜ መውቀስ ትክክል አይደለም።

2.4. ትዕግሥት

አንዳንድ አማኞች ሲመክሩ፥ ሲገሰጹ ምክሩንና ግሳጼ ውን ሰምተው ካለባቸው ድካም ቶሎ ይመለሳሉ። ብዙዎች ግን፥

የበለጠ እልኸኞች ይሆናሉ። "አንተ ማነህና ነው፥ ይህን አድርግ፥ ይህን አታድርግ የምትለኝ" በማለት ተቃውሚቸውን ያሰማሉ። ኃጢአታቸው ግልጽ ቢሆንም፥ የሚሰጣቸውን ምክር አይሰሙም። ክርክር ይወዳሉ። እንደነዚህ ዓይነቶቹን እንዴት መያዝ እንዳለብን ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በሰጠው ምክር ላይ እናያለን። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን *"... እያስረዳህ፥ እየገሠጽህና እየመክርህ በትዕግሥትና በማስተማር ጽና"* ይለዋል (2 ጢሞ. 4፥2)። "መምከር" ብቻ ሳይሆን፥ "መታገስም" እንዳለብን እና ያለን።

በዘመናችን "ክርስቲያን መካሪዎች" ያለባቸው ኃላፊነትና በአገልግሎታቸው ውስጥ የሚከተሉት መመሪያ የሚያጠያይቅና የሚያከራክር እየሆነ መጥቷል። አንዳንድ የዓለም "የሥነ ልቦና" አዋቂዎች፥ ዕርዳታ ፈላጊዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው ፊት ለፊት ሊነግራቸው ያስፈልጋል የሚለውን ሃሳብ ይቃወማሉ። ራሳቸው ይወስኑ እንጂ፥ "እንዲህ ሁኑ፥ እንዲህ አድርጉ" ብሎ ተመካሪዎችን መንገር ትክክል አይደለም ይላሉ። የወንጌላውያን ሕብረት፥ *አንጄ. አዳምሰን* የመሳሰሉ ታዋቂ *"የሥነ ምክር"* ምሁራን፥ "በመጽሐፍ ቅዱሳዊ የምክር አገልግሎት"፥ ምክር ፈላጊውን ለመርዳት ድካሙን ፊት ለፊት በትክክል መንገር፥ እንዲሁም ለችግሩ መፍትሄ ማግኘት የሚችለው ወደ እግዚአብሔር በመመልከት እንደሆነ ማሳወቅ ያስፈልጋል" የሚለውን አቋም ይዘዋል። አስተማሪ ጥረት የሚያደርገው የተማሪውን "አዕምሮ" ለመንካት ሲሆን፥ "መካሪ" ግን ልብን ለመንካት ነው። ዝንባሌውና ጥረቱ ሌሎችን ማነጽና ማበረታታት ነው።

ብዙ ጊዜ "የመምከር ስጦታ" የሚታየው፥ የእረኝነት ልብ ባላቸው ሰዎች ላይ ነው። አንድ ሰው ይሄ ስጦታ እንዳለው የሚታወቀው፥ በመጀመሪያ በሚያቀርበው ስብከትና ትምህርት

ሲሆን፥ ሁለተኛ፥ በግል ከአንድ ሰው ጋር በሚኖረው ውይይት ላይ የዚያን ሰው ግላዊ ችግር ለመፍታት በሚያደርገው ጥረትና ችሎታ ነው። የመምከር ስጦታ ያለው ሰው፥ የሌላው ሰው መንፈሳዊ ዕድገት፥ ስኬታማ ሕይወት ስለሚያሳስበው፥ ጊዜ ወስዶ ችግሩን ለመፍታት ከፍተኛ ፍላጎትና ጥረት ያሳያል። ፒተር ዋግነር የሥነ ምክር ስጦታን ሲገልጹ፥ *"የምክር ስጦታ እግዚአብሔር ለአንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ምዕመናን የሚሰጠው፥ ሌሎችን መምከር፥ ማጽናናት እንዲችሉ፥ የሚያስችላቸው ስጦታ ነው"* አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በምክር ስጦታው በጣም የታወቀው በርናባስ ነበር። *"የቆጵሮስ ተወላጅ የሆነ ዮሴፍ የሚባል አንድ ሌዋዊ ነበር፤ ሐዋርያት በርናባስ እያሉ ይጠሩት ነበር፤ ትርጓሜው የመጽናናት ልጅ ማለት ነው"* (የሐዋ. 4፥36)። ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ጌታ በሚያስደንቅ ሁኔታ ከተገናኘው በኋላ ከሐዋርያት ጋር ለመቀላቀል ፈልጎ ሁሉም ሲጠራጠሩት የተቀበለው በርናባስ ብቻ ነበር። በሌላ ጊዜም ጳውሎስ ከማርቆስ ጋር አላገለግልም ባለበት ጊዜ ማርቆስን የተቀበለው አሁንም በርናባስ ነው። በርናባስ "የማጽናናት ስጦታውን" ተጠቅሞ ማርቆስን ባይቀበለው ኖሮ፥ እኔና እናንተ "የማርቆስ ወንጌልን" ባላገኘንም ነበር።

"የምክር ስጦታ" ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ፥ ክርስቲያኖች በሙሉ እርስ በርሳቸው መደጋገፍ፥ መመካከር፥ እንዳለባቸው መጽሐፍ ቅዱስ ያዛል። *"ይልቅስ ከእናንተ በኀጢአት ተታሎ እልኸኛ እንዳይሆን ዛሬ የተባለው ጊዜ እስካለ ድረስ በየቀኑ በመመካከር ተረዳዱ"* ይላል (ዕብ. 3፥13)። ክርስቲያኖች ሲገናኙ፥ እርስ በርሳቸው መመካከርና መበረታታት አለባቸው። ከዚህ ሁሉ በላይ ግን፥ ሌሎችን ለመምከር ልዩ ስጦታ ያላቸው በክርስቲያኖች መካከል አሉና ስጦታቸውን አምነን በመቀበል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ልንገለገልባቸው ያስፈልጋል። በየአብያተ ክርስቲያናቱ ውስጥ በልዩ ልዩ ምክንያት የተጎዱ፥ ዕርዳታ እየ

ፈለጉ፥ የሚረዳቸው ያጡ ብዙ ክርስቲያኖች እንዳሉ እናውቃለን። በምዕመናኑ መካከል "የመምከር ስጦታ" ያላቸው ካሉ፥ የተጎዱትን መምከርና ማጽናናት ይችላሉ። የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ ሁልጊዜ የምክር አገልግሎት መስጠት አለበት ማለት አይደለም። ከምዕመናኑ መካከል ስጦታው ያላቸው ሰዎችም ምክር ለሚያስ ፈልጋቸው ምዕመናን ምክር መስጠት ይችላሉ።

3. "የመምከር ስጦታ" ያለው ሰው በምን ይታወቃል?

3.1. ሰዎችን ሁልጊዜ ማበረታታት ደስ ይለዋል

"የመምከር ስጦታ" ያለው ሰው፥ ሰው ሁሉ የተሟላና እንዲሁም ትርጉም ያለው ሕይወት እንዲኖረው ይፈልጋል። ሰዎች የተፈጥሮ ችሎታቸውን ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲጠቀሙበት መምከርና ማደፋፈር ደስ ይለዋል። ዕርዳታውን ፈልገው ለመጡት ሰዎች አሸናፊ ሕይወት እንዲኖሩ የሚያስችላቸውን ምክር መስጠት በመቻሉ፥ ወይንም መሣሪያ በመሆኑ ደስ ይለዋል። የመምከር ስጦታ ያለው ሰው "አንድ፥ ሁለት" እያለ ጠቃሚ መመሪያ፥ ወይንም ምክር የመስጠት ችሎታ አለው።

አንድ ጊዜ ከባሏ ጋር ችግር የነበራት ሴት ምክር ፍለጋ ወደ አንዲት ክርስቲያን አማካሪ ዘንድ ሄደች። ችግሯን ዘርዝራ ከተናገረች በኋላ "አማካሪዋ" ማድረግ ያለባትን አራት ነጥብ የያዘ መመሪያ ሰጠቻት። መመሪያውም፥

1) በአሳየሽው መጥፎ ጠባይ ማዘንሽን ገልጸሽ ባልሽን ይቅርታ ጠይቂው፥
2) ዛሬ ማታ ጥሩ እራት አዘጋጅተሽ አብዪው፥
3) በልዩ ሁኔታ እያቀፍሽ ሳሚው፥
4) ቢያንስ ቢያንስ ለአንድ ሳምንት ያህል በሚሰጠው አሳብ

ላይ ምንም ዓይነት ነቀፌታ አታሰሚው የሚል ነበር። ያቺ ሴት አማካሪዋን ለሁለተኛ ጊዜ የምታነጋግርበት ቀጠሮ አንድ ቀን ሲቀረው፥ ደውላ "የሰጠሽኝ አራት ነጥብ ጥሩ አድርጎ ሠርቶልኛል! እኔና ባሌ ሁለተኛ ጫጉላ ላይ እንዳለን እየተሰማን ነውና ሌላ ተጨማሪ ምክር አያስፈልገኝም" አለቻት። ምክር ፈላጊዎች ከላይ እንዳየናት ሴት የተሰጣቸውን ምክር በተግባር ላይ ቢያውሉት፥ ዕርዳታ ፈላጊዎችን ደስተኛ የሚያደርጋቸው ከመሆኑም በላይ፥ የመካሪዎችን ድካም ፍሬያማ ያደርገው ነበር።

3.2. የመምከር ስጦታ ያለው ሰው፥ ሌሎች እንዲያገለግሉ ያደፋፍራል፥

የመምከር ስጦታ ያለው፥ ሌሎች አገልጋዮች በአገልግሎታቸው ፍሬያማ እንዲሆኑ መምከርና ማደፋፈር ደስ ይለዋል። በክርስቶስ አካል ውስጥ የተለያዩ የአካል ክፍሎች እንዳሉና እንዴት እንደሚሠሩ ማወቅ ብቻ ሳይሆን፥ ሌሎችም ይህንን ተረድተው በአካሉ ውስጥ ሥፍራ እንዲኖራቸው ይፈልጋል። የቤተ ክርስቲያን መጋቢ "የመምከር ስጦታ" ካለው፥ ምዕመናን ሁሉ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ አገልግሎት እንዲኖራቸው ያበረታታል! እንዲያገለግሉም ዕድል ይሰጣል። የመምከር ስጦታ ያለው አማኝ፥ ክርስቲያኖች እጃቸውን አጣምረው እንዲቀመጡ አይፈልግም። በአንድ ዓይነት አገልግሎት ውስጥ ገብተው እንዲሳተፉና እግዚአብሔር በሰጣቸው ስጦታ ሌሎችን እንዲጠቅሙ ያደፋፍራል።

3.3. የመምከር ስጦታ ያለው ሰው፥ የግል ሕይወቱን አይደብቅም

የመምከር ስጦታ ያለው ሰው፥ ምክር ለመስጠት ሁል ጊዜ ንቁ ነው። ጥያቄ ያለው፥ የተቸገረ፥ እርዳታ የሚፈልግ ሰው ሲያጋጥመው፥ ምክር ለመስጠት ይቸኩላል። ምክር

ሰጪው አገልግሎቱን ፍሬያማ ከሚያደርጉለት ነገሮች መካከል አንደኛው፥ በግል ሕይወቱ ውስጥ ካጋጠመው ችግር እን ዴት አድርጎ እንዳለፈ የተማረውን ትምህርት ለሌላው ማስተ ላለፍ ሲችል ነው። ምክር ፈላጊ፥ ከራሱ ሕይወት የተለማመ ደውንና ያለፈበትን መናገር ከሚችል አማካሪ ጋር መወያያ ትና እርዳታ መፈለግ ይቀለዋል። "እርሱ እንዲህ አድርጎ ከተሳካለት፥ እኔም ይሳካልኝ ይሆናልI እርሱ ይህን ዓይነት ድካምና ችግር ከነበረበት፥ እኔ የተለየሁ አይደለሁም" በማለት ተስፋ ያደርጋል። የመምከር ስጦታ ያለው ሰው የግል ሕይወ ቱን ገላልጦ ለሌላው መናገር አይከብደውም። ድካሙን ደብቆ "ፍጹምነቱን" ለማሳየት አይሞክርም።

3.4. የመምከር ስጦታ ያለው ሰው፥ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ምክሩን ያቋርጣል

የመምከር ስጦታ ያለው ሰው ዕርዳታ የሚፈልጉትን ሰዎች መርዳት ደስ ይበለው እንጂ፥ የምክር አገልግሎቱን የሚያቋርጥበት ጊዜ አለ። መምከር ደስ ስለሚለው ብቻ ምክር አይሰጥም። ዕርዳታ ፈላጊው ምክሩን በተግባር ላይ ማዋል አለበት። ካልሆነ፥ "የነገርኩህን ነገር በሥራ ላይ የማታውለው ከሆነ፥ የምነግርህን መቀበል የማትፈልግ ከሆነ፥ ምክሬን የማ ትሰማ ከሆነ፥ ልረዳህ አልችልም። የራስህንም፥ የእኔንም ጊዜ ታጠፋለህና እዚህ ላይ ብናቆም ይሻላል" በማለት ይነግረዋል። የምክር ሰጪዎች አገልግሎት ፍሬያማ እንደሆነ የሚታየው አማካሪዎች ባላቸው ችሎታ፥ ወይንም ልምምድ ሳይሆን፥ ምክር ፈላጊዎች ምክሩን በተግባር ላይ ሲያውሉት ብቻ ነው። ተመካሪው ምክሩን በተግባር ላይ የማያውል ከሆነ፥ የመካሪው ልፋት ዋጋ ቢስ እንደሚሆን ግልጽ ነው። መካሪው ጊዜውንና ጉልበቱን በአግባቡ ለመጠቀም ስለሚፈልግ፥ ምክሩን የማይ ቀበለውን ሰው ትቶ፥ ፊቱን ምክሩን ወደሚቀበለው ዕርዳታ ፈላጊ ያዞራል።

3.5. የመምከር ስጦታ ያለው ሰው፥ አሳቡን መግለጽ ይችላል

የመምከር ስጦታ ያለው ሰው አገልግሎቱን የሚፈጽመው በንግግር ነው። "የመምከር ስጦታ አለኝI ግን አሳቤን ገልጬ ማስረዳት አልችልም" የሚል አማኝ ቢኖር፥ በእርግጥ ያ ሰው የመምከር ስጦታ እንዳለው ያጠራጥራል። የመምከር ስጦታ ያለው ሰው የልቡን አሳብ ሳይጨነቅ እንደልቡ ገልጾ የማስረ ዳት ችሎታ አለው። "እንዴት ልናገር?" ብሎ አያስብም። በተፈጥሮው ራሱን በንግግር ጥሩ አድርጎ መግለጽ ይችላል።

3.6. የመምከር ስጦታ ያለው ሰው፥ በሰው ላይ አይፈርድም

ሰው ሁሉ ሌላውን የሚመለከትበት የራሱ የሆነ አቋም አለው። አንዳንዶች ሌላውን የሚያዩት "ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ነው" ወይንም "አይደለም" ብለው ነው። በመካከል መሆን ይችላል አይሉም። የመምከር ስጦታ ያላቸው ሰዎች ግን ስለ ሌላው ያላቸው አመለካከት የተለየ ነው። በሁሉም ነገር ፍጹም የሆነ፥ ወይንም ሙሉ በሙሉ ተስፋ የሌለው ማንም የለም ብለው ያምናሉ። ስለዚህ የሚመክሩት ሰው ምንም ያህል የተበላሸ ሕይወት ቢኖረውም፥ ያ ሰው ፍጹም ለመለወጥ ተስፋ የለውም በማለት አይፈርዱም። በመፍረድ ፈንታ የሚረዱትን ሰው ልክ እንዳለ በመቀበል መመሪያ በመስጠት፥ ትክክለኛ አቅጣጫ እንዲይዝ ያደፋፍሩታል። የመምከር ስጦታ ያለው አማኝ ብዙዎቹን መርዳት የሚችለው በሰው ላይ የማይፈርድ፥ በድካሙ ላይ ብቻ ትኩረት የማይ ሰጥ በመሆኑ ነው። የመምከር ስጦታ ያላቸው ሰዎች በፍቅር የተሞሉ፥ ይቅር ባዮችና ሌሎችን ልክ እንዳሉ መቀበል የሚችሉ ናቸው።

☆ ☆ ☆ ☆